# ● መጽሐፈ ድጓ ላይ የተጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው ●



አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው ካሣ

(የመጻሕፍተ ሊቃውንት፣ የመጻሕፍተ ብሉያትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)

ሐምሌ ፳፪፣ ፳፻፲፫ ዓ.ም

## መጽሐፈ ድጓ ላይ የተጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

፩. መምህር ዮሐንስ ንጉሥ ክርስቶስን ባየው ጊዜ እነሆ የእግዚአብሔር በግ አለ ይላል። የእግዚአብሔር በግ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር በግ፣ የእግዚአብሔር ቃል እየተባለ ይጠራል። ይህ ግን ብዙ ጊዜ እኛ ከለመድነው ዘርፍ የተለየ ዘርፍ ነው። ለምሳሌ የሰው በግ ብንል ዘርፉ ሰውና ባለቤቱ በግ በባሕርይ የተለያዩ ናቸው። ወደ እግዚአብሔር ስንመጣ ግን ከዚህ የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን። ዘርፉ ባለቤቱን ነው። ቃል ራሱ እግዚአብሔር ነው። በግዕ የተባለውም ራሱ እግዚአብሔር ነው። ይህ ከሆነ ለምን በግ ተባለ ከተባለ ደግሞ በብሉይ ኪዳን በበግ መሥዋዕት ሰዎች ከሚመጣ መቅሠፍት ይድኑበት ነበር። ይህ ብቻ ሳይሆን ለደኅንነታቸው የሚሠዉት የድኅነት መሥዋዕት ነበር። ያንን ምሳሌ አድርጎ ክርስቶስም በሥጋም በነፍስም ከሚመጣ መቅሠፍት የምንድንበት በመስቀል ተሰቅሎ የሚያድነን መሥዋዕት በመሆኑ እስከ ሱታፌ አምላክነት ድረስ የምንደርስበት አማናዊ የድኅነት መሥዋዕት በመሆኑ በግ ተብሏል። "ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷል" እንዲል (1ኛ ቆሮ.5፥7)። በብሉይ ኪዳን መሥዋዕቱ በግ፣ መሥዋዕቱን የሚቀበል እግዚአብሔር፣ መሥዋዕቱን የሚያቀርበው ደግሞ ሊቀ ካህናት ነበር። ክርስቶስ ግን በመስቀል ላይ ራሱ መሥዋዕት፣ ራሱ መሥዋዕት አቅራቢ፣ ራሱ መሥዋዕት ተቀባይ ሆኖ አድኖናል። "ወውእቱ በግዐ መሥዋዕት ወውእቱ ካህን ሠዋዒ ወውእቱ ተወካፌ መሥዋዕት ምስለ አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ" እንዲል (ሃይ.አበ.36፥26)።

፪. ዮሐንስ መጥምቅን ወንጌላዊ ሲለው ወንጌልን ጽፏል እንዴ?

መልስ፦ በእርግጥ ወንጌልን መጻፍ ወንጌላዊ ያሰኛል። በዚህ መንገድ ወንጌልን የጻፉ አራቱ ማቴዎስ፣ ዮሐንስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ ወንጌላውያን ይባላሉ። በተጨማሪም በሐዲስ ኪዳን ሌሎች ቅዱሳን ያስተማሩት ትምህርትም ወንጌል ይባላል። ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ "ስለዚህ በሚቻለኝ መጠን በሮሜ ላላችሁ ለእናንተ ደግሞ ወንጌልን ልሰብክ ተዘጋጅቻለሁ" ብሏል (ሮሜ 1፥15)። ወንጌል ማለት የምሥራች ማለት ነው። ዮሐንስ መጥምቅም መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ እያለ አስተምሯልና ወንጌላዊ ተብሏል።

፫. መምህር ክርስቶስን ያጠመቀ ካህን ዮሐንስ በእውነት ከመላእክት ይበልጣል ይላል። ከመላእክት የሚበልጠው በምንድን ነው? እንዲሁ "ርእዩ ዕበዮ ለዮሐንስ ዘመላእክት ይሰግዱ ሎቱ ኀይለ ልዑላን ኪያሁ ይሴብሐ----ታላላቅ ኀይሎች እርሱን የሚያመሰግኑት፣ መላእክት የሚሰግዱለትን የዮሐንስን ታላቅነቱን እዩ" ይላል። መላእክት ዮሐንስን ያመሰግኑታል? ይሰግዱለታል?

መልስ፦ መብለጥ መበላለጥ አንጻራዊ ነው:: ቅዱስ ኤፍሬም አምላክን በሥጋ በመውለዷ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን እርሷ ከኪሩቤል ትበልጣለች ብሎ ነበር:: ቅዱስ ያሬድ ደግሞ ከዚህ ጌታን በማጥመቁ ዮሐንስን ከመላእክት ይበልጣል ብሎታል:: መላእክት ዮሐንስን አመሰገኑት የሚለው የአድናቆት የጸጋ የክብር ምስጋና ነው:: ጌታ በምጽአት ጊዜ ጻድቃንን የአባቴ ቡሩካን ብሎ እንደሚያመሰግናቸው ያለ ነው:: መላእክትም በእግዚአብሔር ሕግ የሚሔድ ሰው ሲያዩ ያመሰግኑታል:: ይሰግዱለታል መባሉም የአክብሮት ስግደት ነው:: ለድንግል ማርያም ጌታን በመውለዷ የአክብሮት ስግደት እንደሚሰግዱ ጌታን ላጠመቀው ዮሐንስም የአክብሮት ስግደትን ይሰግዱለታል ማለት ነው::

**፬. ዮሐንስ መጥምቅ መታሰቢያው በርእሰ ዐውደ ዓመት ለምን ሆነ? ሁልጊዜ መታሰቢያው በመስከረም ፩ ቀን ነው?**

መልስ፦ ዮሐንስ ሰማዕት የሆነ መስከረም ፪ ቀን ነው:: በመጻሕፍት ልማድ ደግሞ የጎደለ ሞልቶ የተረፈ ትቶ መግለጽ ልማድ ስለሆነ መስከረም ፩ ቀንም አንድ ቀን ከተረፈ ብሎ ቅዱስ ዮሐንስ ተብሏል:: ወንጌላዊው ዮሐንስ በዋለበት ዓመት ሲሆን ደግሞ ለወንጌላዊው አድሎ መናገር ነው:: ዞሮ ዞሮ ዮሐንስ መጥምቅ መታሰቢያው በርእሰ ዐውደ ዓመት (የዐውደ ዓመት መጀመሪያ) የሆነው ሰማዕት የሆነው መስከረም 2 ቀን ስለሆነ ነው:: ስለሆነም ሰማዕት የሆነበት ቀንና ዋና መታሰቢያው መስከረም 2 ነው::

**፭. መጽሐፈ ድጓ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ በትግርኛ ቋንቋ ድጓዕ ማለት መዝሙረ ኀዘን፣ ሙሾ፣ ሰቆቃው ማለት ነው:: ሰቆቃወ ኤርምያስ ለማለት ድጓዐ ኤርምያስ እንዲል:: ስለዚህ መጽሐፈ ድጓ ማለት መጽሐፈ መዝሙር ማለት ነው:: አንድም ድግ ማለት ትጥቅ ማለት ነው:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን በአገልግሎት ያሸበረቀ በመሆኑ ድጓ ድጓ ለቤተክርስቲያን ይባላል::

**፮. ዮሐንስ ጌታውን መራ ወደ ዮርዳኖስ አደረሰ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ከዚህ ይህ የጌታ መመራት ፈቃዳዊ መመራት ነው:: ይህም ማለት ዮሐንስኒ ሀሎ ያጠምቅ በሄኖን ስለሚል ክርስቶስ ደግሞ ከዮሐንስ መጠመቅ ፈቃዱ ስለሆነ ነው:: ጌታ ዮሐንስ ወዳለበት በመሔዱ ጌታውን መራው ተብሏል:: እንጂ ጌታ በፍጡር የሚመራ ስላልሆነ አመራራዊ ወይም አዛዥዊ መምራት አይደለም::

**፯. ዮሐንስ ሆይ የግንብ ቤቶችን ንቀህ በሰማያት ያለ ቤትን በማሰብ ልብስህን የግመል ጸጉር አደረግህ ይላል:: የግንብ ቤቶችን ትተህ ያለው ዮሐንስ የግንብ ቤት ነበረው ወይ?**

መልስ፦ ዮሐንስ ከሕፃንነቱ ጀምሮ በበረሃ ያደገ በመሆኑ የግንብ ቤቶች አልነበሩትም። ነገር ግን ከበረሃ ወጥቶ እንደሌሎች ሰዎች የግንብ ቤቶችን ሠርቶ መኖር እየቻለ ስለእግዚአብሔር በበረሃ መኖርን መርጧልና "የግንብ ቤቶችን ትተህ" ተብሏል። ትተህ የሚለው የፈቃድ መተውን ያመለክታል።

፰. ቤተክርስቲያን ወደ ዮሐንስ ክርስቶስ አንተ ነህን ስትል አሰምታ ተናገረች። እርሱም እኔስ ክርስቶስን አይደለሁም አላት። ዮሐንስን የጠየቀችው ቤተክርስቲያን ያላት የትኛዋን ቤተክርስቲያን ነው?

መልስ፦ ቤተክርስቲያን ያላት ምእመንን፣ ማኅበረ ምእመንን ነው። በዘመኑ ተጠምቀው፣ ልጅነትን አግኝተው የነበሩ ምእመናን ኖረው አይደለም። ከብዙ የጽሑፍ ስልቶች መካከል አንዱ የአሁኑን ወደኋላ ሄዶ መጠየቅ ወይም አሁን ላይ ሆኖ ትላንትን መጠየቅ ይጠቀሳል። ለምሳሌ አባ ሕርያቆስ በኋላ ዘመን ተነሥቶ የሐዋርያትን ሥራ ለራሱ አድርጎ "በላዕነ ወሰተይነ ምስሌሁ" ብሏል (ቅዳሴ ማርያም)። የኋላ ምእመናን የቀድሞ ሰዎች የጠየቁትን ጥያቄ ጥያቄ አድርገው ዮሐንስን ይጠይቁታል። ለቀድሞ ሰዎች የመለሰላቸውን መልስ ደግሞ የኋላ ሰዎችም ተቀብለው ይመሰክራሉ (ዮሐ.1፥20)። እንጂ ዮሐንስ ለኋላ ምእመናን ከሞት ተነሥቶ ጠይቀውት እርሱም መልሶላቸው አይደለም።

፱. ዮሐንስ መጥምቅ እና ቅዱስ ያሬድ ሞትን ቀምሰዋል ወይስ የለም?

መልስ፦ ዮሐንስ መጥምቅ አዎ ሞትን ቀምሷል። ቅዱስ ያሬድን በተመለከተ ሁለት አይታዎች አሉ። እነዚህም አንደኛው አልሞተም ተሠወረ እንጂ የሚል ሲሆን ሁለተኛው ሞቷል የሚል ነው። የግንቦት 11 ስንክሳር አረፈ (ሞተ) ብሎ መቃብሩ ግን እንዳልታወቀ "ወመቃብሪሁሰ ኢተዐውቀ እስከ ዮም" ብሏል። ገድሉና ድርሳኑም "ወቅዱስሰ ያሬድ ካህን ፈጸመ ገድሎ በምድረ ሰሜን ወአዕረፈ። ወሀሎ ሥጋሁ እስከ ይእዜ በምሥራቀ ሰሜን እንዘ ኢይትዐወቅ ወኢይትከሠት ኢለመኑሂ" ይላል። ስለዚህ ከሁለቱ አይታዎች መጽሐፋዊ ማስረጃ ያለው ማረፉ ነው።

፲. ዮሐንስ ልብስ የግመል ጸጉር ነው ይላል። የግመል ጸጉር ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ከግመል ከጫንቃዋ ከጋማዋ ቢፈለግ ጥቂት ጸጉር ስለማይታጣ እናቱ ኤልሳቤጥ ሰው እንዳይጣላው ብላ ከዚያ ልብስ አሠርታ አልብሰዋለችና ነው (ማቴ.3፥4 ትርጓሜ)።

፲፩. ካህን ዮሐንስ ብርሃን ክርስቶስን ባየው ጊዜ እነሆ የእግዚአብሔር በግ አለ ይላል። ዮሐንስ እንዴት ክህነትን አገኘ?

መልስ፦ ዮሐንስ ክህነትን መቼና እንዴት እንዳገኘ የተጻፈ ነገር አላገኘሁም። አላውቀውም። ቅዱስ ያሬድ ግን ዮሐንስ ካህን እንደነበረ ገልጾልናል።

፲፪. ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ ካህን በማድረግ ዮሐንስን እግዚአብሔር ከፍ ከፍ አደረገው ሲል እግዚአብሔር ከማሕፀን ለይቶ ካህን አድርጎ ሲመርጥ ለጽድቅና ለኃጢአት ቀድሞ ወስኗል አያስብልም?

መልስ፦ አያስብልም። እግዚአብሔር ሲመርጥ የኋላን ሁኔታ አውቆ ነው። ዮሐንስ ካደገ በኋላ በራሱ ነጻ ፈቃድ እግዚአብሔርን በንጹሕ ልብ እንደሚያገለግል እግዚአብሔር ስላወቀ ካህን አድርጎታል። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ነጻ ፈቃድን ሰጥቷል። ከዚህ በኋላ ሰዎች መልካም ቢሠሩም ራሳቸው ፈቅደው የሚሠሩት ነው። ክፉ ቢሠሩም ራሳቸው መርጠው የሚሠሩት እንጂ ሌላ አስገዳጅ አካል የለም። ሰዎች ምንን መርጠው እንደሚሠሩ ደግሞ እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ስለሆነ አስቀድሞ ያውቃል። ይህ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ተመሳሳይ ነው። ከሰው ልጆች ሁሉ ንጽሕት እንደምትሆን አውቆ ከማሕፀን ጀምሮ ከመርገም ጠብቋታል። ነቢዩ ኤርምያስም በኋላ በሚሠራው መልካም ሥራ ምክንያት ቀደስኩከ እምከርሠ እምከ (ከእናትህ ማሕፀን ጀምሮ መረጥኩህ) ተብሏል።

፲፫. ሰማዕት ወደ ርስታቸው መንግሥተ ሰማያት ተሻገሩ ሲል ምን ማለት ነው? ከእመቤታችን በቀር መንግሥተ ሰማያት የገባ አለ ወይ? ዳግም ምጽአት ሳይከናወን መንግሥተ ሰማያት ይገባል ወይ?

መልስ፦ በገነት የነበሩ ሰዎች በኋላ በምጽአት ወደ መንግሥተ ሰማያት ስለሚገቡ የገነቱን ለመንግሥተ ሰማያት ሰጥቶ ተናግሮ ነው እንጂ ከምጽአት በፊት ወደ መንግሥተ ሰማያት ገብተው አይደለም። መንግሥተ ሰማያት የሚገባ ከምጽአት በኋላ ነው። መተርጉማን ደጀ ሰላምን በገነት፣ ቤተክርስቲያንን በመንግሥተ ሰማያት የመሰሉበት ምክንያት ለዚህ ነው። ከደጀ ሰላም ቤተክርስቲያን እንደምትከብር ሁሉ ከገነትም መንግሥተ ሰማያት የከበረች ናት። ቤተክርስቲያን የሚገባ ሰው ደጀ ሰላም ቆይቶ እንደሚገባ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ ሰውም ገነት ቆይቶ ይገባል። ደጀ ሰላም ያለ ሰው ከቤተክርስቲያን አለሁ እንደሚል በገነት ያሉትም በኋላ መንግሥተ ሰማያት ስለሚገቡ ወደ መንግሥተ ሰማያት ገቡ ይባላል።

፲፬. ዮሐንስ ክርስቶስ ካጠመቀ በኋላ ራሱ ተጠመቀ ሲል ምን ማለት ነው? ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ ተመልሶ ዮሐንስን አጠመቀው ማለት ነው?

መልስ፦ ቅዱስ ያሬድ ዮሐንስ ጌታን ካጠመቀው በኋላ እርሱ ራሱ ዮሐንስም መጠመቁን ገልጿል። የጥምቀቱ ሂደትና ቅደም ተከተል ምን እንደነበረ ግን ዘርዘር አድርጎ አልገለጸውም። ስለዚህ አላውቀውም።

**፲፭. ዮሐንስ ጌታን ሲያጠምቀው በክርስቶስ ራስ ላይ ውሃዎች ፈሉ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ዮሐንስ ጌታን ሲያጠምቅ ውሃን እየጠለቀ በጌታ ራስ ሲያፈስስ ውሃዎች በጌታ ራስ ላይ ይፈሉ ነበር ማለት ነው:: ፈልሐ ማያት ዲበ ርእሱ ያለው ይህንን ነው:: ይህም የተጠመቀው ክርስቶስ የሕይወት ውሃ ከመሆኑ በተጨማሪ እሳተ መለኮት መሆኑንም ያስረዳናል::

**፲፮. "ብፁዓን እሙንቱ ካህናት ውሉደ ብርሃን በሃይማኖት ድኅኑ እምኵናት" ይላል:: ድኅኑ እምኵናት ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ይህ መሠረት የሚያደርገው እስራኤላውያን ካህናት ዮርዳኖስን ሲሻገሩ የነበረውን ኩነት ነው:: እስራኤላውያን ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድረ ርስትን ሲወርሱ ብዙ ጦርነቶችን አድርገው ስለነበር ነው:: ከዚያ ሁሉ ድነው ምድረ ርስትን ወርሰዋል:: ፍጻሜው ግን ማንኛውም ካህንና ምእመን በሃይማኖት ከልዩ ልዩ መከራዎች እንደሚድን ያመለክታል::

**፲፯. ዮሐንስ ከነቢያት በኋላ እና ከወልድ መምጣት በፊት የኃጢአታቸውን ቤዛ አጠምቅ ዘንድ ተላክሁ ብሎ አሰምቶ ተናገረ ይላል:: የኃጢአታችውን ቤዛ ማለቱ ምን ለማለት ነው?**

መልስ፦ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛችን ነው ስንል እኛ በሠራነው በደል፣ እኛ በሠራነው ኃጢአት ሞት ይገባን የነበረ ቢሆንም የእኛን ሞት ሞቶ እኛን ማዳኑን ለመግለጽ ነው:: ስለእኛ ኀጢአት በመሰቀሉ የኃጢአታችን ቤዛ ተብሏል::

**፲፰. አንተም ሕፃን የልዑል ነቢይ ትባላለህ ብሎ ዘካርያስ በልጁ ላይ ትንቢት ተናገረ:: ይህን የተናገረው የሥጋ አባቱ ካህኑ ዘካርያስ ነው ወይስ ነቢዩ ዘካርያስ ነው? የቅዱስ ዮሐንስ አባት ዘካርያስ እና የትንቢተ ዘካርያስ ጸሓፊ ዘካርያስ ይለያያሉ ወይስ አንድ ሰው ነው?**

መልስ፦ ወአንተኒ ሕፃን ነቢየ ልዑል ትሰመይ ብሎ ትንቢት የተናገረ የሥጋ አባቱ ዘካርያስ ነው (ሉቃ.1፥76):: ከደቂቀ ነቢያት አንዱ የሆነው ዘካርያስና የዮሐንስ አባት ዘካርያስ በተለያዩ ዘመናት የነበሩ የተለያዩ ሰዎች ናቸው::

**፲፱. ዮሐንስ ክርስቶስን ሲያጠምቀው እጁን አልጫነበትም ይባላል:: ሥዕላትም የሚሳሉት በዚያው መንገድ ነው:: ድጓ ላይ ግን ራሱን ዳሰሰው ይላልና ቢያስታርቁልኝ::**

መልስ፦ ቅዱሳት ሥዕላት ዮሐንስ ሳይዳስሰው በፊት የነበረውንና ውሃ በእፍኙ ይዞ ሲያጠምቀው የነበረውን ኩነት ለመግለጽ እጁን ረቦ አሳይተዋል:: ቅዱስ ያሬድ ደግሞ እጁን ረቦ ብቻ ሳይሆን የጌታን ራስንም እንደዳሰሰ ለመግለጽ ወገሠሦ እንተ ኢትትገሠሥ ርእሶ ብሏል:: ዳሰሰው ካለ እንደገና ኢትትገሠሥ (የማትዳሰስ) ለምን አለ ከተባለ በመለኮቱ ከመዳሰስ ሩቅ ስለሆነ ነው:: ታዲያ መልሶ ዳሰሰው ለምን አለ ከተባለ

የቃል ገንዘብ ለሥጋ፣ የሥጋ ገንዘብ ለቃል ሆኗልና። ራሱ የመለኮት ገንዘብ በመሆኑ ነው።

**፳. ከካህኑ ዘካርያስ ወገብ ኮከብ ወጣ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ደጋግ ሰዎችን ኮከብ ማለት መጽሐፋዊ ልማድ ነው። ከአብርሃም የሚወለዱ ደጋግ ሰዎችን ለመግለጽ "አበዝኖ ለዘርዕከ ከመ ኮከበ ሰማይ" እንዳለ (ዘፍ.26፥4)። ቅዱስ ጳውሎስም ክብረ ቅዱሳንን ለመግለጽ "ኮከብ እምኮከብ ይኄይስ ክብሩ" ብሏል (1ኛ ቆሮ.15፥41)። በዚህ አግባብ ቅዱስ ያሬድ ዮሐንስ መጥምቅን ኮከብ ብሎታል። ኮከብ ዮሐንስ ከዘካርያስ ተወለደ ማለት ነው።

**፳፩. አበዮ ዮሐንስ ወይቤሎ ባዕደ ሶበ አጠምቅ በስምከ አጠምቅ። ወኪያከ ሶበ አጠምቅ እግዚኦ ምንተ እብል። በስምከ ሲል ምን ማለት ነው? የዮሐንስ ጥምቀት ዓይነት አሁን አለ?**

መልስ፦ የዮሐንስ ጥምቀት የንስሓ ጥምቀት ነው። ምንም እንኳ የንስሓ ጥምቀት ቢሆንም ነቢየ እግዚአብሔር እንደመሆኑ በእግዚአብሔር ስም ያጠምቅ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስም እግዚአብሔር ስለሆነ ሌላውን በስምህ አጠምቃለሁ ብሎታል። የዮሐንስ ዓይነት ጥምቀት አሁን የለም። ምናልባት አንዳንድ ካህናት በቀኖናቸው በጠበል መጠመቅንም ካካተቱት የዮሐንስን ጥምቀት ይመስላል እንጂ።

**፳፪. "አቤቱ ከጥልቁ ልቤ ጠራውህ። ከጥልቁ ማለት ከልብ ሥር ማለት ነው" ይላል። የልብ ስር ማለት ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ አሁን ለነፍስ የለባዊነት ከዊን ሥር ኖሮት አይደለም። ፍጹም መሻቱን፣ ፍጹም መፈለጉን ለመግለጽ ከልቤ ሥር ጠራውህ ብሏል። ይኸውም ፊጽሜ ጠራውህ ማለት ነው። የልብ ሥር ያለው ፍጹም መሻቱን ነው።

**፳፫. "ኢየሱስ ዮሐንስን ውሃ ተቀድሶ ለሰው ልጆች መድኀኒት ይሆን ዘንድ በውሃ አጥምቀኝ አለው" ይላል። ውሃ ተቀድሶ ለሰው ልጆች መድኀኒት ይሆን ዘንድ ሲል ምን ለማለት ነው?**

መልስ፦ በኦሪት ዘፍጥረት እንደምንመለከተው በሥነ ፍጥረት መንፈሰ እግዚአብሔር በውሃዎች ላይ ሰፍፎ ይኖር ነበር (ዘፍ.1፥2)። ይህን መንፈስ መሻ*ፍ-ቃ/ን የተባለ ሊቅ በነፋስ ቢተረጉመውም ሳዊሮስና መተርጒማነ ኦሪት ደግሞ በቅደም ተከተል በመንፈስ ቅዱስና በልጅነት ተርጉመውታል። በኋላ የሰው ልጆች ሲያጠፉ በውሃ ጠፉ (ዘፍ.7፥10)። ከዚያ በኋላ ውሃ የመርገም ምልክት ተደርጎ ይታይ ነበር። ክርስቶስ ከተጠመቀበት በኋላ ግን ያ የመርገም ምልክት ውሃ የበረከት የልጅነት ምንጭ ሆኗልና ውሃ ተቀድሶ የሰው ልጆች መድኀኒት ሆነ ተብሏል።

**፳፬. የልቡናችንን ዓይን ይገልጽልን ዘንድ እንግዲህ የክርስቶስን መንፈስ እንቀበል ይላል። የክርስቶስን መንፈስ እንቀበል ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ቅዱስ ያሬድ የክርስቶስ መንፈስ ብሎ ከዚህ የገለጸው ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ነው:: ሀብተ መንፈስ ቅዱስን እንቀበል ማለት ነው:: በእርግጥ መንፈስ የሚለው ቃል በብዙ መንገድ ይተረጎማል:: መንፈስ ነፋስ ተብሎ ይተረጎማል:: "እስመ መንፈስ ኀበ ፈቀደ ይነፍኅ:: ወቃሎ ትሰምዕ:: ወኢተአምር እምኀበ ይመጽእ ወኀበሂ የሐውር" እንዲል (ዮሐ. ፫፥፰):: ትርጉሙም ነፋስ በወደደው ይነፍሳል:: ባሕር ሲገሥጽ ዛፍ ሲያናውጥ ትሰማዋለህ:: ወዴት እንደሚሄድ ከየት እንደሚመጣ አታውቀውም ማለት ነው:: መንፈስ ነፍስ ተብሎም ይተረጎማል:: "ወጸርሐ ካዕበ እግዚእ ኢየሱስ በዐቢይ ቃል ወወፅአት መንፈሱ ሶቤሃ" እንዲል (ማቴ. ፳፯፥፶):: ትርጉሙም ጌታም ሁለተኛ አሰምቶ ተናገረ ያን ጊዜም ነፍሱ ከሥጋው ተለይታ ወጣች ማለት ነው:: መንፈስ ሰይጣን ተብሎም ይተረጎማል:: "ጋኔን እኩይ አው መንፈስ ርኩስ" እንዲል (ጦቢ.፮፥፰):: አጋንንት ርኩሳን መናፍስት እየተባሉ ይጠራሉ:: መንፈስ ምትሐት ተብሎም ይተረጎማል:: ምትሐት ማለት የማይጨበጥ የማይዳሰስ ነገር ግን የሚዳሰስና የሚጨበጥ የሚመስል ነው:: ይኸውም እንደ ጥላ ያለ ነው:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኂላ በቶማስ ተዳሷል:: ይኸውም ምትሐት እንዳልሆነ ለማጠየቅ ነው:: "ወደንገፁ ወፈርሁ ወመሰሎሙ ከመ ዘመንፈሰ ይሬእዩ" እንዲል:: ጌታ ራሱም ለምትሐት ሥጋ አጥንት እና በጠቅላላው የሚዳሰስ ነገር እንደሌለው ለሐዋርያት ሲያስረዳ "ርእዩ እደውየ ወእገርየ ከመ አነ ውእቱ ወግሥሡኒ ወአእምሩ እስመ ለመንፈስሰ አልቦቱ ሥጋ ወዐፅም በከመ ትሬእዩ ብየ" ብሏቸዋል (ሉቃ.፳፬፥፴፱):: መንፈስ ልብ፣ ዕውቀት ተብሎም ይተረጎማል:: "ወእሁቦሙ መንፈሰ ሐዲሰ" እንዲል (ሕዝ.፲፩፥፲፱):: መንፈስ ትምህርት ተብሎም ይተረጎማል:: "አኃዊነ ለኵሉ መንፈስ ኢትእመንዋ:: አላ አመክርዋ ለመንፈስ ለእመ እምኀበ እግዚአብሔር ይእቲ" እንዲል (፩ኛ ዮሐ.፬፥፩):: ወንድሞቻችን መንፈስን ሁሉ አትመኑ:: ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተገኘች እንደሆነች መርምሩ ተብሏል:: በዚህ ጊዜ ትምህርትን መንፈስ እንዳላት አስተውል:: መንፈስ መልአክ ተብሎም ይተረጎማል:: "አኮኑ ኵሎሙ መላእክት መንፈስ እሙንቱ ወይትፌነው ለመልእክት በእንተ እለ ሀለዎሙ ይረሱ ሕይወተ ዘለዓለም" እንዲል (ዕብ.፩፥፲፬):: መንፈስ መንፈስ ቅዱስ ተብሎም ይተረጎማል:: በዚህ ጊዜ ከሦስቱ አካላት አንዱን ያመለክታል (ማቴ.፳፰፥፲፱፣ ሉቃ.፫፥፳፪):: ይኸውም ከአብ የሠረፀ አካላዊ ሕይወት ነው:: "እስመ መንፈሰ እግዚአብሔር መልአ ዓለመ ወዘይእኀዝ ኵሎ ዓለመ" እንዲል (ጥበ.፩፥፯):: መንፈስ መለኮት ተብሎም ይተረጎማል:: "በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ" እንዲል (፩ኛ ጴጥ.፫፥፲፰):: በዚህ ጊዜ በመለኮት ሕያው መሆኑን ያመለክታል:: ቅዱሳት መጻሕፍት ሀብተ መንፈስ ቅዱስን፣ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን "መንፈስ ቅዱስ" ሲሉትም ይገኛሉ:: ለምሳሌ ሉቃስ ወንጌል ላይ ስለ ዮሐንስ መጥምቅ "ወይመልእ ላዕሌሁ መንፈስ ቅዱስ እምከርሠ እሙ" ተብሏል (ሉቃ.፩፥፲፭):: በዚህ ጊዜ ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ገንዘብ ያደርጋል ማለት ነው እንጂ አካለ መንፈስ ቅዱስን በምልዐት ገንዘብ ያደርጋል ማለት አይደለም:: አካለ መንፈስ ቅዱስ በዓለም ሁሉ የመላ ነውና:: አካለ መንፈስ ቅዱስ የሌለበት ቦታ የለም:: በኅድረት በዮሐንስ አካል ይመላበታል

ለማለት ነው እንዳይሉ አካለ መንፈስ ቅዱስ በዮሐንስ አካል ብቻ ሳይሆን በዓለም ሁሉ ያለና ዓለምን የሚተርፍ ነው:: ስለዚህ በተለየ በዮሐንስ ይመላል ያለው ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ያድርበታል ሲል ነው:: በኤልሳቤጥ መንፈስ ቅዱስ ሞላባት የሚለውም እንዲሁ ነው:: ኤልሳቤጥ ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ገንዘብ አድርጋ ድንግል ማርያምን ጌታን አመሰገነች ማለት ነው:: በተጨማሪ ጌታ ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን አሳደረባቸው ተብሏል:: ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ሰጣቸው ማለት ነው:: "ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ" እንዲል (ዮሐ.፳፥፳፪):: የሐዋርያት ሥራ ላይ "ጴጥሮስ ይህን ነገር ገና ሲናገር ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ" ተብሏል (የሐዋ. ሥራ ፲፥፵፬):: ወረደ ማለት ምሥጢር ገለጠላቸው ሀብቱን ሰጣቸው ማለት ነው እንጂ በአካል ነው እንዳይሉማ መንፈስ ቅዱስ በሁሉ ቦታ ያለ ስለሆነ የሚወርድ የሚወጣ አይደለም:: ልጅነትን፣ ክብርን መንፈስ ቅዱስ ይላቸዋል:: ምክንያቱም እነዚህም ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ስለሆኑ ነው:: ለምሳሌ "ወእምዝ ወደዩ እደዊሆሙ ላዕሌሆሙ:: ከዚህም በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው:: ወነሥኡ መንፈሰ ቅዱሰ" ሲል ልጅነትን ተቀበሉ ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው (የሐዋ. ሥራ ፰፥፲፯):: ልጅነት የሚለው ደግሞ ክብር ነው:: አዳም ዕፀ በለስን በመብላቱ ክብሩን አጣ እየተባለ መነገሩ ልጅነቱን አጣ ማለት ነው::

**፳፫. ጌታ በሰንበት አርፏልና ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ጌታ በሰንበት አረፈ ማለት ሰማይንና ምድርን እንዲሁም በውስጣቸው የሚኖሩ ፍጥረታትን ፈጥሮ ጨረሰ ፈጥሮ ተወ ማለት ነው:: እንጂ ድካም ኖሮበት አረፈ ማለት አይደለም:: መፍጠርን መተውን ያመለክታል (ዘፍ.2፥2 አንድምታ ትርጓሜ)::

**፳፬. በመጀመሪያ ሣርን በኋላ ሰብልን አቤቱ የምድርን ፍሬ ባርክ:: ሣር እና ሰብል መቀዳደማቸው ምስጢሩ ምንድን ነው?**

መልስ፦ ሣር የሚለው በቁሙ ሣርን ነው:: ከፍሬ በፊት መጀመሪያ የሚገኝ ሣር ነውና:: ፍሬ የሌለውን ቡቃያውንም ሣር ብሎታል:: ከቡቃያ ቀጥሎ ሰብል ይገኛል:: ሰብል ያለው የዘረዘረውን እህል ነው:: ከሰብል በኋላ የሚመጣው ደግሞ ፍሬ ነው:: ስለዚህ መጀመሪያ ቡቃያውን ቀጥለህ የዘረዘረውን (ዝርዝሩን) መጨረሻ ላይ ደግሞ ፍሬውን ባርክ ማለት ነው::

**፳፭. ጌታችን የሕይወት ፍሬን ልቀሙ የመድኀኒት ቦርቦርቴንም የራስ ቍርንም ተቀዳጁ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ልቀሙ ካለ ዘንድ ፍሬ አለ:: በትርጓሜ ቋንቋ ፍሬ ግሥ ነው:: ወይም በቅኔ ቋንቋ ፍሬ ሰም ነው:: ሕይወት ወርቅ ነው:: በቅኔ መንገድ ደግሞ ሰም ለወርቅ ማሰሪያ ያተርፍለታል:: ስለዚህ ልቀሙ የሚለውን ሥሩ ወይም አድርጉ ማለት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ መልካም ሥራን ሕይወት፣ ክፉ ሥራን ሞት ይለዋል:: ቅዱስ ያሬድም መጽሐፍ

ቅዱስን መሠረት አድርጎ የሚጽፍ ነውና ከዚህ መልካም ሥራን ሕይወት ብሎታል። "ወናሁ ሤምኩ ቅድመ ገጽከ ዮም ሕይወተ ወሞተ" እንዲል (ዘዳ.30፥15)። ስለዚህ የሕይወት ፍሬን ልቀሙ ማለት መልካም ሥራን ሥሩ ማለት ነው። ቦርቦርቴ ራስን ከጦር ከሰይፍ ለመከላከል የሚያገለግል በራስ የሚጠለቅ ከብረት የሚሠራ እንደ ቆብ ያለ ነው። ያን ያደረገ ሰው ሰይፍ ጦር እንደማያስፈራው ሁሉ እናንተም መልካም ሥራን ተቀዳጁ ማለት ነው። መልካም ሥራን የያዘ ደግሞ ምንንም አይፈራም። እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ደፋር ይሆናል (ሮሜ 8፥35-39)።

፳፰. እግዚአብሔር ሰውን በመውደዱ ሰንበትን ሠራ ይላል። ሰውን በመውደዱ ሲል ለሌሎች ፍጥረታትስ?

መልስ፦ ሰንበት የተፈጠረች በዋናነት ለሰው ልጆች ዕረፍት ትሆን ዘንድ ነው። ምስጢሩ ግን ሰንበት የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ናት። ከምድራውያን ፍጥረታት ደግሞ በመንግሥተ ሰማያት ለዘለዓለም የሚኖር ሰው ብቻ ስለሆነ ሰውን በመውደዱ ሰንበትን ሠራ ተብሏል። እግዚአብሔር በባሕርዩ ሁሉን ፍጥረት ይወዳል። በባሕርዩ ፍቅር ነውና (1ኛ ዮሐ.4፥8)። ሌሎች ፍጥረታት ግን ትንሣኤ የላቸውም። ከመጀመሪያውም የተፈጠሩት ለሰው ጊዜያዊ ሕይወት አገልግሎትን ሰጥተው ያልፉ ዘንድ ነው። ሰውን በመውደዱ ያሰኘው ይህ ነው። ሰውን ይወዳል ማለት ሌሎችን ይጠላል ማለት አይደለም።

፳፱. ሰውን የሚወድ ክርስቶስ ሰንበትን ለዕረፍት ሠራ ይላል። ቅዱስ ያሬድ ሰንበት የሚላት የትኛዋ ሰንበት ናት? ቀዳሚት ሰንበትስ አልፋለች?

መልስ፦ ቅዱስ ያሬድ በዚህ አገባቡ ሰንበት የሚላት ቅዳሜን ነው። አያይዞ እስመ ባቲ አዕረፈ እምኲሉ ግብሩ ይላልና (ዘፍ.2፥3)። ከብሉይ ኪዳን ዐሥሩ ትእዛዛት አልተሻሩም። ከዐሥሩ ትእዛዛት አንዱ ደግሞ ሰንበትን አክብር የሚለው ነው። ይህ ደግሞ በዋናነት የተነገረው ለቅዳሜ ነው። ቅዳሜ አላለፈችም አልተሻረችም። አሁን በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ሐዋርያት በቀኖና እሑድንም እንድናከብር ስለገለጹልን እሑድንም ሰንበተ ክርስቲያን ብለን እናከብራለን። ሁለቱንም እናከብራቸዋለን ማለት ነው።

፴. የዱር እንስሳትና የሰማይ ወፎች እንዲሁም የባሕር ዓሣዎች እርሱን ያመሰግናሉ ይላል። ያመሰግናሉ ሲል ምን ማለቱ ነው?

መልስ፦ እርሱ እግዚአብሔር ራሱ በሚያውቀው እኛ በማናውቀው መንገድ ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎችም ደማውያን ፍጥረታት ያመሰግኑታል ማለት ነው።

፴፩. ማኅበረ በኵር አማኅበሩ አማኅብሮ ይላል። ማኅበረ በኵር የተባሉ እነማን ናቸው?

መልስ፦ በኵር የተባለ ክርስቶስ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ "ፈነዎ ለበኵሩ ውስተ ዓለም" እንዳለ (ዕብ.1፥6)፡፡ ሥጋ ቃልን ተዋሕዶ የአብ የባሕርይ ልጅ ሆኗል፡፡ እርሱ የባሕርይ ልጅ በመሆን ከቀደመ በኋላ እኛ ደግሞ እርሱን በኵር አድርገን የጸጋ ልጅነትን እናገኛለን፡፡ የድንግል ማርያምም ብቸኛ የመጀመሪያ ልጇ ነው፡፡ የአብም ብቸኛ ልጁ ነው፡፡ በሁለቱም በኩል በኵር ቢባል ይገባዋል፡፡ ማኅበረ በኵር ማለት ማኅበረ ክርስቶስ ማለት ነው፡፡ እኒህም በእርሱ አምነው የተጠመቁ ምእመናን ሁሉ ናቸው፡፡

፴፪. ፋሲለደስ ሆይ ስምህን የጠሩ መታሰቢያህን ያደረጉ ኃጥኣን በኪዳንህ ይጸድቃሉ ይላል፡፡ ኃጥኣን በኪዳንህ ይጸድቃሉ ሲል ምን ማለት ነው? ከጸደቀስ ለምን ኃጥእ አለው? ማንም ኃጥእ በቃል ኪዳን ይጸድቃል?

መልስ፦ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል "ኃጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም" ብሏል (ማር.2፥17)፡፡ ይህም ማለት በቀድሞ ሥራቸው ኃጥኣን የነበሩ ሰዎች ትምህርቱን ሰምተው ከኃጢአት ተመልሰው በጽድቅ ሥራ ይኖሩ ዘንድ ጠራኋቸው ማለት ነው፡፡ የጻድቃንን መታሰቢያ ማድረግ ራሱን የቻለ አንድ የጽድቅ ሥራ ነው፡፡ ስለዚህ ኃጥኣን ከኃጢአታቸው ተመልሰው የጻድቃንን መታሰቢያ ቢያደርጉ ይህ ሥራቸው ያጸድቃቸዋል ማለት ነው፡፡ ይህም ጌታ በተናገረው ቃል መሠረት ነው፡፡ "ጻድቅን በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ያገኛል" ብሏልና (ማቴ.10፥41)፡፡ ከጸደቁ ለምን ኃጥእ ተባሉ ለሚለው በቀድሞ ሥራቸው ምክንያት ነው፡፡ ቃል ኪዳን ከጽድቅ መንገዶች አንዱ እንጂ ብቸኛው አይደለም፡፡ ስለዚህ ሰው በቃል ኪዳን ብቻ ይጸድቃል አንልም፡፡ ጽድቅ በማመን፣ ምሥጢራትም በመፈጸም፣ መልካም ሥራን በመሥራት፣ በቃል ኪዳንና በመሳሰለው ይገኛል፡፡ በአንዱ ብቻ ይገኛል ግን አይባልም፡፡ ስለዚህ ሰው ለመዳን ሁሉንም ለመሥራት መጣር አለበት፡፡

፴፫. ፋሲለደስ የት አከባቢ የነበረ ነው?

መልስ፦ መጽሐፈ ገድሉ እንደሚገልጸውና ስንክሳር መስከረም 11 እንደሚገልጸው ፋሲለደስ የሮም የሠራዊት አለቃ የነበረና ነገሥታትንም በአማካሪነት ያገለገለ ታላቅ ሰው ነው፡፡ ስለዚህ ፋሲለደስ ሮም አካባቢ ይኖር የነበረ ሰው ነው፡፡

፴፬. ስለዚህም ቤተክርስቲያን ከከበሩ በዓላት አልቃ በጥበብና በዕውቀት፣ በጸናጽልና በከበሮ በዓልህን ታከብረዋለች፡፡ ከከበሩ በዓላት አልቃ ሲል ምን ለማለት ነው?

መልስ፦ የቅዱሳን በዓላት ሁሉ የከበሩ በዓላት ናቸው፡፡ በስንክሳር እንደተገለጸው ከዓመት እስከ ዓመት የብዙ ቅዱሳን በዓላት ይውላል፡፡ ቢሆንም ግን መታሰቢያቸው ከመነበብ ውጭ ጸላት ተቀርጾላቸው፣ መልክእ ተደርሶላቸው፣ ቤተክርስቲያን ታንጾላቸው የሚከበሩ ጥቂቶች ናቸው፡፡ ፋሲለደስ ከእነዚህ ከጥቂቶች አንዱ ስለሆነ ካልተሠራላቸው አንጻር ከከበሩ በዓላት አልቃ ታከብረዋለች ተብሏል፡፡

**፴፭. የኃጢአት ማስተሥረያ ትሆን ዘንድ ቤተክርስቲያንን በሰማያዊት መቅደስ አምሳል አነጿት ሠሯት ይላል። በሰማይ መቅደስ አለ ወይ?**

መልስ፦ በሰማይ በዚህ በመሬት እንዳለችው ያለች የተለየች መቅደስ ኖራ አይደለም። በሰማይ መቅደስ አለች እያለ የሚገልጻት ጠቅላላ መንግሥተ ሰማያትን ነው። "ወእምዝ ተርኀወ መቅደሱ ለእግዚአብሔር ዘውስተ ሰማይ" እንዲል (ራእ.11፥19)። ከዚህ አያይዞ በሰማይ ታቦት አለች እየተባለ የሚነገረው ስለምእመን ነው። ታቦት የተባለ ምእመን ነው። "ወአስተርአየት ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር እንተ ውስተ መቅደሱ" ሲል ምእመን መንግሥተ ሰማያትን ወርሳ ከብራ ታየች ማለት ነውና (ራእ.11፥19 አንድምታ ትርጓሜ)።

**፴፮. የፈላ እርሳስን ከሙጫ ጋር አድርገው ቢያጠጧችሁ ሲል የፈላ እርሳስ ምንድን ነው?**

መልስ፦ እርሳስ እንደ ብረት ያለ የመዓድን ዓይነት ነው። ብረትን በእሳት አቅልጠው ልዩ ልዩ ቅርጽ እንደሚሰጡት ሁሉ እርሳስም ሲቀልጥ ወደፈሳሽነት የሚለወጥ የፈላ ይሆናል። ይህንን የጠጣ ሰው ሰውነቱ ተሰነጣጥቆ ይሞታል። የፈላ እርሳስን ቢያጠጧችሁ ያለው ይህንን ነው።

**፴፯. ዛንጅር ምንድን ነው?**

መልስ፦ ዛንጅር በቀድሞው ዘመን ወንጀለኞች ይታሰሩበት የነበረ የብረት ሰንሰለት ነው።

**፴፰. ቤተ ክርስቲያን የኃጢአት ማስተሥረያ እንዴት ልትሆን ትችላለች? በካህናት ጸሎት አይደለም ወይ ኃጢአት የሚሠረይ?**

መልስ፦ የኃጢአት ማስተሥረያ መባሏ ንስሓ ገብተን ሥጋውን ደሙን የምንቀበልባት በመሆኗ ነው። ሰው ምንም እንኳ ንስሓ ቢገባ ከጥምቀት በኋላ የሠራው ኃጢአት የሚሠረየው ሥጋውን ደሙን በመቀበል ነው። ኃጢአት ዘእምድኅረ ጥምቀት ይሠረይ በቍርባን እንዲል። ስለዚህ ኃጢአት በካህናት ጸሎትም፣ ቤተክርስቲያን ሄዶ በመቍረብም ይሠረያል።

**፴፱. ኢቀደሶኑ ደሙ ክቡር ለዕፀ መስቀሉ ወበእንተዝ ንሕነ ናመልኮ። የክርስቶስ ደም የፈሰሰበት ነውና መስቀልን እናመልከዋለን ይላል። እናመልከዋለን ሲል ምን ማለቱ ይሆን?**

መልስ፦ አምለከ የሚለው የግእዝ ቃል አመለከ፣አከበረ ተብሎ ይተረጎማል። ወበእንተዝ ንሕነ ናመልኮ ሲል ናመልኮ ምስጢሩ እናከብረዋለን ማለት ነው። በአጭሩ መስቀልን እናመልከዋለን ማለት የጸጋ ክብርን እናከብረዋለን ማለት ነው።

**፵. መስቀል ሆይ ስለ ቅዱስ ስምህ ርዳን አድነንም ይላል። ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ መስቀል፣ ሰንበት ሰሚ ወይም ተናጋሪ አይደሉም። ነገር ግን በመስቀልም በሰንበትም እግዚአብሔር ታላላቅ ሥራዎችን ስለሠራባቸው የተከበሩ ናቸው። በቅዳሴ ሰአሊ ለነ ሰንበት-ሰንበት ሆይ ለምኚልን ሲል ይገኛል። አሁን ሰንበት የምትሰማ ሆና አይደለም። በሰንበት ታላላቅ ሥራን የሠራህ አምላክ ሆይ በሰንበት የሠራኸውን ሥራ አስበህ ይቅር በለን ማለት ነው። ይህን የመሰለ በመጽሐፍ ቅዱስም አለ። ዕለት መናገር የማትችል ቢሆንም እንደምትናገር አስመስሎ ይናገራል። "ዕለት ለዕለት ትጐሥዕ ነቢበ፤ ወሌሊት ለሌሊት ታየድዕ ጥበበ" እንዲል (መዝ.19፥2)። መስቀል ሆይ ርዳን የሚለውም ጌታ ሆይ በመስቀል ሰቅለህ ያዳንከንን ማዳን አስበህ ርዳን ማለት ነው። በማድረጊያው አድራጊውን መግለጽ ነው።

፵፩. ደብተራ ፍጽምት እንተ ኢገብራ እደ ሰብእ። በደሙ ክቡር በዕፀ መስቀሉ ተቀደሰት ቤተ ክርስትያን ምስጋዶሙ ለመሃይምናን። እንተ ተሐንፀት በእደ ካህናት ወተቀደሰት በአፈ ጳጳሳት እምነ ጽዮን ቅድስት እንተ የዐውዳ ስብሐት ይላል። እንተ ኢገብራ እደ ሰብእ እና እንተ ተሐንፀት በእደ ካህናት እንዴት ነው የሚተረጎምው? ወተቀደሰት በአፈ ጳጳሳት ሲልና በደሙ ክቡር በዕፀ መስቀሉ ተቀደሰት ሲል እንዴት ነው?

መልስ፦ እንተ ኢገብራ እደ ሰብእ (ሰው ያልሠራት) መባሉ ቤተክርስቲያንን የመሠረታት ክርስቶስ መሆኑን ያመለክታል (ኤፌ.2፥20)። መሥራችንና ባለቤትን ሲያመለክት ሰው ያልሠራት ተብሏል። በካህናት እጅ የተሠራች ማለቱ ደግሞ ምእመናን በካህናት ተጠምቀው ቤተክርስቲያን ስለተባሉ ማጥመቃቸውን፣ ማስተማራቸውን ሲያመለክት ነው። ቤተክርስቲያን የተሠራች የተቀደሰች በክርስቶስ ደምና በመስቀሉ ነው። በአፈ ጳጳሳት ተቀደሰት ሲል ደግሞ በጳጳሳት የተመሰገነች ማለት ነው።

፵፪. ንግሥት ዕሌኒ ዕንባቆም ነቢይ ሥራውን ያደነቀውን መስቀልን ፈለገች ይላል። ስለ መስቀል ዕንባቆም ተናግሮ ነበር?

መልስ፦ አዎ ተናግሯል። "በማእከለ ክልኤ እንስሳ ርኢኩከ ከመ ከመ ይቀርብ ዓመቲሁ አአምረከ ወከመ ከመ ይበጽሕ ጊዜሁ እሌብወከ" ብሎ ተናግሯል (ትን. ዕን.3፥2)። በሁለት እንስሳት መካከል አየውህ የሚለው በፈያታዊ ዘየማንና በፈያታዊ ዘጸጋም መካከል በመስቀል ላይ ተሰቅለህ አየውህ ማለት ነው። ሰው የሚናገር እንስሳ (እንስሳ ነባቢ) ይባላልና። "ወኵሉ እንስሳ ነባቢ" እንዲል (ሃይ.አበ.110፥23)። በማድረጊያ አድራጊን በአድራጊ ማድረጊያን መግለጽ መጽሐፋዊ ልማድ ነውና በሁለት ወንበዴዎች መካከል በመስቀል ተሰቅሎ ያየው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህንን ነቢዩ ዕንባቆም ቀድሞ በትንቢት አይቶት ጊዜው ሳይደርስ እንደደረሰ እንደደረሰ አይቶ አድንቋል።

፵፫. እንደ ዮሐንስ ቀሲስ አፉን እስኪስመው ድረስ ለንዑድ ኤዎስጣቴዎስ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ሞገስ ተሰጠው ይላል። ምን ለማለት ነው? የትኛው ቀሲስ ዮሐንስ ነው?

መልስ፦ ቀሲስ ዮሐንስ የተባለ ወንጌላዊው ዮሐንስ ነው። ምንም እንኳ ሐዋርያት በፓትርያርክ ደረጃ የነበሩ ቢሆንም ፓትርያርክ የበታቾቹን ሥራ ሁሉ መሥራት ስለሚችል ወይም ደግሞ በቀደመ መዓርጉ ቀሲስ ብሏል። እንዲሁም ስለትሕትና ቀሲስ ተብሏል። ይህን የመሰለ ደግሞ 2ኛ ዮሐ.1፥1 ላይ ተገልጿል። "እምነ ቀሲስ ለኅሪት ወለእግዝእት ወለደቂቃ ለእንተ አነ አፈቅራ በጽድቅ..." እንዲል። የመልክአ ኢየሱስ ደራሲም "ሰላም ለአፉከ ለዮሐንስ ዘሰአሞ ንጽሐ ኅሊናሁ ወልቡ ለዐይነ ፍትወትከ ሶበ አደሞ ኢየሱስ ክርስቶስ መፍቀሬ የውሃት ወተቀይሞ..." ብሏል። አፍን መሳም የፍቅር ምልክት እንደሆነ ደግሞ "ይስዕመኒ በስዕመተ አፉሁ" ተብሎ ተገልጿል (መሓ. መሓ.1፥2)። እናት ሕፃን ልጇን አፉን ግንባሩን መሳሟ ጽንዐ ፍቅሯን ይገልጻል። እንደዚሁ ኢየሱስ ክርስቶስም እንደ እናት እንደ አባት የሚወደው ልጁን ይስመዋልና ኤዎስጣቴዎስን እንደ ዮሐንስ ሳመው ተብሏል።

፵፬. የመስቀል ችንካሮችን ባየች ጊዜ ዕሌኒ በአንደበቷ እልል አለች በእግሯም አሸበሸበች ይላል። በእግሯም አሸበሸበች ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ በእግር ማሸብሸብ የሚለው የሀገራችን ሊቃውንት እንደሚያስረግጡት ያለ ነው። እጅን በማጨብጨብ፣ እግርን በማስረገጥ፣ በአንደበት እልል በማለት እጅን፣ እግርን፣ አንደበትን ለፈጠረ እግዚአብሔር የአምልኮ ምስጋናን ማመስገን ነው።

፵፭. ማርያም ሆይ የወልድን መስቀል እየለበስሽ (ለብሰሽ) ፈጽሞ ደስ ይበልሽ ሲል ምን ማለቱ ነው?

መልስ፦ መስቀል እንደሸማ የሚለብሱት፣ እንደ ሰርመዴ የሚከናነቡት፣ እንደ መጎናጸፊያ የሚጎናጸፉት ሆኖ አይደለም። በመስቀሉ የተፈጸመውን ድኅነት እያሰብሽ ደስ ይበልሽ ማለት ነው። ቅዱሳን የእግዚአብሔርን ማዳን እያሰቡ ደስ እያላቸው ይኖራሉና።

፵፮. ዕሌኒ መልአኩን ስለ ክርስቶስ መስቀል ንገረኝ አለችው ይላል። ማንኛው መልአክ ነው?

መልስ፦ ከዚህ የመልአኩ ስም አልተገለጸም። ድርሳነ መስቀል ዘመጋቢት ላይ ቅዱስ ገብርኤል እንደሆነ ተገልጿል።

፵፯. ስሑታንን ይመልስ ዘንድ በእንጨት መስቀል ላይ ኃጥአንን ታገሠ ይላል። ኃጥአንን ታገሠ ሲል ምን ለማለት ነው?

መልስ፦ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ ኃጥኣን አይሁድ ይዘባበቱበት ይሰድቡት ነበር። በጥፊ እየመቱም ክርስቶስ ሆይ የመታህ ማን ነው? እስኪ ንገረን እያሉ ያፌዙበት ነበር። አምላክ ከሆንክ እስኪ ከመስቀል ውረድ ሲሉት ሁሉ ታግሦ ዝም አላቸው። ቅዱሰ ያሬድ ተዐገሠ ኃጥኣነ ያለው ይህንን ነው። ቅዱስ

ዮሐንስ አፈወርቅም ኦ ትዕግሥት ዘመጠነዝ ትዕግሥት ያለው ይህንኑ ነው (ቅዳሴ ዮሐንስ አፈወርቅ)።

፵፰. አይሁድስ ኢያእመሩ በቅንዐቶሙ መድኀኒቶሙ ሰቀሉ ይላል። አላወቁም እንዴ?

መልስ፦ አዎ አይሁድ አላወቁም። ቅዱስ ጳውሎስም ይህንን ሲገልጽ "ወሶበሰኬ አእምሩ እምኢሰቀልዎ ለእግዚአ ስብሐት። አውቀውስ ቢሆን የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር" ብሏል (1ኛ ቆሮ.2፥8)። ላለማወቃቸው ምክንያቶቹ ግን ራሳቸው ናቸው። ምቀኝነታቸው፣ ቅንዐታቸው፣ ጥላቻቸው መድኀኒታቸውን ላለማወቅ መንሥኤ ሆናቸው።

፵፱. መስቀል አብርሃም ለመሠዊያ የፈለጠው፣ የማይነቅዝ እንጨት ነው ሲል ምን ማለት ነው? የማይነቅዝ እንጨት አለ ወይ?

መልስ፦ የማይነቅዙ የእንጨት ዓይነቶች አሉ። ለምሳሌ በትርጓሜ በብዛት የተገለጸው ሸምሸርሰጢን የሚባለው እንጨት አይነቅዝም። በብሉይ ኪዳን ንዋየ ቅድሳት ሲሠሩ ከሸምሸርሰጢን ይዘጋጁ ነበር (ዘፀ.25፥2-26 አንድምታ ትርጓሜ)። ከዚያ ተቀድሰው ለደብተራ ኦሪት አገልግሎት ይውሉ ነበር። በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት በብዛት የሚውል መስቀል በመሆኑ በማይነቅዝ እንጨት ተመስሏል። አብርሃም ለመሠዊያ የፈለጠው እንጨት የተባለው ይስሐቅን ለመሠዋት ወደ ተራራ ከወሰደው በኋላ ያዘጋጀው እንጨት ነው። በዚያ እንጨት ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ የመጣውን በግ አርዶ ይስሐቅን አድኖታል። ይስሐቅ የሰው ልጆች ሁሉ ምሳሌ ነው። በጉ የክርስቶስ ምሳሌ፣ ዕፀ ሳቤቅ የድንግል ማርያም ምሳሌ ነው። በጉ የታረደበት ያ እንጨት ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ምሳሌ ነው (ዘፍ.22፥13 አንድምታ ትርጓሜ)።

፶. መስቀል ዓለምን ያዳነ ነው ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ክርስቶስ ዓለምን ያዳነው በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ነው። መስቀል ዓለምን ያዳነ ነው ሲልም ጌታ በእርሱ ሆኖ እንዳዳነበት ለመግለጽ ነው። በማድረጊያ አድራጊን፣ በአድራጊ ማድረጊያን መግለጽ ልማደ መጻሕፍት ነው። በባሕርዩ የሚያድን እግዚአብሔር ብቻ ነው (1ኛ ሳሙ.14፥23)። በጸጋ ደግሞ የማዳንን ኀይል ሰጥቷቸው የሚያድኑ መላእክት፣ ሰዎች፣ ጊዜያት፣ መካናት፣ ንዋያት...የመሳሰሉት አሉና ነው (ኤፌ.2፥16፤ 1ኛ ሳሙ.14፥48)።

፶፩. መስቀል አጋንንትን የሚያባርር ነው ሲል ምን ማለት ነው? ሁሉም ክርስቲያን መስቀል አለው። ታዲያ ለምን አንዳንዱ ሰው አጋንንት ያደረበት ሆነ?

መልስ፦ መስቀል አጋንንትን የማባረር ሥልጣን አለው። አንዳንድ ጊዜ ግን በመስቀልም የማይለቅ ጋኔን ሊኖር ይችላል። በወንጌል እንደተጠቀሰው ሐዋርያትም ሁሉን በሽታ

ሲፈውሱ አንዱን ግን መፈወስ አቅቷቸው ነበር። ክርስቶስም ያ ጋኔን የሚወጣ በጾምና በጸሎት እንደሆነ ነግሯቸዋል (ማቴ.17፥21)። በጠቅላላው የፍጡራን የማዳን ኀይል የጸጋ ስለሆነ ወሰን ስላለበት ነው። በተጨማሪም አንዳንድ ጊዜ የሰው ልጆች ሲታበዩ ትሕትናን እስኪማሩ በእግዚአብሔር ትእዛዝ አጋንንት የማይወጡበት ጊዜ አለ። በመጽሐፈ መነኮሳት ይህን የሚያረጋግጥልን ታሪክ አለ። "በእንተ ምንትኑ ጊዜ ይትመየጡ ሰይጣናት በስመ ክርስቶስ ወትእምርተ መስቀል ወጊዜ ኢይትመየጡ። ሰይጣናት የጌታን ስም ስንጠራባቸው መስቀል ስናማትብባቸው አንዳንድ ጊዜ ድል ተነሥተው የሚመለሱ አንዳንድ ጊዜ ድል ተነሥተው የማይመለሱ ስለምንድን ነው" ብሎ ከጠየቀ በኂላ እኛ ልንጠቀምበት ሲሆን እንደሚችል ገልጿል (ፊልክስዩስ ተስእሎ 29)።

## ፶፪. ይህንን ኀላፊ ዓለም የናቃችሁት ነጻ አውጭዎች ናችሁ ይላል። ነጻ አውጭዎች ማለት ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ቅዱሳን ነጻ አውጪዎች ይባላሉ። በመጀመሪያ ራሳቸውን ከኃጢአት ነጻ ስላወጡና በሕገ እግዚአብሔር ጸንተው ስለኖሩ ነው። "ነገር ግን ነጻ የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸናበት፥ ሥራንም የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነው፥ በሥራው የተባረከ ይሆናል" እንዲል (ያዕ.1፥25)። ሁለተኛ አስተምረው ኃጥኣንን ከኃጢአት፣ ከሓድያንን ከክሕደት ነጻ አውጥተው አማኝ ጻድቅ ያድርጋሉና ነው (ማቴ.10፥8)።

## ፶፫. መስቀል በሰማይ ነገሠ ሲል እንዴት ነው?

መልስ፦ ሰማይ የተባሉ መላእክት ናቸው። መጻሕፍት በማደሪያ ኀዳሪን በኀዳሪ ማደሪያን መጥራት ልማዳቸው ነውና (ዘዳ.32፥1)። መስቀል በመላእክት ነገሠ ማለት ነው። ይህም የነገሠ እንዲከበር መስቀል በመላእክት ዘንድም ተከበረ ማለት ነው። እንዲሁም በቁሙ የነገሠ ከሁሉ በላይ እንዲታይ ትእምርተ መስቀልም ለንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ኒቁስጣኑ ኒቁስጣጣኑ ብሎ በሰማይ በከዋክብት መካከል ታይቷልና ነው።

## ፶፬. መስቀል በመንገድ ለዕው*ራን መሪ ነው ሲል ምን ማለት ነው? መሪያችን ክርስቶስ አይደለም ወይ?

መልስ፦ የመስቀል፣ የቅዱሳን ሰዎች፣ የመላእክት መሪነት የጸጋ መሪነት ነው። በባሕርዩ ፍጥረቱን ሁሉ የሚጠብቅ፣ የሚመግብና የሚመራ እግዚአብሔር ነው። ለፍጡራን ደግሞ በጸጋ ሰጥቷቸዋል። መስቀል መሪ ነው ሲባል በተሰጠው ጸጋ የሚመራ ስለሆነ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ መሪያችን ነው ሲል ደግሞ አምላክ እንደመሆኑ በባሕርዩ መሪ መሆኑን ይገልጻል። ይህ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አገላለጽ ነው። በባሕርዩ ብርሃን ክርስቶስ ስለሆነ "እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ" ብሏል (ዮሐ.8፥12)። በጸጋ ሐዋርያትም

ብርሃን ስለሆኑ "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ" ተብለዋል (ማቴ.5፥14)። መስቀል የዕው*ራን መሪ የሚለውም በዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል መሠረት የተነገረ ነው።

**፶፭. የተተውኩ የተጣልኩ ሆኜ ሳለ በመስቀልህ አበራህልኝ እያለች ቤተክርስቲያን [ኢየሱስን] ታመሰግነዋለች ይላል። የትኛዋ ቤተክርርስቲያን ናት?**

መልስ፦ ይህ ስለምእመናን የተነገረ ነው። ምእመናን ልጅነትን አግኝተው የክርስቶስ ማደሪያ ስለሆኑ ቤተክርስቲያን ይባላሉ ይህም ቤተክርስቶስ ማለት ነው (ዮሐ.14፥23፤ 1ኛ ቆሮ.3፥16)። ምእመናን ለ5500 ዘመን ያህል የተተዉ በሲኦል የተጣሉ ነበሩ። በኋላ ግን ክርስቶስ መጥቶ አድኗቸዋልና አመስግነውታል። በሲኦል የነበሩ ነፍሳት በዕለተ ዓርብ ጌታ በአፀደ ነፍስ ሄዶ ቀኝ እጁን አሳይቷቸው ያም ጥምቀት ሆኗቸው ድነዋልና። "የማነ እዴየ መጠውክዎሙ ወኮነቶሙ ጥምቀተ" እንዲል (ሃይ.አበ.3፥13)።

**፶፮. ዕፅ ሳቤቅ ማለት የይቅርታ እንጨት ማለት ነው ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ የይቅርታ እንጨት የተባለ መስቀል ነው። ክርስቶስ በላዩ ተሰቅሎ ለሰው ልጆች ሁሉ ይቅርታን የሰጠበት ነውና (ሉቃ.23፥34)። ለዚህ ለመስቀል ዕፀ ሳቤቅ ምሳሌው በመሆኑ ዕፀ ሳቤቅ ማለት የይቅርታ እንጨት ማለት ነው ተብሏል። ቤዛ ይስሐቅ በግዕ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ መጥቶ ይስሐቅ እንዳነበተ። ቤዛ ኵሉ እጓለ እመሕያው ክርስቶስ ደግሞ በመስቀል ተሰቅሎ ሰው ሁሉ ድኖበታልና ነው።

**፶፯. ምድር እንዳትነዋወጥ አደረገ ሲል ምን ማለት ነው? የመሬት መደርመስ፣ የገደል መናድና የመሳሰሉት እንዴት ይታያሉ?**

መልስ፦ ጥቂቱን አልቦ፣ ብዙውን ሁሉ ማለት መጽሐፋዊ ልማድ ነው። መሬት በጠቅላላዋ እንዳትነዋወጥ አደረጋት ማለት ነው እንጂ ከእርሷ በጣም ጥቂት ክፍሎች አይደረመሱም አይነዋወጡም ለማለት አይደለም። መታረስ የምትችል እንደመሆኗ፣ የተሠራችም ለሰው ልጅ እንደመሆኗ ሰው ራሱ ፈልጎ ተራራውን ሊንድ፣ ሸለቆውን ሊሞላ ይችላል። ይህን በማድረጉ ግን ምድርን መላዋን እንድትነዋወጥ አያደርጋትም። እግዚአብሔርም ለሰው ተግሣጽ ይሆን ዘንድ አንዲት የተወሰነች ቦታን ሊያነዋውጣት ይችላል።

**፶፰. ጳውሎስ ድንግል ማርያምን የነጻነት ድንኳን ብሏታል። ለምን የነጻነት ድንኳን አላት?**

መልስ፦ በደብተራ ኦሪት እግዚአብሔር በረድኤት አድሮ እስራኤላውያንን ከሥጋ መቅሠፍት፣ ከመከራ ሥጋ ያድናቸው ነበር (ዘፀ.40፥34)። ያች ድንኳን ግን ጊዜያዊ ነበረች። በውስጧ የሚኖረው ታቦትም አንዳንድ ጊዜ በጠላት ሲማረክ ይታይ ነበር (1ኛ ሳሙ.4፥11)። ድንግል ማርያም ዘለዓለማዊ ድንኳን ናት። ይህ ብቻ ሳይሆን ከእርሷ

የተወለደው ክርስቶስም ለሥጋም ለነፍስም ነጻነትን የሰጠና የሚሰጥ በመሆኑ እርሷ የነጻነት ድንኳን ትባላለች።

**፶፱. ስለ ድንግል ማርያም ሲናገር በውስጧ ሰው ተወለደ ይላል። ለምን ሰው አለ? አምላክ ወሰብእ ለምን አላለም?**

መልስ፦ ክርስቶስ ሰው እንደመሆኑ በወንጌልም ብዙ ቦታ ላይ ራሱን የሰው ልጅ እያለ ገልጿል። አምላክ እንደመሆኑ ደግሞ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ እያለ ገልጿል። መጻሕፍት አንዳንድ ጊዜ የሰው ልጅ፣ አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ልጅ እያሉ ቢገልጹትም ተዋሕዶውን በመዘንጋት ሳይሆን ተዓቅቦን ለመግለጽ ነው። ተዋሕዶው በውላጤ፣ በቡዓዴ፣ በቱሳሔ፣ በፍልጠት፣ በሚጠት፣ በኅድረት እና በመሳሰለው አይደለምና። ተዋሕዶው በተዓቅቦ ነው። ሰው ሲባል አምላክነቱንም በመዘንጋት አይደለም። እግዚአብሔር ሲባል ሰውነቱን በመዘንጋት አይደለም። በተዋሕዶ ፍጹም መገነዛዘብ ስላለ አምላክም ሰውም ማለት ነው እንጂ። ለዚያ ነው መምህረ ዓለም ቅዱስ ቄርሎስ "ወመጻሕፍትሰ ቦ ዘይቤላ በእንተ መለኮቱ ወቦ ዘይቤላ በእንተ ትስብእቱ እንዘ ውእቱ ከመ አምላክ ወሰብእ። ወቦ ዘይቤላ በእንተ መለኮቱ ወትስብእቱ ኅቡረ" ያለው (ሃይ.አበ.74፥37)።

**፷. ቤተክርስቲያን ጴጥሮስንና ጳውሎስን አይታ ልጅ ወንድሜ ወደ አትክልት ቦታ ወረደ አለች። ልጅ ወንድሜ ያለችው ማንን ነው?**

መልስ፦ ቤተክርስቲያን ልጅ ወንድሜ እያለች የምትገልጸው ጌታችን መድኅኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው። ያረጁ ወላጆች በልጆቻቸው እንደሚረዱ፣ ወንድም መከታ እንደሆነ ሁሉ ክርስቶስም ለቤተክርስቲያን ረዳቷ መከታዋ ነውና ልጅ ወንድሜ ትለዋለች (መሓ.መሓ.1፥14)።

**፷፩. ቤተክርስቲያን አሳዳጅ ሲሰደድ ገፊ ሲገፋ ድንቅ ነገርን አይታ ምንኛ ታደንቃለች ሲል ምን ለማለት ነው?**

መልስ፦ አሳዳጅ የነበረው ጳውሎስ በኋላ በክርስቶስ አምኖ በክፉዎች ሲሰደድ፣ ክርስቲያኖች ከዋሉበት አላሳድር ካደሩበት አላውል ብሎ ይገፋቸው የነበረው ጳውሎስ በኋላ በክፉዎች ሲገፋ ቤተክርስቲያን ታደንቃለች ማለት ነው። አሳዳጅ የነበረ ሲሰደድ፣ ገፊ የነበረ ሲገፋ ያስደንቃልና።

**፷፪. ሦስት ዕፀ ሕይወትን በምድር ላይ የተከለ የመላእክት ክብራቸው ክርስቶስ ነው ይላል። ሦስቱ ዕፀ ሕይወት እነማን ናቸው?**

መልስ፦ ሦስቱ ዕፀ ሕይወት የተባሉ ምድር በተፈጠረች ጊዜ በገነት የነበሩት ሦስቱ ዕፀዋት ናቸው። እነዚህም አንደኛው አዳም እንዳይበላው የታዘዘው ዕፀ በለስ፣ ሁለተኛው

ሺ ዓመት ከሆነው በኋላ በልቶት ታድሶ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገባበት የነበረው ዕፀ ሕይወት፣ ሦስተኛው አዳም በገነት ሳለ ይበላው ዘንድ የተፈቀደለት ሌላው ዕፅ ነው:: ዕፀ በለስ ዕፀ ሕይወት የተባለበት ምክንያት ባይበሉት በጎውን የሚያሳውቅ በመሆኑ ነው:: በምሥጢር ሊቃውንት ትንሣኤን፣ ሥጋውን ደሙን፣ ፍቅርን ዕፀ ሕይወት ብለዋቸዋል (ውዳሴ ማርያም ዘነሙስ ትርጓሜ):: መተርጉማን ደግሞ ጥምቀትን፣ ሥጋውን ደሙን፣ ንስሓን ዕፀ ሕይወት ይሏቸዋል:: እነዚህ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት ያስገባሉና::

፷፫. ሁለት ጡቶቿ የተባሉ የቤተክርስቲያን ሁለቱ ሕጎቿ ናቸው ሲል እነማን ናቸው?

መልስ፦ የቤተክርስቲያን ሁለቱ ሕጎቿ የተባሉ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን ናቸው::

፷፬. የቅዱሳን መዓዛቸው በቆላ እንዳለ እንደ ሱፍ አበባ ነው ሲል ምን ማለት ነው? የሱፍ አበባ ለምን ተመረጠ?

መልስ፦ የሱፍ አበባ ዙሪያውን እሾኻም ነው:: በእሾህ መካከል እሾህ የሌለበት የሚያምር አበባ አለ:: ቅዱሳንም በኃጥኣን መካከል የሚኖሩ ጻድቃን በመሆናቸው በሱፍ አበባ ተመስለዋል:: የሱፍ አበባ ሲያዩት ደስ እንደሚያሰኝ የቅዱሳን ሥራቸውም ደስ ያሰኛል ማለት ነው::

፷፭. የሽመላ ድምፅ በምድራችን ተሰማ ሲል ምን ማለት ነው? የሰው ኃይሉ እንደ ሣር ደካማ ነው ሲልስ ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ሽመላ አፉ ረዘም ያለ የወፍ ዓይነት ነው:: ሽመላ በብዛት ለሰው የሚታየው በዘመነ መጸው (ጥቢ) ክረምት ካለፈ በኋላ ነው:: የክረምት የማለፉ ምልክት ነው:: ቅዱስ ያሬድ የተፈጥሮን ሁኔታ እየገለጸ ለምሳሌ የአበቦችን ማበብ፣ የአዝማራውን መድረስ፣ የሽመላን ድምፅ፣ የሮማንን ማፍራት፣ የወይንን ማበብና የመሳሰሉትን በመጥቀስ የዚህ ሁሉ ባለቤት የሆነውን እግዚአብሔርን አመስግኗል:: ይህን የመሰለ አቀራረብ በመጽሐፍ ቅዱስም አለ (መሓ. መሓ.2፥11-13):: የሰው ኀይሉ እንደሣር ደካማ ነው:: ሣር ከብቶች የሚግጡት፣ በቀላሉ የሚበጠስ፣ ዕድሜው አጭር እንደሆነ ሁሉ ሰውም ደካማ ነው ማለት ነው::

፷፮. ሁለቱ ጡቶቿ መንታነት እንዳላቸው እንደ ፌቆ ግልገሎች ናቸው ሲል ፌቆ ምን ዓይነት እንስሳ ናት?

መልስ፦ ፌቆ ፍየልን የምትመስል በጣም ፈጣን የዱር እንስሳ ናት::

፷፯. ሮማኖች አፈሩ ሲል ሮማን ምንድን ነው?

መልስ፦ ሮማን ውስጡ ቀያይ ፍሬዎችን የያዘ ላዩ ብርቱካንን ወይም ሽንኩርትን የሚመስል የአትክልት ዓይነት ነው።

፰፰. "በጊዜው የተደሰተ ያዝናል። በጊዜው ያዘነ ይደሰታል። በጊዜው ባዕለ ጸጋ የሆነ ድኻ ይሆናል። በጊዜው ድኻ የሆነ ባዕለ ጸጋ ይሆናል። የዱር አበባም በጊዜው ያልፋል። የማያልፍ የለም" ሲል ምን ለማለት ነው?

መልስ፦ በጊዜው ያዘነ ይደሰታል የተባለ ስለጽድቅ ብለው ኀዘን የሚደርስባቸው ሰዎች በኋላ በምጽአት የአባቴ ቡሩካን ወደእኔ ኑ ተብለው ደስ ይላቸዋል ማለት ነው። "የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው መጽናናትን ያገኛሉና" እንዲል (ማቴ.5፥4)። በጊዜው የተደሰተ ያዝናል የተባለ ደግሞ በክፋት የተደሰተ ሰው በሞጽአት ጊዜ እናንተ ርጉማን ከእኔ ሒዱ ሲባል ያዝናል ማለት ነው። "ወእለኒ ይበክዩ ከመ ዘኢበከዩ ወእለኒ ይትፌሥሑ ከመ ዘኢተፈሥሑ ወእለኒ ተደለዉ ከመ ዘኢተደለዉ ወእለኒ ይሣየጡ ከመ ዘኢተሣየጡ ወእለኒ ይመልኩ ከመ ዘኢመለኩ። ወእለኒ ይበልዑ ከመ ዘኢበልዑ ወእለኒ ይሰትዩ ከመ ዘኢሰትዩ እስመ ኵሉ ተድላ ዝ ዓለም የኀልፍ" እንዲል (1ኛ ቆሮ.7፥30-31)። በክፋት ባዕለ ጸጋ የነበረው መንግሥተ ሰማያትን አጥቶ ድኻ ይሆናል። በጽድቅ ምክንያት ድኻ የነበረው መንግሥተ ሰማያትን አግኝቶ ባዕለ ጸጋ ይሆናል ማለት ነው። ባዕለ ጸጋ የነበረው በሞት ሁሉን ያጣል። መልካም በመሥራቱ ምክንያት ድኻ የነበረው በሞት ገነትን አግኝቶ ባዕለ ጸጋ ይሆናል።

፰፱. ድንግል ማርያም ሐዳስዩ ጣዕዋ መባሏ ምሳሌነቱ እንዴት ነው?

መልስ፦ ረኀበ ነፍሳችንን የሚያስወግድ የሰባ ፍሪዳ ክርስቶስን ስለወለደችልን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሐዳስዩ ጣዕዋ ትባላለች።

፱. የአባቶቻችን የቅዱሳን አምላካቸው ክርስቶስ ዐይን ያላየውን ጆሮ ያልሰማውን (መንግሥተ ሰማይን) ይሰጣቸዋል ይላል። ዮሐንስ ደግሞ በራእዩ ራእ.21፥1 ወእምዝ ርኢኩ ሰማየ ሐዲሰ ወምድረ ሐዳሰ ይላል። አይቃረንም?

መልስ፦ አይቃረንም። ዮሐንስ አየሁ ማለቱ በራእይ ነው። የራእይ እይታ ከኩነት እይታ የተለየ ነው። ስለመንግሥተ ሰማያት ሁላችንም ሰምተናል። ታዲያ ለምንድን ነው ጆሮ ያልሰማት መባሉ ከተባለ መኖሯን ሰማን እንጂ መንግሥተ ሰማያት ምን እንደምትመስል የሚገልጽ ዜና አልሰማንምና ነው። የሰማነው ቢኖርንኳ ራእይ እንጂ አማናዊ አይደለምና። ራእይ ለተመልካቹ በሚገባ መንገድ የተመልካቹን አቅም መሠረት ባደረገ ነገር ይነገራል ይታያልና። አሁን ላይ መንግሥተ ሰማያትን እንደሆነችው አድርጎ መግለጽ የሚችል አንደበት፣ መስማት የሚችል ጆሮ የለንም።

፱፩. በድንጋይ መወገርን በታገሠ በእስጢፋኖስ በዓል ዛሬ ደስታ ሆነ ይላል። በተወገረበት በዓል መከራውን ማሰብ ሲገባ እንዴት ደስታ ሆነ አለ?

መልስ፦ ሰማዕታት መከራ ተቀብለው ሰማዕት የሆኑባት ዕለት የድል ቀናቸው ናት፡፡ ከዚህ ዓለም ድካም አርፈው ወደ መልካም ዓለም የተሸጋገሩበት ቀን ነውና፡፡ ሞቶሙሰ ለጻድቃን ዕረፍቶሙ ይእቲ እንዲል፡፡ መከራቸው የደስታ ምንጭ እንደሆናቸው በማሰብ መከራ የተቀበሉበትን ቀን በደስታ እናከብረዋለን፡፡

**፸፪. ሚልክያስኒ ይቤ እግዚአብሔርሰ ግብተ ይመጽእ ወየኀድር ውስተ ጽርሑ ሲል ለምን ግብተ አለ? ትንቢት በነቢያት አስቀጥሮ አይደል በድንግል ማርያም ያደረው?**

መልስ፦ እውነት ነው የክርስቶስ መምጣት በትንቢተ ነቢያት ተነግሮ፣ ምሳሌ ተመስሎለት ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን አምላክ ሰው ሲሆን ያወቀ አልነበረም፡፡ እንኳንስ ሰው መላእክትም አላወቁም ነበርና በድንገት ተብሏል፡፡ "ወኢያእመረ መኑሂ እምእለ ሀለዉ ውስተ አርያም ምሥጢረ ምጽአቱ" እንዲል (ሃይ.አበ.60፥11)፡፡

**፸፫. ድንግል ማርያምን ደመና ቀሊል ሲላት ምሳሌነቱ እንዴት ነው?**

መልስ፦ ቀሊል ማለት ፈጣን ማለት ነው፡፡ አቅለሉ ክነፊሆሙ ብሎ አፋጠነ እንዲል (ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ)፡፡ ፈጣን ደመና ማለት ነው፡፡ ፈጣን መባሏ ለበጎ ምግባር ፈጣን ናትና፡፡ ይህም ለሰው ሁሉ በመራራቷና ከዚህም ባሻገር ለውሻ ሳይቀር የምትራራ በመሆኗ ነው፡፡

**፸፬. የዚህን ዓለም መከራ ደስታ ያደረጉ አባቶቻችን ንዑዳን ክቡራን ናቸው ይላል፡፡ እንዴት ነው የዚህን ዓለም መከራ ደስታ ማድረግ የሚቻለው?**

መልስ፦ የዚህን ዓለም መከራ ደስታ ማድረግ የሚቻለው ተድላ መንግሥተ ሰማያትን በማሰብ ነው፡፡ ቅዱሳን ለሰማዕትነት ይሽቀዳደሙ የነበረው የክርስቶስን ፍቅር በማሰብና የመንግሥተ ሰማያትን ደስታ በማሰብ ነበር፡፡

**፸፭. ሠርፀ ጴጥሮስ ማን ናቸው?**

መልስ፦ ሠርፀ ጴጥሮስ ማን እንደሆኑና ታሪካቸው ምን እንደሆነ ከሌላ መጽሐፍ እስካሁን አላገኘሁም፡፡

**፸፮. ሰሎሞን መልካሟ ርግቤ ይላታል፡፡ የብርሃን ደጃፍ፣ የቃል መዝገብ፣ እውነተኛዋ ዕፀ ጳጦስ ናት ሲል እንዴት ነው?**

መልስ፦ ርግብ የዋህ እንደሆነች ሁሉ ድንግል ማርያምም የዋሂት ኀዳጊተ በቀል ስለሆነች መልካሟ ርግብ ትባላለች፡፡ መዝገብ መያዣ ነው፡፡ ድንግል ማርያም የቃል መዝገብ መባሏ ቃልን በሥጋ ፀንሳ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማሕፀኗ ተሸክመው ኖራለችና፡፡ ሙሴ ዕፀ ጳጦስን ሐመልማሉ ነበልባሉን ሳያጠፋው፣ ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥለው አይቷል፡፡ በዚሁ ምሳሌ ድንግል ማርያም እሳተ መለኮት ሳያቃጥላት በሥጋ

የፀነሰችው ሐመልማል በመሆኗ ዕፀ ጳጦስ ዘበአማን ትባላለች፡፡ የብርሃን ደጃፍ መባሏ፡፡ በደጃፍ ይገቡበታል ይወጡበታል፡፡ የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ ያለ ጌታም ከእርሷ ተፀንሶ ተወልዷልና የብርሃን ደጃፍ ተብላለች፡፡

፸፯. እስጢፋኖስ [በድንጋይ] ለወገሩት ይቅርታን ለመነ ሲል ምን ማለት ነው? እኛስ ዛሬ እየወገሩን ይቅርታን ልንለምን ነው? ይህ ይቅርታ ለሁሉም ሰው ነው ወይስ እንዴት ነው? ቤተክርስቲያንን ለሚያፈርስ ሃይማኖትን ለሚንድም ይቅርታን መጠየቅ አለብን?

መልስ፦ የሚበድሉንን ይቅርታ ማለት ከሁላችንም ይጠበቃል፡፡ ይቅርታ ማለት በደል አታድርግባቸው ማለት ነው፡፡ ከይቅርታ በተጨማሪ ትክክለኛ ፍትሕንም ማስፈን አለብን፡፡ በነፍስ እንዳይቀጣቸው ብንለምንም በሠሩት ክፉ ሥራ ግን ተበዳይ ተክሦ በዳይ ክሦ መታረቅ ይገባል፡፡ ክርስቶስ ሳያውቁ ለበደሉት አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ብሏል፡፡ እያወቁ ለሚያጠፉትና ንስሓ ለማይገቡት ደግሞ እንደ ዳዊት የሚገፉኝን ግፋቸው ብሎ መጸለይ ይቻላል (መዝ.34፥1)፡፡ ቤተክርስቲያንን ለሚያፈርስ ሃይማኖትን ለሚንድም ይቅርታን መለመን ይገባል፡፡ ቤተክርስቲያንን በማፍረሱ ሃይማኖትን ለመናድ በመሞከሩ ግን ከይቅርታ ባሻገር ላጠፋው ጥፋት ፍትሕ መስጠት ይገባል፡፡

፸፰. ሰማያዊ ወታደር የሆነ ገብረ ክርስቶስ ሙሽራውን [ክርስቶስን] ተከትሎ በትዕግሥቱ ሰይጣንን አሸነፈው ይላል፡፡ ሰማያዊ ወታደር ሲል ምን ለማለት ነው?

መልስ፦ ሰማያዊውን ዓለም ለመውረስ የሚያበቃ መልካም ሥራን በመሥራት የሚተጉ ሰዎች ሰማያውያን ወታደሮች ይባላሉ፡፡ ሰማያውያን ያሰኛቸው በተፈጥሯቸው ሳይሆን በምግባራቸው ነው፡፡ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 10 መነኰሳትን ወመነኰሳትኒ መላእክት ምድራውያን ወሰብእ ሰማያውያን እንዳላቸው ያለ ነው፡፡

፸፱. ድንግል ማርያምን የሰማዕታት እናታቸው የመላእክት እኅት ብሎ ጠራት፡፡ ከምን አንጻር ነው? ዘወትር በወርቅ የሚከድኗት በውስጧ ሕግ ያለባት ታቦት ናት ሲልስ ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ድንግል ማርያም የሰማዕት እናታቸው መባሏ ሄሮድስ ልጇን ሊገድልባት በፈለገ ጊዜ ወደ ግብፅ ስትሰደድ እሾሁ ወግቷታል፣ ውሃ ጠምቷታል፣ እንቅፋት መትቷታል፡፡ በጠቅላላው ሰማዕታት እንደሚደርስባቸው መከራ ደርሶባታል፡፡ ሰማዕታት በመከራ እርሷን ይመስላሉና እናታቸው ትባላለች፡፡ የመላእክት እኅት መባሏ መላእክት ንጹሓን እንደሆኑ እርሷም በሥጋም በነፍስም ንጽሕት ናትና፡፡ በብሉይ ኪዳን በወርቅ የተከደነች ታቦት ነበረች በውስጧም ጽላት ነበረ፡፡ ያቺ የእመቤታችን ምሳሌ ናት፡፡ ወርቁ የንጽሕናዋ ምሳሌ፣ ጽላቱ የጌታ ምሳሌ፡፡ ቃሉ የቃል፣ አካለ ጽሌ የትስብእት ምሳሌ ነው፡፡ ዘወትር የሚከድኗት መባሏ ዘለዓለም ድንግል ለመሆኗ ምሳሌ ነው፡፡

፹. አባ ዮሐኒ እግዚአብሔር የወደደውና እንደ ንስር ክንፍ የሰጠው ነው ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው እንደ ንስር ክንፍ አውጥቶ ነበር ማለት ነው? መላእክትስ በእውነት እንደ ንስር ክንፍ አላቸው?ለመላእክትና ለቅዱሳን ሰዎች ክንፍ አላቸው ሲባል እንዴት ነው?

መልስ፦ ስለ ቅዱሳን ለምሳሌ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ አባ ዮሐኒና ሌሎችም ክንፍ ተሰጣቸው ሲባል ረቂቅ ክንፍ ተሰጣቸው ማለት ነው። እንጂ እንደ ወፍ እንደ ንስር የሚታይ ክንፍ ሰጣቸው ማለት አይደለም። ለመላእክትም ረቂቅ ክንፍ አላቸው። በሌላ አገላለጽ በክንፍ ከቦታ ቦታ እንደሚንቀሳቀሱበት ሁሉ ቅዱሳንም ሲበቁ እንደ መላእክት በሐሳብ ከፈለጉበት ቦታ ደርሰው ይመጣሉና ይህንን ለመግለጽ ነው።

፹፩. ማርያም ንጹሕ የመና ሙዳይ ናት ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ በብሉይ ኪዳን ከሰማይ የወረደ መና ይቀመጥበት የነበረ ሙዳይ (አገልግል) ነበረ። ድንግል ማርያም የዚያ ሙዳይ (አገልግል) ምሳሌ ናት ማለት ነው። ከሰማይ የወረደ መና ወልደ እግዚአብሔር በእርሷ ማሕፀን ለዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ተቀምጧልና የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው (ዮሐ.6፥41)።

፹፪. ከጊዜ በፊት የነበረውን ቃልን የወለደች ድንግልን ወልዳታለችና ሐና ከሴቶች ሁሉ ትበልጣለች ሲል ምን ማለት ነው? እመቤታችን ከሴቶች ትበልጣለች ታዲያ እንዴት ይታረቃል?

መልስ፦ ሐና ከሴቶች ሁሉ ትበልጣለች ሲል ከዚህ የተጠቀሰው ሁሉ ፍጹም ሁሉ አይደለም። ከሴቶች ትበልጣለች ሲል ከብዙ ሴቶች ትበልጣለች ማለት ነው። ይህም ድንግል ማርያምን አያካትትም። ከድንግል ማርያም የሚበልጥ ፍጡር የለምና። ድንግል ማርያም ከፍጡራን ሁሉ በላይ ናት።

፹፫. እግዚአብሔር ከፋራን ከቴማን ይመጣል የሚለው እንዴት ይተረጎማል?

መልስ፦ በብሉይ ኪዳን ዘመን በቴማንና በፋራን እግዚአብሔር ተአምራትን አድርጓል (ዕን.3፥3)። እስራኤላውያንንም ረድቷል። ድንግል ማርያም በቴማንና በፋራን ተራሮች ትመሰላለች። እግዚአብሔር ወልድ ከእርሷ ተወልዶ እስራኤል ዘነፍስ የተባልን ክርስቲያኖችን ረድቶናልና አድኖናልና።

፹፬. መልአክ በመልአክ ያልፋል እንጂ አሳልፈኝ አይልም ሲባል እንዴት ነው?

መልስ፦ መላእክት ረቂቃን ስለሆኑ አንዱ መልአክ በአንዱ መልአክ አካል ያልፋል ማለት ነው። እንኳንስ መላእክት የፀሐይ ብርሃንም በአየር መካከል አልፎ ከእኛ ሲደርስ ይታያልና። ረቂቅና ረቂቅ አይገፋፉምና።

፹፭. ካህናተ ሰማይ ቁጥራቸው 24 ናቸው? አንዳንድ መምህራን 24 ሰዓት ስለሚያመሰግኑ 24 ተባሉ እንጂ ቁጥራቸው 24 አይደሉም ይላሉ። የትኛው ነው ትክክል?

መልስ፦ ካህናተ ሰማይ ብዛታቸው 24 እንደሆነ ዮሐንስ አቡቀለምሲስም ገልጿል (ራእ.19፥4)። ስለዚህ ቁጥራቸው 24 አይደለም የሚለው አነጋገር ትክክል አይደለም። የሚያመሰግኑም ሁልጊዜ ነው። በ24 ሰዓት ሁሉ ያመሰግናሉ ቁጥራቸውም 24 ነው።

**፹፯. አርባዕቱ እንስሳ ሲል ምን ማለት ነው? እርሱ ራሱ ተሸክሟቸው የጌታቸውን ዙፋን ይሸከማሉ ሲልስ እንዴት ነው?**

መልስ፦ አርባዕቱ እንስሳ የተባሉት አራቱ ኪሩቤል ናቸው። እንስሳ የተባሉበት ምክንያቱም አንዱ ገጸ ላሕም፣ አንዱ ገጸ ሰብእ፣ አንዱ ገጸ ንስር፣ አንዱ ገጸ አንበሳ በመሆናቸው ነው። ሰው እንስሳ ነባቢ ይባላል። በሰውኛ አገላለጽ ሰውና ላም እንስሳ ይባላሉ። ስለዚህ በበዛው አራቱ እንስሳ ተብለዋል። ፍጥረታትን ሁሉ የሚሸከም የሚይዝ እግዚአብሔር ነው። እንዲያ ከሆነ ኪሩቤል የሚሸከሙት የተባለው ለምንድን ነው ከተባለ በዘፈቀደ ለፍጡራን የሚገለጥበትን መንበር ይሸከማሉና ነው። እንጂ እርሱን እግዚአብሔርንስ በባሕርዩ ሊሸከሙት አይችሉም። እርሱ ይሸከማቸዋል እንጂ።

**፹፰. ሐዋርያትም የወልደ እግዚአብሔርን ፈለጉን ተከተሉ ሲል ምንም ማለት ነው? ወልድ ተነሥቷል ሐዋርያትም ተነሥተዋል ማለት ነው?**

መልስ፦ ወልደ እግዚአብሔር የተባለ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የእርሱን ፈለግ ተከተሉ ማለት እርሱ ወንጌልን እንዳስተማረ ሐዋርያትም ወንጌልን አስተማሩ ማለት ነው። እርሱ በባሕርዩ ደግ ቅዱስ ሲሆን እነርሱ ደግሞ በጸጋ ደጋግ ቅዱሳን ሆኑ ማለት ነው። እርሱ ክርስቶስ ከሞት እንደተነሣ ሐዋርያትም በዳግማይ ምጽአት ከሞት ይነሣሉና ነው። ከዚህ ቀደም ግን ከሞት አልተነሡም።

**፹፱. ክርስቶስን ዳዊት ጠል በፀምር እንደሚወርድ ነው አለው ሲል ምን ማለት ነው? ፀምር ምንድን ነው?**

መልስ፦ ፀምር የሚባለው የበግ ጠጉር ነው። ጠል (ጤዛ) በበግ ጠጉር ሲወርድ የበጉ ጠጉር ጠሉን ይይዘዋል። ይህ የነገረ ክርስቶስና የነገረ ማርያም ምሳሌ ተደርጓል። ጠል ከሰማይ እንደሚመጣ ወልደ እግዚአብሔርም ስለልዕልናው ከሰማይ መጣ ይባላልና ጠል የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው። ጠልን የበግ ፀጉር እንደሚቀበለውና እንደሚይዘው ድንግል ማርያምም ይኩነኒ ብላ ተቀብላ ወልደ እግዚአብሔርን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማሕፀኗ ፀንሳ ይዘዋለችና ድንግል ማርያም የፀምር ምሳሌ ናት።

**፺. አባ ዮሐኒ በእምነቱ እንደ ኖኅ በትዕግሥቱ እንደ ኢዮብ ነው ይላል። እምነትንና ትዕግሥትን እንዴት ነው የምንገልጻቸው?**

መልስ፦ በእምነቱ እንደኖኅ ማለቱ ኖኅ ይህቺ ምድር በማየ አይኅ እንደምትጠፋ አምኖ መርከብ ሠርቷል። ይህ የመታመኑ ምልክት ነው። አባ ዮሐኒም አምላኩን ታምኖ

የሚኖር ስለነበረ በእምነቱ እንደ ኖኅ ተብሏል። ትዕግሥት የሚለው ሰምቶ መቻልን አይቶ ማለፍን ነው። ይህም ስለእግዚአብሔር ብለን የሚደርስብንን መከራ በምስጋና ሆነን ሳናማርር መቻልን ያመለክታል። ኢዮብ ብዙ መከራ ቢደርስበትም እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔር ነሣ በማለት ታግሦ አለፈው እንጂ አላማረረም። አባ ዮሐኒም ብዙ ነገሮችን ታግሿልና በትዕግሥቱ እንደ ኢዮብ ነው ተብሏል።

፺. ከመላእክት ሁሉ የአራቱ ኪሩቤል ክብር ይበልጣል ይላል። መላእክት በክብር ይበላለጣሉ?

መልስ፦ አዎ ይበላለጣሉ። ነገር ግን መበላለጣቸው አንጻራዊ ነው። ኪሩቤል ከሌሎች መላእክት በክብር ይበልጣሉ የተባሉት መንበሩን የሚሸከሙ እነርሱ በመሆናቸው በዚህ ምክንያት ነው።

፺፩. ፀወርተ መንበር ከነገደ ኪሩቤል ብቻ ናቸው ወይስ ከሱራፌልም አሉ? ከሱራፌልም ካሉ ለምን ኪሩቤል ተባሉ?

መልስ፦ ፀወርተ መንበር አራቱ ኪሩቤል የሚባሉት ሁለቱ ከነገደ ኪሩቤል ሁለቱ ከነገደ ሱራፌል ተመርጠዋል። ስያሜያቸው ኪሩቤል የተባለበት ምክንያት ግን ኬረበ=አራት አደረገ ስለሚል አራትነታቸውን ለመግለጽ ስለሆነ ነው። እንጂ ነገዱን ኪሩቤልን አስቦና የተመረጡትን ሁለቱን ከኪሩቤል መሆናቸውን አስቦ አይደለም። እንዲያ ቢሆን ኖሮማ ሱራፌልም በተባሉ ነበር።

፺፪. ኪሩቤል ፀወርተ መንበር ሲባሉ ቦታቸውን ይለቃሉ?

መልስ፦ ኪሩቤል እግዚአብሔር በዘፈቀደ ለፍጡራን የሚገለጥበትን መንበር የሚሸከሙ ናቸው። ስለዚህ እግዚአብሔር በዘፈቀደ መገለጥ ወደፈለገበት ቦታ ሁሉ ይሄዳሉ። ኀበ አንጸረ ቀዳማዊ የሐውሩ የሚል ለዚህ ነው።

፺፫. ኢሳይያስ በሚያምር የሥጋ ልብስ ከኤዶም የሚወጣ የሚያምር ነው አለው ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ኤዶም የተባለች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት። ከእርሷ በሚያምር (በሚያስፈራ) የሥጋ ልብስ የሚወጣ ማለት ወልደ እግዚአብሔር ከእርሷ ሥጋንና ነፍስን ነሥቶ ተዋሕዶ የሚወለድ ነው ማለት ነው። የሚያስፈራ መባሉ ለአጋንንት፣ ለአይሁድ ነው። የሚያምር፣ ደስ የሚያሰኝ መባሉ ለምእመናን ለመላእክት ነው።

፺፬. በእምነት በሰማያት ተስፋን አገኙ የእሳትን ኀይልም አጠፉ ሲል ምን ማለት ነው? የእሳት ኀይል ምንድን ነው?

መልስ፦ የእሳትን ኀይል አጠፉ ሲል የእሳት ኀይሉ ማቃጠሉ ነው። አንዳንድ ቅዱሳን በእምነት የእሳትን ኀይል አጥፍተዋል ማለት ወደ እሳት ቢጥሏቸውም እግዚአብሔር እንደ ሠለስቱ ደቂቅ እሳቱን ያቀዘቅዝላቸው ነበር ማለት ነው። በሌላ መንገድ ወደ ገነት በመግባታቸው የሲኦልን እሳት ሳያገኙት ቀርተዋል ማለት ነው።

፺፫. ጊዮርጊስ የሰማዕታት አለቃ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?

መልስ፦ እግዚአብሔር ባወቀ ጊዮርጊስን የሰማዕታት አለቃ ብሎታል። ይኸውም በተቀበለው መከራና ባለው ጽንዐ ሃይማኖት መሠረት ነው።

፺፬. እግዚአብሔር ስለእርሷና ስለዘመዶቿ በእንጨት ላይ ተሰቀልኩ አለ ይላል። ለእርሷ ሲል ምን ማለት ነው? ድንግል ማርያም ከበደል ንጹሕ ናት። ታዲያ ለምን ስለእርሷ ተሰቀልኩ ይላል?

መልስ፦ ክርስቶስ የተሰቀለው ስለዓለም ሁሉ ነው። ያዳነውም ዓለምን ሁሉ ነው። ስለዘመዶቿ ተሰቀልኩ ማለቱ ስለአዳም ልጆች ሁሉ ተሰቀልኩ ማለቱ ነው። "የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ" እንዲል (2ኛ ቆሮ.5፥14)። ስለእርሷ ብሎ ስለእመቤታችን መናገሩ ራሷ "ጌታዬና መድኀኒቴ" ባለችው አግባብ የሚተረጎም ነው (ሉቃ.1፥47)። ይህም በሌላው ሊደርስ ከነበረው ሁሉ አድኗታልና። እንዳይደርስባትም ጠብቋታልና ነው። ከመርገም መጠበቁን ነው ማዳን ያለው። ገነት ለመከፈት የክርስቶስን ደም ትፈልግ ነበር። ሌላው ስለእርሷ ተሰቀልኩ ማለቱ ደግነቷን አስቤ ሌሎችንም ስለእርሷ ስል ማርኳቸው ማለቱ ነው። ስለዘመዶቿ ሲል ቀጥሎ አብርሃምሀ፣ ዳዊትሀ እያለ ደጋጎችን ስለሚጠቅስ ስለደጋጎች ብዬ ደጋጎችን አስቤ ተሰቅዬ ሌሎችን ሰዎችም አዳንኳቸው ማለት ነው።

፺፭. ማርያምስ [ማርያም ግን] ከጥንት ጀምሮ በአዳም ባሕርይ እንደ ዕንቊ ታበራ ነበር ይላል። ምን ማለት ነው? ከአዳም ጀምሮ ደም እየተቀዳ ይመጣ ነበር የሚሉ አሉ (አንድምታ ውዳሴ ማርያም)። እንዴት ይታያል? ዕንቊ ምንድን ነው?

መልስ፦ ከአዳም ጀምሮ እስከ ዕለተ ምጽአት የሚነሡ የሰው ልጆች ባሕርይ አንድ ዓይነት ነው። ብዙ ጊዜ ወልደ እግዚአብሔር ባሕርያችንን ተዋሐደ እያልን ስንናገር ከድንግል የነሣው ሥጋ ባሕርዩ ከእኛ ጋር አንድ ስለሆነ ነው። ባሕርያችንን ብለን የምንናገረው (ሃይ.35፥3፤ ሃይ.38፥4፤ ሃይ.አበ. 83፥10)። ስለዚህ ማርያም በአዳም ባሕርይ እንደ ዕንቊ ታበራ ነበር ያለው በተለየ የእርሷ አካል መርገመ ሥጋ፣ መርገመ ነፍስ የሌለበት መሆኑን ይገልጻል። እንጂ ከአዳም ጀምሮ እየተቀዳች እየተቀዳች መጣች ማለት አይደለም። የድንግል ማርያም ህልውና የሚጀምረው ከሐና ደም ሲከፈል ከኢያቄም (ሳዶቅ) ዘር ሲከፈል ነው። እንጂ ከቀድሞ ጀምሮ እንደ ቦይ ስትቀዳ የመጣች አይደለችም። ይህ በጽጌ ረዳ አምሳል ነው። ጽጌረዳ ግንዱ እሾኻም ሆኖ ሳለ እሾህ

የሌለበት ምርጥ አበባን ያወጣል:: እንደዚሁ በመርገመ ሥጋ በመርገመ ነፍስ ከነበሩ አበው መርገም የሌለባት መዓዛዋ ድንቅ የሆነች አበባ ድንግል ማርያም ተገኘችልን:: ዕንቊ የሚባለው የመዓድን ዓይነት ነው:: ከሌላው አፈር በተለየ የሚያበራ የከበረ መዓድን ነው:: እመቤታችን በዚህ አምሳል መገለጿ ዕንቊ ከአፈር ከድንጋይ እንደሚከብር እርሷም ከሰው ልጆች ሁሉ የከበረች በመሆኗ ነው::

፺፰. ሚካኤልን በዐሥራ አራቱ ታላቅ ልመናህና በድንቅ ትህትናህ ማልድልን ይላል:: ዐሥራ አራቱ ልመናዎች እነማን ናቸው?

መልስ፦ ምንም እንኳ ቅዱስ ሚካኤል ሁልጊዜም ስለሰው ልጆች ልመናን ቢያቀርብም በተለየ ደግሞ በመታሰቢያ ዕለቶቹ ከሌላው ጊዜ በበለጠ በቃል ኪዳኑ ለምኖ ድኅነትን ያሰጣል:: ዐሥራ አራቱ ልመናህ የተባሉ በየወሩ በየወሩ በ12 በ12 ሚካኤል ስለነፍሳት ይለምናልና ነው:: በዝርዝር መስከረም 12፣ ጥቅምት 12፣ ኅዳር 12፣ ታኅሣሥ 12፣ ጥር 12፣ የካቲት 12፣ መጋቢት 12፣ ሚያዝያ 12፣ ግንቦት 12፣ ሰኔ 12፣ ሐምሌ 12፣ ነሐሴ 12 ናቸው:: እነዚህ የ12ቱ ወራት 12 ይሆናሉ:: ሁለቱ ደግሞ አንዱ የኅዳር አእላፍ ኅዳር 13፣ ሌላኛው የኅዳር ካህናተ ሰማይ ኅዳር 24 ናቸው:: 14ቱ የተባሉ በጠቅላላ እነዚህ ናቸው::

፺፱. ሚካኤል ኃጢአትንም ያስተሠርያል ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ በባሕርዩ ኃጢአትን ይቅር የሚል እግዚአብሔር ብቻ ነው:: የፍጡራን ይቅር ባይነት የጸጋ ማስተሥረይ ነው:: ጌታ ለሐዋርያት ኃጢአትን እንዲያስተሠርዩ ሥልጣንን እንደሰጣቸው ያለ ነው (ዮሐ.20፥23):: መልአኩም ያስተሠርያል የተባለ በዚህ አግባብ የጸጋ ነው::

፻. የመላእክት አለቃ ሚካኤል ስለሙሴ ሥጋ ከሰይጣን ጋር በተነጋገረ ጊዜ የስድብን ቃል ይናገር ዘንድ አልደፈረም ሲል ምን ማለት ነው? እግዚአብሔር ይገሥጽህ ማለት ስድብ አይደለም ወይ?

መልስ፦ እግዚአብሔር ይገሥጽህ ማለት ከስድብ ጋር አይገናኝም:: ሰይጣን የሙሴ አፅም የት እንዳለ ሊያሳያቸው ፈልጎ ነበር:: ይህም በአፅሙ እንዲያመልኩና ከእግዚአብሔር ለማራቅ በማሰብ ነበር:: በዚህ ሁኔታ ሰይጣን ከሚካኤል ጋር ሲነጋገር እግዚአብሔር ይገሥጽህ ብሎታል (ይሁ.1፥9):: ሙሉ ታሪኩ ከሌሎች አዋልድ መጻሕፍት ይገኛል:: ስድብ የሚባለው ለሌሎች ክፉ ስም መስጠት፣ አዋርዶ መናገር ነው:: እግዚአብሔር ይገሥጽህ ማለት ደግሞ ከእነዚህ የተለየ ነው::

፻፩. ሚካኤል ዐይኑ የርግብ፣ ልብሱ የመብረቅ የወርቅ ሐመልማል ነው ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ የርግብ ዓይን ጽሩይ (የጠራ) ነው። ቅዱሳን መላእክትም አጥርተው ያያሉና ዓይናቸው የርግብ እየተባሉ ይገለጻሉ። ሚካኤል ዐይኑ የርግብ የተባለ በዚህ አግባብ ነው። መብረቅ አስፈሪ እንደሆነ መላእክትም ግሩማን ስለሆኑ የሚካኤልን ግሩምነት ለመግለጽ ልብሱ የመብረቅ ተብሏል። የወርቅ ሐመልማል የሚለውም በልብስ ላይ የሚደረግ ከወርቅ የተሠራ ልምላሜ ማለት ነው። ይህ ለመላእክት ሲነገር ወርቅ የተከበረ እንደሆነ ንጹሕ ጽሩይ እንደሆነ ቅዱሳን መላእክትም ንጹሓን ክቡራን መሆናቸውን ለመግለጽ የተነገረ ነው። በሌላ መልኩ ለመላእክት ረቂቃን ልብሶች፣ ረቂቃን ዐይኖች ስላላቸው ስለዚያ የተነገረም ነው።

፻፪. መላእክት [እርሱን እግዚአብሔርን] ማየትን ይመኛሉ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ እግዚአብሔርን በባሕርዩ ያየው አንድስ እንኳ የለም (ዮሐ.1፥18)። ይህ ብቻ ሳይሆን በዘፈቀደ የሚገለጥበትን አካል ለማወቅ ራሱ ቅዱሳን መላእክት በጣም ይመኛሉ። ይህን ለመግለጽ ነው። ሰው በሆነ ጊዜ በሥጋ በማየታቸውም በጣም ደስ ብሏቸዋል። "ዘያፈትዎሙ ለመላእክት ከመ የሐውጽዎ" እንዲል (ሃይ.አበ.75፥22)።

፻፫. የመላእክት አለቃ ሚካኤል የእግዚአብሔር አማካሪ ነው ሲል ምን ማለት ነው? ፈጣሪ አማካሪ ያስፈልገዋል ወይ?

መልስ፦ ቅዱስ ሚካኤል መልአከ ምክሩ (የምክሩ አበጋዝ) ይባላል። ከሚካኤል በፊት እግዚአብሔር ነበረ። ሚካኤል አማካሪ የተባለበት ምክንያት እግዚአብሔር የቅዱሳንን ባለሟልነት ለመግለጽ ሊያደርገው ያሰበውን ይነግራቸዋልና ሊያደርገው ያለውን ነገር ለሚካኤል ነግሮት ስለሚሰማ ነው። ለመላእክት ብቻ ሳይሆን ለነቢያትም ሊያደርገው ያሰበውን ይነግራቸው ነበር። "እስመ አልቦ ዘይገብር እግዚአብሔር ዘኢከሠተ ወዘኢነገረ ለአግብርቲሁ ለነቢያት" እንዲል (አሞፅ 3፥7)። ስለዚህ አማካሪ መባሉ ክብሩን በሰውኛ ለመግለጽ እንጂ እግዚአብሔር ፍርድ አላውቅ ብሎ የሚረዳው ረዳት አስፈልጎት አይደለም።

፻፬. ሰውና መላእክት ማኅበራቸው አንድ ነው ሲል በምንድን ነው?

መልስ፦ ሁላችንም የምናመልከው አንድ እግዚአብሔር፣ ሁላችንም የምናምነው በአንዲት ሃይማኖት ስለሆነ መላእክትና ሰዎች አንድ ማኅበር አለን ይባላል።

፻፭. ዘካርያስ ሁለንተናዋ የወርቅ የሆነ፣ በቀኟና በግራዋ የዘይት ቅርንጫፎች ያሉባት፣ ሰባት መብራቶችና ሰባት ቧንቧዎች በላዩዋ ያለባት የብርሃን መቅረዝን አየ ይላል ምን ማለት ነው? ሰባት መብራቶችና ሰባት ቧንቧዎች ምንድን ናቸው?

መልስ፦ ዘካርያስ በራእይ እኒህን አይቷል። ይህ ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ሆኗል። መቅረዝ የእርሷ ምሳሌ ከእርሷ የተገኘው ብርሃን የጌታ ምሳሌ

ነው:: ወርቅ የንጽሕናዋ ምሳሌ ነው:: ለቤተክርስቲያንም ምሳሌ እንደሆነ ቅዱስ ያሬድ ገልጿል:: ሰባት ቧንቧዎች የሰባቱ ዕለታት ምሳሌዎች ናቸው:: ሰባቱ መብራቶች የሊቃውንት ምሳሌ ናቸው:: በሰባቱ ቧንቧዎች ያለፈ ፈትል ዘይትን አግኝቶ ለሌላው እንደሚያበራ ሁሉ ሊቃውንትም ትምህርትን ከእግዚአብሔር አግኝተው በሰባቱ ዕለታት እያስተማሩ ለምእመናን እውነትን ጽድቅን ያበራሉና ነው::

## ፻፮. ድንግል ማርያም የተዘጋች በር፣ ማሰሮ፣ ሐውልት፣ የጳዝዮን እንቁ እና የኖኅ መርከብ መባሏ ምሳሌው እንዴት ነው?

መልስ፦ የተዘጋች የምሥራቅ በር የተባለች በምሳሌ ነው (ሕዝ.44፥2):: ሕዝቅኤል በራእይ ያየት ደጅ እግዚአብሔር ገብቶ የወጣባት ስለሆነች ተዘግታ እንደምትኖር ይገልጻል:: እግዚአብሔር በድንግል ማርያም ማሕፀን ተፀንሶ ተወልዷል:: ከእርሱ በስተቀር ወደእርሷ ገብቶ (ከእርሷ ተፀንሶ) የወጣ (የተወለደ) ስለሌለ ይህንን ለመግለጽ ነው:: የድንግል ማርያምን ዘለዓለማዊ ድንግልና ይገልጽልናል:: ድንግል ማርያም በኤልሳዕ ማሰሮ የተመሰለችበት ምክንያት ኤልሳዕ በአዲስ ማሰሮ ጨው ጨምሮ መራራውን ውሃ ከምረቱ አድኖታል:: ከአዲሲቱ ማሰሮ የተወለደው አልጫውን ዓለም ያጣፈጠው የሕይወት ጨው ክርስቶስ (ጼው ዘአጥዐሞ ለልሱሕ) ደግሞ መርገመ ሥጋን መርገመ ነፍስን አጥፍቷልና በአዲስ ማሰሮ የተመሰለች ለዚህ ነው (2ኛ ነገ.2፥20-22):: ኢያሱ ሕገ እግዚአብሔርን ለሕዝቡ ካስተማረ በኋላ አንዲት ድንጋይ አንስቶ ብትክዱ ምስክር ይሆንባችኋል ብሏል:: "ኢያሱም ለሕዝቡ እነሆ የተናገረንን የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉ ሰምቷልና ይህ ድንጋይ ይመሰክርብናል:: እንግዲህ አምላካችሁን እንዳትክዱ ይህ ምስክር ይሆንባችኋል አላቸው" እንዲል (ኢያ.24፥27):: ድንጋዩ ቃሉን ሰምቶ ምስክር እንደሆነ ሁሉ ድንግል ማርያምም ቃለ እግዚአብሔርን ሰምታ ምስክር ሆናለችና ነው:: "ወብፅዕት አንቲ እንተ ተአምኒ ከመ ይከውን ቃል ዘነገሩኪ እምኀበ እግዚአብሔር" እንዲል (ሉቃ.1፥45):: የጳዝዮን ዕንቊ የከበረ እንደሆነ ድንግል ማርያምም ከፍጥረት ሁሉ የከበረች ስለሆነች በጳዝዮን ዕንቊ ተመስላለች:: በኖኅ መርከብ የመመሰሏ ምስጢር ኖኅ ማለት የስሙ ትርጓሜ ዕረፍት ማለት ነው:: ኖኅ በመርከቢቱ እንደነበረ ዕረፍተ ሥጋ ዕረፍተ ነፍስ የሆነ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሷ በድንግል ማርያም ተፀንሶ ለዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ኖሯልና ነው::

## ፻፯. ናግራን የት አከባቢ ያለች ሀገር ናት? የአሸናፊዎች የሰማዕታት ሀገር ናት ሲልስ ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ናግራን የመን አካባቢ የምትገኝ ሀገር ናት:: ብዙ ክርስቲያኖች ነበሩባት:: ነገር ግን አንድ አይሁዳዊ ተነሥቶ ብዙ ምእመናንን ገድሏል:: ብዙዎችም በሰማዕትነት አርፈዋል:: በዚህ ምክንያት ሀገሪቱ የአሸናፊዎች የሰማዕታት ሀገር ተብላለች:: ለእውነት መሞት አሸናፊነት ነውና::

**፻፰. የሚያስፈራ ባሕርን እንደ ግድግዳ አቁሞ በመካከሉ መንገድን አሳየ ሲል ምን ማለት ነው?የሚያስፈራ ባሕር ምንድን ነው?**

መልስ፦ ይህ ስለባሕረ ኤርትራ የተነገረ ነው። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብጽ ሲያወጣቸው ባሕረ ኤርትራን ከፍሎ ነው። አስፈሪ የሆነውን ባሕረ ኤርትራ እንደ ግድግዳ ግራና ቀኝ አቁሞላቸው ተሻግረዋል (ዘፀ.14፥22)። የሚያስፈራ ባሕር መባሉ ባሕር በተፈጥሮ አስፈሪነትም (ግሩምነት) ስላለው ነው።

**፻፱. ወለተ ጴጥሮስ ማን ናት? የኬፋ ልጅ ሲልስ እንዴት ነው?**

መልስ፦ ወለተ ጴጥሮስ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ የተወለደች ኢትዮጵያዊት ቅድስት ናት። የካቶሊክ አስተምህሮን በመቃወምና የምንኵስና ሕይወትን በማስፋፋቷ ትታወቃለች። ይህ ዓይነቱ የድን ክፍል አዋልድ ድን ይባላል። ቅዱስ ያሬድ ያልደረሰው የቅዱስ ያሬድን የድርሰት ስልት ተከትለው ሌሎች አባቶች ከድጓው ጋር ጨምረው ያዘጋጁት ማለት ነው። ኬፋ የጴጥሮስ ሌላ ስሙ ስለሆነ ወለተ ጴጥሮስ ለማለት ወለተ ኬፋ እያለም ተጨማሪ ስምን ይገልጻል (ዮሐ.1፥42)።

**፻፲. ምድር በሚካኤል ጸሎትና ልመና ታድራለች ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ይህ ቅዱስ ሚካኤል ለሰው ልጆች እንደሚለምን ለመግለጽና እግዚአብሔር ደግሞ የቅዱስ ሚካኤልን ልመና ሰምቶ ምድርን በረድኤት እንደሚጠብቃት የተገለጸ ነው። "ብቻ" የሚል አገላለጽ ስለሌለ የሚካኤልን አማላጅነት ከመግለጽ የዘለለ አጠቃላይና ብቸኛ ነገር ነው ለማለት አይደለም።

**፻፲፩. ሚናስ በሰማይ አዳራሽ የተመረጠ ነው ሲል ምን ማለት ነው? አዳራሽ የተባለው ምንድን ነው?**

መልስ፦ አዳራሽ ያለው ክብርን ነው። እንጂ በሰማይ ልዩ ልዩ አዳራሾች ኖረው አይደለም። የጻድቃንን ክብር ለመግለጽ አዳራሽ፣ ቤት፣ ማኅደር እያሉ መግለጽ ልማደ መጻሕፍት ነው። ጌታ እንኳ ሲያስተምር "እስመ ውስተ ቤተ አቡየ ብዙኅ ማኅደር ወምዕራፍ ቦቱ። ወናሁ እብለክሙ ከመ አነ አሐውር ወአስተዳሉ ለክሙ መካነ። ወእመአኮሰ እምኢይቤለክሙ ከመ አሐውር ወአስተዳሉ ለክሙ ማኅደረ" ብሏል (ዮሐ.14፥2)። ስለዚህ ሚናስ በሰማይ አዳራሽ የተመረጠ ነው ማለት በሰማያዊ ክብር የከበረ ነው ማለት ነው።

**፻፲፪. የእግዚአብሔር መላእክት ፊታቸው ከፀሐይ ይልቅ ሰባት እጅ ያበራል ሲል ምን ማለት ነው? ሚካኤል ሊቀ መላእክት መባሉ ለፀወርተ መንበርም ነው?**

መልስ፦ የመላእክት ብርሃን ከፀሐይ ብርሃን ይልቅ ሰባት እጥፍ ነው ማለት ነው። ጻድቃንም ከምጽአት በኋላ ከፀሐይ ሰባት እጅ የበለጠ እንደሚያበሩት ያለ ነው። "አሜሃ

ይበርሁ ጻድቃን ምስብዒተ እደ እምብርሃነ ፀሐይ በመንግሥተ አቡሆሙ ዘበሰማያት" እንዲል (ማቴ.13፥43)። ሚካኤል ሊቀ መላእክት መባሉ ለሁሉም ነው። ይህም ለፀወርተ መንበርም ለካህናተ ሰማይም ነው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር በዘፈቀደ የሚገለጥበትን ዙፋን በመሸከም ኪሩቤል የበለጡ ቢሆንም በሌላ መልኩ ደግሞ የሁሉም ነገድ አለቃ ሆኖ በመሾሙ ሚካኤል የሁሉ አለቃ ነው። አለቅነቱ የአዛዥነትና የታዛዥነት አለቅነት አይደለም። የዕውቀት፣ የእግዚአብሔርን ምስጢር የማወቅ ቅድምናና እርሱ እግዚአብሔር ባወቀ ነው።

**፻፲፫. አኗኗራችን በጸጥታ ይሆን ዘንድ አቤቱ አምላካችን ሆይ እንማልድሀለን ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ በጸጥታ ማለት በሰላም ማለት ነው። የሑከት ተቃራኒ ጸጥታ ነው። ስለዚህ አኗኗራችን በሑከት በብጥብጥ ሳይሆን በጸጥታ በሰላም ይሆን ዘንድ አቤቱ እንለምንህለን ማለት ነው።

**፻፲፬. ካህን በተጋ ጊዜ ብርሃን ለዓለም ሁሉ ተገለጠ ሲል ምን ማለት ነው? ካህናት ንጹሕ አክሊል በራሳቸው ላይ አለ ሲልስ ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ አክሊል የክብር ምልክት ነው። ካህናት ንጹሕ አክሊል በራሳቸው ላይ አለ ማለት የተወደደ ክብር አላቸው ማለት ነው። ካህን በተጋ ጊዜ ብርሃን ለዓለም ሁሉ ተገለጠ ማለቱ የካህን ትጋት ለዓለም ብርሃን እንደሚሆን ይገልጻል። ይህም ሐዋርያትን "የዓለም ብርሃን ናችሁ" ባላቸው አግባብ የሚተረጎም ነው (ማቴ.5፥14)። ሐዋርያት የተቻላቸውን ያህል አስተምረው በማለፋቸው የዓለም ብርሃን እንደተባሉ ሁሉ በእነርሱ እግር የተተካ ካህንም ለአገልግሎት መትጋቱ አገልግሎቱ ለዓለም ሁሉ የሚጠቅም ስለሆነ ብርሃን ለዓለም ሁሉ ተገለጠ ተብሏል።

**፻፲፭. ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ሙሽራዋ ነው ሲል ምን ለማለት ነው?**

መልስ፦ ቅዱስ ያሬድ ብዙ ጊዜ ክርስቶስን በሙሽራ [መርዓዊ] ቤተክርስቲያንን በሙሽሪት [መርዓት] እየመሰለ ተናግሯል (ማቴ.25፥6)። ይህም ሙሽራና ሙሽሪት በጋብቻ አንድ እንደሚሆኑ ሁሉ ክርስቶስና ቤተክርስቲያንም አንድ ናቸውና ነው። አንድነታቸውም ቤተክርስቲያን እርሱን በማምለክ ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስቲያንን በመጠበቅ ነው (ዮሐ.3፥29)።

**፻፲፮. ሰውን የሚወድ ክርስቶስ ሁልጊዜ ይቅር ባይ ነው ሲል እንዴት ነው? በተለያዩ ጊዜያት የሚከሰቱ ከበባድ አደጋዎች ከይቅር ባይነቱ አንጻር እንዴት እንገልጻቸዋለን?**

መልስ፦ ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕርዩ ይቅር ባይ ነው። ይቅር ባይነቱ የባሕርዩ እንደመሆኑ መጠን ከአካሉ ተለይቶ አያውቅም። ለዘለዓለሙ የእርሱ ገንዘብ ሆኖ ይኖራል እንጂ።

በተለያዩ ጊዜያት የተከሠቱና የሚከሠቱ ከባድ አደጋዎች ከይቅር ባይነቱ ጋር አይቃረኑም። አደጋዎች የተደረጉበት ምክንያት ምናልባትም አደጋ የደረሰባቸውን ሰዎች ለመጥቀምም ሊሆን ይችላልና። እግዚአብሔር የሚያደርገው ነገር ሁሉ ለሰው ልጆች ጥቅም ነውና። ደግሞም እግዚአብሔር መሐሪ ብቻ ሳይሆን ፈታሒም ጭምር ነው። ፈታሒነቱና መሐሪነቱ የተስማሙለት አምላክ ስለሆነ ሁሉን እንደ ጊዜ ግብሩ እንደሚገባው ያደርጋል።

**፻፲፯. የድንግል በኵሯ ሲል እንዴት ነው የሚተረጎምው? ክርስቶስን ከወለደች በኋላ ተከታይ ልጅ ስለሌላት እንዴት ነው በኵሯ የተባለ?**

መልስ፦ ኢየሱስ ክርስቶስ የድንግል ማርያም የበኵር ልጇ ነው (ማቴ.1፥25)። በኵር ለመባል መስፈርቱ መጀመሪያ መወለድ ነው እንጂ ተከታይ ልጆች መኖራቸው አይደለም። ስለዚህ ምንም እንኳ ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ከጌታ በቀር ልጅ ባይኖራትም እርሱ የወለደችው ጌታ ግን የመጀመሪያም የመጨረሻም ልጇ በመሆኑ በኵሯ ይባላል። ይህንን የመሰለ ለአብም ተነግሯል። ወልድ የአብ ብቸኛ ልጁ ነው (ዮሐ.3፥16)። ተከታይ ባይኖረውም በኵሩ ተብሏል። “ፈነዎ ለበኵሩ ውስተ ዓለም” እንዲል (ዕብ.1፥6)።

**፻፲፰. ይቀውም ሎሙ በደብተራ ሲል ምን ለማለት ነው?**

መልስ፦ ክርስቶስ ለጻድቃን በሰማያዊት ደብተራ በገነት [በመንግሥተ ሰማያት] ይቆምላቸዋል ተብሏል። ይቆምላቸዋል ለክርስቶስ ሲነገር ይፈርድላቸዋል ተብሎ ይተረጎማል። "እግዚአብሔር ቆመ ውስተ ማኅበረ አማልክት" ሲል ምስጢሩ ፈረደ ማለት ነውና (መዝ.81፥1)። ይቀውም ሎሙ በደብተራ ማለት በመንግሥተ ሰማያት ይፈርድላቸዋል ማለት ነው። ነግሦላቸው እንደሚኖር ለማመልከትም ይሆናል። ቆመ በምስክር ነገሠ ተብሎም ይተረጎማልና።

**፻፲፱. በክርስቶስ ያላችሁ ሥጋችሁን አንጹ ይላል። ሥጋ እንዴት ነው የሚነጻ?**

መልስ፦ ሥጋችሁን አንጹ የሚለው ሰውነታችሁን አንጹ ለማለት ነው። ይህም ማለት ኃጢአትን ባለመሥራት ጽድቅን በመሥራት ጸንታችሁ ኑሩ ማለት ነው (ያዕ.4፥8)።

**፻፳. ጻድቃን ሞት በሌለበት በኢየሩሳሌም ደስ ይላቸዋል ሲል ኢየሩሳሌም የተባለች ማን ናት?**

መልስ፦ ከዚህ ኢየሩሳሌም ያላት ከሰባቱ ሰማያት አንዷ የሆነችውና ጻድቃን ለዘለዓለም ወርሰዋት የሚኖሯት መንግሥተ ሰማያት ናት። የመንግሥተ ሰማያት ሌላ ስሟ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ነውና።

**፻፳፩. ጴጥሮስ ወታደሮችን የተላካችሁበትን ፈጽሙ አላቸው ሲል ምን ማለት ነው? ልዩ የሆነች ቀሚሱን አውልቆ አንገቱን ሰጣቸው ሲል ምን ማለት ነው? የተላኩበት ምንድን ነው?**

መልስ፦ ይህ ጴጥሮስ የእለእስክንድሮስ፣ የአርዮስና የአኪላስ መምህር የነበረው ተፍጻሜተ ሰማዕት ጴጥሮስ ነው፡፡ ዐላውያን እስር ቤት አስረውት ነበር፡፡ ቀሚሱን አውልቆ የሚለው በአንገቱ ዙሪያ የነበረውን የቀሚስ ክፍል አንገቱ እስኪታይ ዝቅ አድርጎ ለማለት ነው፡፡ ሰማዕትነትን ለመቀበል እርሱን መግደል ለሚፈልጉት ጭፍሮች አንገቱን አመቻችቶ ሰጥቷቸው ገድለውታል፡፡ እርሱም በዚህ ሰማዕትነቱን ፈጽሟል፡፡ ጭፍሮች የተላኩበት መልእክት መግደል ነበር፡፡

፻፳፪. የማሸነፍ ፍርዱ እስኪ መለስ ተጠበቅ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ የእግዚአብሔር ፍርድ በአሸናፊነት የሚሰጥ ፍርድ ነው፡፡ ፍርዱም አሸናፊ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ፍርድ በዘመን ብዛት የማይለወጥ ነውና፡፡ ይህ ፍርዱ እስኪመለስ ማለቱ የጌታ ፍርድ በምልአት የሚደረግ በምጽአት ጊዜ ስለሆነ ምጽአት እስኪሆን ድረስ በመልካም ሥራ ጸንተህ ኑር ማለት ነው፡፡ እስኪመለስ የሚለው እስኪሆን ማለት ነው፡፡ ገብአ በምስክር ኾነ ተብሎም ይተረጎማልና፡፡

፻፳፫. የጻድቅ ሥልጣኑ በክብር ከፍ ከፍ ይላል ሲል እንዴት ያለ ሥልጣን ነው?

መልስ፦ ሥልጣን ማለት በአንድ ነገር ላይ ባለቤት መሆን ማለት ነው፡፡ ጻድቃን በዚህ ምድር እያሉ እግዚአብሔር በፍጡራን ላይ ተአምራትን ያደርጉ ዘንድ በጸጋ ያሠለጥናቸዋል፡፡ ይህ ሥልጣናቸው በክብር ከፍ ከፍ ይላል ማለት በዚህ ምድርም በወዲያኛው ዓለምም የመልካም ሕይወት ባለቤት ሆነው ይኖራሉ ማለት ነው፡፡

፻፳፬. ጴጥሮስ ተፍጻሜተ ሰማዕትን ለአሕዛብ የሕግ መምህር ነው ሲል ምን ማለት ነው? የሕግ መምህር ክርስቶስ አይደለም ወይ?

መልስ፦ የሕግ መምህር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን የሕግ መምህር ነው ስንለው ግን ሕግን ከባሕርዩ አንቅቶ የሚሰጥ በባሕርዩ መምህር የሆነ ማለታችን ነው፡፡ በባሕርዩ መምህር እርሱ ብቻ ነውና (ማቴ.23፥8)፡፡ ቅዱሳን ደግሞ ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ጸጋ ሕጉን ያስተምራሉና የሕግ መምህራን ይባላሉ፡፡ ከዚህ ጴጥሮስ የሕግ መምህር የተባለው በጸጋ ነው (የሐዋ. ሥራ 5፥34)፡፡

፻፳፭. አንተ የእግዚአብሔር ሰው ግን ከነውር ሽሽ እውነትንም ተከተል ሲል ማንን ነው?

መልስ፦ የእግዚአብሔር ሰው የሚባሉ በእግዚአብሔር አምነው የተጠመቁ ሰዎች ናቸው፡፡ ቅዱስ ያሬድ እነዚህን ምእመናን ሲመክር ከነውር ሽሹ እውነትን ተከተሉ ብሏቸዋል፡፡ ነውር የሚለው ኃጢአት ነው፡፡ ከኃጢአት ሽሹ ማለቱ ነው፡፡ እውነት ያለው ጽድቅ ነው፡፡ ጽድቅን ሥሩ ማለት ነው፡፡

# መጽሐፈ ድጓ ዘአስተምህሮ ላይ የተጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው



አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው ካሣ
(የመጻሕፍተ ሊቃውንት፣ የመጻሕፍተ ብሉያትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)
ነሐሴ ፺፣ ፳፻፲፫ ዓ.ም

## ዘአስተምሕሮ

**፻፷፮. እመቤታችን በደብተራ ጳውሊ ትመሰላለች። በየትኛዋ ደብተራ ነው? በዕብራውያን የጠቀሳት ናት ወይስ ይሰፋቸው ከነበሩት?**

መልስ፦ እመቤታችን በደብተራ (በድንኳን) የተመሰለችው ዕብራውያን ላይ በተጠቀሰችው ደብተራ ነው። "ወክርስቶስሰ ዘመጽአ ከዊኖ ሊቀ ካህናት ለእንተ ትመጽእ ሠናይት በውስተ እንተ ተዐቢ ወትጌይስ ደብተራ እንተ ኢገብራ እደ ሰብእ ወኢኮነት በውስተ ዝ ዓለም" እንዲል (ዕብ.9፥11)። ለዚህም ማስረጃው ሰው ያልሠራት [እንተ ኢገብራ እደ ሰብእ] የሚለው አገላለጽ ነው። ጳውሎስ ድንኳንን ሰፋ ከተባለ ግን ሰው የሠራት ስለሆነች ለተጠቀሰው ምሳሌነት አትሆንም።

**፻፷፯. ኢየሱስ ክርስቶስ ያልተሠራና ያልተፈተለ ልብስ ነው ሲል ምን ማለት ነው? ዐይኖቹ ከወይን ይልቅ የሚያምሩ፣ ጥርሶቹ እንደበረዶ ነጭ የሆኑ ናቸው ሲልስ ምንን ለመግለጽ ነው?**

መልስ፦ ይህ በትርጓሜ ቋንቋ "ልብስ" ግሥ ይባላል። በቅኔ ቋንቋ ደግሞ "ልብስ" ስም ይባላል። ክርስቶስን በልብስ መስሎታል። ያልተሠራና ያልተፈተለ ልብስ የሚባለው ሥረ ወጥ ልብስ ነው። ሥረ ወጥ ልብስ የሚባለው ደግሞ ጫፍና ጫፉ እየተሰፋ የሚሠራ ሳይሆን ድርና ድርን ወይም ዘሐና ዘሐን በማዋሐድ የሚሠራ ልብስ ነው። ይህ ልብስ ከተሰፋው ልብስ ይልቅ ጽኑ ነው። የድሩና የድሩ ተዋሕዶም ከተሰፋው ይልቅ የጸና ነው። ኢየሱስ ክርስቶስም በዚህ መመሰሉ የቃልና የሥጋ ተዋሕዶ ጽኑ መሆኑን ያመለክታል።

**፻፷፰. ልብሱን በወይን ያጥባል፣ መጎናጸፊያውንም በፍሬ ደም የሚያጥብ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ሲል ምን ለማለት ነው?**

መልስ፦ ይህ በብሉይ ኪዳን ለይሁዳ ወልደ ያዕቆብ የተነገረ ቢሆንም በትንቢት ለክርስቶስም እንደሆነ ተነግሯል። ልብሱን በወይን ያጥባል ማለት ሰውነቱ በዕለተ መስቀል በደም እንደሚታለል ያመለክታል። መጎናጸፊያውን በፍሬ ደም ያጥባል ሲል መጎናጸፊያ የተባሉ ምእመናን ናቸው። ምእመናንን በሥጋው በደሙ ያከብራል ማለት ነው (ዘፍ.49፥10-12 አንድምታ ትርጓሜ)።

**፻፷፱. ጭቃና ኩስ የሆንክ የሰው ልጅ ሆይ ራስህን ለምን ከፍ ከፍ ታደርጋለህ ሲል ምን ለማለት ነው?እግዚአብሔር ሰውን አክብሮ ሠራው ከሚለው ጋር እንዴት ይታረቃል? ሰው ግን ከንቱን ይመስላል ሲልስ ሰው የክብሩ ወራሽ አይደለም ወይ ለምን እንዲህ አለ?**

መልስ፦ እውነት ነው እግዚአብሔር ሰውን በአርአያው አክብሮ ፈጥሮታል (ዘፍ.1፥26-27)። የሰው ልጅ ግን ይህን ክብሩን ጠብቆ መኖር ሲገባው ባለመጠበቁ ከክብሩ ወርዶ እንደ እንስሳ ሆነ ተብሏል። "ወዕጓለ እመሕያውሰ እንዘ ክቡር ውእቱ ኢያእምረ። ወኮነ

ከመ እንስሳ ዘአልቦ ልብ ወተመሰሎሙ" እንዲል (መዝ.48፥20)። በመሆኑም በምንረግጠው ጭቃና ኩስ ተመስሏል። ከንቱም ተብሏል። ምንም እንኳ በምጽአት ተነሥተን ለዘለዓለም በደስታ በመንግሥተ ሰማያት ብንኖርም በዚህ ምድር ያለን ሕይወት ግን አጭርና የተናቀ በመሆኑና ሥጋችንም በዚህ ዓለም ሳለ እስከ ምጽአት በስብሶ የሚቀር በመሆኑ ቅዱስ ያሬድ በጭቃ በኩስ መስሎ ተናግሮታል።

፻፴. ወርቅና ብር የእኔ ነው ለወደድኩት እሰጠዋለሁ ሲል ምን ለማለት ነው? ብርን አትውደዱ ከሚለው ጋር እንዴት ይታረቃል?

መልስ፦ በዚህ ምድር ያለ አካል ያለው ነገር ማንኛውም በተፈጥሮ የእግዚአብሔር ገንዘብ ነው። ወርቅና ብር የእኔ ነው ያለውም በተፈጥሮ ባለቤቱ እርሱ እግዚአብሔር በመሆኑ ነው። እግዚአብሔር ለፈቀደውም ይሰጠዋል። ብርን አትውደዱ ማለቱ ብር አያስፈልግም ተብሎ አይተረጎምም። ብርን አትውደዱ ማለት ከእግዚአብሔር በላይ አታምልኩት ማለት ነው። በብር አትመኩበት ማለት ነው እንጂ። ስለዚህ ምንም የሚጣላ ነገር የለውም።

፻፴፩. እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን ማረፊያዬ ይላታል ሲል ምን ማለት ነው? እግዚአብሔር ይወሰናል ወይ?

መልስ፦ እግዚአብሔር በአካል በሁሉ ቦታ ያለ ነው። በዓለም ሁሉ የሚኖር ዓለምን የሚተርፋት እንጂ የማትተርፈው አምላክ ነው። ቤተክርስቲያንን ማረፊያዬ ማለቱ ግን የጸጋው ግምጃ ቤት በመሆኗ ነው። ረድኤቱን፣ ጸጋውን የሚሰጥበት የተለየች ቦታ በመሆኗ ነው። እግዚአብሔር ጸጋውን በማንኛውም ቦታ በማንኛውም ጊዜ በማንኛውም ሁኔታ መስጠት ቢችልም የበለጠ እርሱ ራሱ ፈቅዶ የሚሰጥባት በመሆኗ ቤተክርስቲያንን ማረፊያዬ ብሏታል (1ኛ ነገ.9፥3)።

፻፴፪. በሰንበት ቀን ቤተክርስቲያንን ምስጋና ይከባታል ሲል ምን ማለት ነው? ሌሎች ቀን ምስጋና የላቸውም ማለት ነው?

መልስ፦ ይህ ዓይነቱ አገላለጽ በጸናው መናገር ይባላል። ከሰባቱ ዕለታት በተለየ ሰው ሁሉ ወደእርሷ ተሰብስቦ እግዚአብሔር የሚያመሰግንባት ዕለት ሰንበት ናት። ምንም እንኳ በሌላው ቀንም ምስጋና ቢኖርም በሰንበት ያለው ምስጋና ግን ብዙ በመሆኑ ይህንን ለመግለጽ በሰንበት ቤተክርስቲያንን ምስጋና ይከባታል ተብሏል።

፻፴፫. ሰንበትን መላእክት በሰማያት ጻድቃን በገነት ያከብሯታል። ባሕር፣ ዓሣዎች፣ አናምርትና ፍጥረታት ሁሉ ያከብሯታል ሲል ምን ለማለት ነው?

መልስ፦ ባሕርና ሌሎችም ግዑዛን ፍጥረታት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል ማለት በእነርሱ ምክንያት እግዚአብሔር ይመሰገናል ማለት ነው እንጂ አፍ አውጥተው

ያመሰግኑታል ማለት አይደለም (መዝ.18፥1)። ዓሣዎች፣ አናምርት፣ አናብስትና ሌሎችም ደማውያን ፍጥረታት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል ማለት ደግሞ እርሱ እግዚአብሔር በሚያውቀው እኛ በማንረዳው መልኩ ያመሰግኑታል ማለት ነው።

**፻፴፬. ቤተክርስቲያንን የንስር ዐይን ያላያት ሲል ምን ማለት ነው? በሰማይ ላለው አርአያ ናት ሲባልስ እንዴት ነው?**

መልስ፦ ቤተክርስቲያን በሰማይ ላለው አርአያ ናት ማለት በሰማይ 24ቱ ካህናተ ሰማይ፣ አራቱ ኪሩቤል፣ ሌሎችም መላእክት በየመዓርጋቸው እንዳሉና እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግኑ ሁሉ በቤተክርስቲያን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናትና ምእመናን በየመዓርጋቸው እግዚአብሔርን ያመሰግኑታልና ነው። ኪሩቤል የሊቃነ ጳጳሳት፣ ሱራፌል የጳጳሳት፣ አጋእዝት የኤጲስ ቆጶሳት፣ ኀይላት የቆሞሳት፣ አርባብ የቀሳውስት፣ መናብርት የዲያቆናት፣ ሥልጣናት የንፍ*/ቀ ዲያቆናት፣ ሊቃናት የአናጕንስጢሳውያን፣ መኳንንት የመዘምራን፣ መላእክት የዐፀውተ አናቅጽ ምሳሌ ናቸውና (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 9 አንድምታ ትርጓሜ)። የንስር ዐይን ያላያት ሲል ንስር የተባለ ዲያብሎስ ነው። ዲያብሎስ ያላሳሳታት ቤተክርስቲያን ማለት ነው። አንድም በምስጢር ቤተክርስቲያን የተባለች መንግሥተ ሰማያት ናት። ዲያብሎስ ያላያት መንግሥተ ሰማያት አለች ማለት ነው። "ወፍኖት ዘኢርእያ ያፍ ወኢነጸራ ዐይነ ንስር። ወኢኬድዋ ደቂቅ ዝኁራን" እንዲል (ኢዮ.28፥7-8)።

**፻፴፭. ልጅ የወጣትነት ሥራን ተዋት የሚለው ምኑን ነው?**

መልስ፦ ወጣትነት የሚባለው የእሳት ባሕርይ የሚሰለጥንበት ወቅት ነው። በዚህ ጊዜ ብዙው ወጣት በዝሙትና በሌሎችም ኃጣውዕ ይፈተናል። ስለዚህ እኒህን በመሳሰሉ ኃጢአቶች አትውደቅ ለማለት የወጣትነትን ሥራ ተው ተብሏል። በበዛው መናገር እንጂ በወጣትነታቸው የጽድቅ ሥራን የሠሩ ደጋግ አባቶችም ነበሩ፣ አሉ፣ ይኖራሉ።

**፻፴፮. ዘገብሮ ለሰብእ በአርአያ ዚአሁ ይላል። አርአያና አምሳል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ አምሳልና አርአያ አንድ ወገን ነው። በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል ተፈጥረናል ማለት እግዚአብሔር በባሕርዩ የሚገዛውን ፍጥረት የሰው ልጅ ደግሞ በጸጋ ይገዛዋልና ነው (ዘፍ.1፥26 አንድምታ ትርጓሜ)።

**፻፴፯. ብሔረ ሕያዋንና ብሔረ ብፁዓን ልዩነቱ ምንድን ነው?**

መልስ፦ ብሔረ ሕያዋን የሚባለው ከዚህ ምድር ያረጉ እነ ነቢዩ ኤልያስ፣ እነ ሄኖክና ሌሎችም እስከ ምጽአት ድረስ ይኖሩበት ዘንድ የተሰጠ ቦታ ነው። ብሔረ ብፁዓን ደግሞ እንደእኛ የሚጋቡ፣ የሚዋለዱ፣ የሚሞቱ ሰዎች የሚኖሩበት ቦታ ነው። ቢሆንም ግን ክፋት የሌለበት ደጋጎች ብቻ የሚኖሩበት ዓለም ነው።

፻፹፰. ሀለዉ ዕደው እለ ኢጥእምዎ ለሞት ይላል፡፡ እነ ኤልያስ እነ ሄኖክ ወዘተርፈ ሕያዋን ናቸውና ጥምቀታቸው መቼ ተፈጸመ?

መልስ፦ መቼ እንደተጠመቁ የሚገልጽ ምንም ዓይነት መረጃ ሰምቼ አላውቅም፡፡ ስለዚህ የዚህን መልስ አላውቀውም፡፡

፻፹፱. አናንያ፣ አዛርያ፣ ሚሳኤል ፊታቸውን በትእምርተ መስቀል አማተቡ ሲል አሁን እኛ በጣታችን እንደምናማትበው ያለ ነው ወይስ ሌላ ትርጉም አለው?

መልስ፦ ይህንን ታሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ አላገኘሁትም፡፡ ቅዱስ ያሬድ አማተቡ ብሏል፡፡ ዝርዝር ታሪኩን መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከተጻፈው ውጭ አላውቀውም፡፡ [ምናልባት የመስቀል ምልክት በመላእክት ዓለምም ይታወቅ የነበረ ስለሆነ ገብርኤል በመካከላቸው ሲቆም የእርሱን የመስቀል ምልክት ለእነርሱ አድሎ ተናግሮ ይሆን? እኔ እንጃ ዙሮ ዙሮ አላውቀውም]፡፡

፻፺. ነቢያት ሰበኩት ምስክርም ሆኑት ወላዲ አብንም እጅህን ላክ አሉት ሲል ምን ማለት ነው? እጅህን ላክ ሲል ምንድን ነው?

መልስ፦ ወልድ የአብ ክንድ፣ የአብ ኀይል፣ የአብ እጅ...ወዘተ እየተባለ ይጠራል፡፡ እጅ ከሰውነታችን ሳይለይ የወደቀን አንሥቶ እንደሚመለስ ሁሉ ወልድም ከአብ ህልውና ሳይለይ ሰውነትን ገንዘብ አድርጎ የሰው ልጆችን አድኗልና እጅ፣ ክንድ ይባላል፡፡ ስለዚህ ከሞት፣ ከባሕርይ ጕስቁልና ያድነን ዘንድ ልጅህን ላክ እያሉ ነቢያት ትንቢት ይናገሩ እንደነበር ቅዱስ ያሬድ ገልጾልናል፡፡

፻፺፩. ከዓለም ደስታ የራቀ ክቡር ኤልያስ በንጽሕናና በቅድስና የሥጋውን ቤት ሠራ ይላል፡፡ የሥጋውን ቤት ሠራ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ የሥጋውን ቤት ሠራ ቅኔያዊ አነጋገር ነው፡፡ ምስጢሩ ሰውነቱን በንጽሕናና በቅድስና አስጌጠ ማለት ነው፡፡

፻፺፪. ኤልያስ ለእግዚአብሔርም የሰላም መሥዋዕትን አቀረበ ይላል፡፡ የሰላም መሥዋዕት የሚለው ምንድን ነው?

መልስ፦ የሰላም መሥዋዕት የሚባለው ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የደኅንነት መሥዋዕት ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ሰዎች ኃጢአት ስለሠሩ ኃጢአታቸው ይሠረይ ዘንድ የሚያቀርቡት የኃጢአት መሥዋዕት ነበረ፡፡ ይህ የኤልያስ መሥዋዕት ግን ከኃጢአት መሥዋዕት የተለየ የእግዚአብሔርን አምላክነት ለሌሎች ለማሳወቅ የተደረገ መሥዋዕት ስለሆነ የሰላም መሥዋዕት ተብሏል፡፡

**፻፵፫. ኤልያስና ዮሐንስ የፍየል ሌጦዎችን ይታጠቃሉ። ኤልያስና ዮሐንስ ኑሯቸውም በገዳም ነው። በወገባቸው መታጠቂያ አለ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ዮሐንስና ኤልያስ በቁመ ልብሳቸው የፍየል ቆዳ (ሌጦ) ነበር ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ መታጠቂያን ይታጠቁ ነበር። ኑሯቸው በገዳም ነበር መባሉ ብዙ ጊዜያቸውን ያሳለፉት በዱር ስለነበረ ይህንን ለመግለጽ ነው።

**፻፵፬. ኤልያስ በጸሎቱ ከሰማይ ዝናምን አዘነመ እና ለጎመ ሲል ምን ለማለት ነው? አዘነመና ለጎመ እንዴት ይታረቃሉ?**

መልስ፦ ነቢዩ ኤልያስ መጀመሪያ እስራኤላውያን በመበደላቸው ምክንያት ዝናም እንዳይዘንብ ጸልዮ ሰማይን ከልክሎታል። በኋላ ደግሞ የሰውን መቸገር አይቶ እንደገና ዝናብ ይዘንብ ዘንድ ጸልዮ አዝንቧል።

**፻፵፭. ኤልያስ በእሳት ፈረስ ሠረገላ ወደ ሰማይ ዐረገ ይላል። የእሳት ፈረስ እና ሠረገላ ምንድን ናቸው?**

መልስ፦ በእሳት ፈረሶች የሚጎተት ሠረገላ ኤልያስን ወደሰማይ አሳርጎታል። ያ ሠረገላና የእሳት ፈረሶቹ ከየት እንደመጡና ምን እንደሆኑ ግን ዝርዝር ጉዳይ አላገኘሁም።

**፻፵፮. ገብርኤል ማለት ከሚለው መጀመርያ ሰው የሆነ አምላክ ነው የሚባለው ወይስ አምላክ የሆነ ሰው? ማለቴ ቅደም ተከተሉ አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ ነው የሚባለው ወይስ እንዴት ነው?**

መልስ፦ ብእሲ ወአምላክ ሲል "ወ" ቅጽል ናት። ስለዚህ አምላክ የሆነ ሰው ተብሎ ይተረጎማል። አምላክ ወሰብእ ሲል ደግሞ ሰው የሆነ አምላክ ማለት ነው። እንዲሁም "ወ" ዋዌ ሆና "ም" ተብላ ትተረጎማለች። ስለዚህ ብእሲ ወአምላክ ሲል ሰውም አምላክም ተብሎ ይተረጎማል። ምሥጢሩ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆኑን ያመለክታል። አምላክ ሰው ሲሆን በዚያው ቅጽበት ሰው አምላክ ሆኗል። ስለዚህ መቀዳደም ስለሌለ በሁለቱም ቢገለጽ ይሆናል። በትርጓሜያችን እንደምንገልጸው የተዋሕዶው ጀማሪ ቃል ነው። "ቃል ሽቶ ተዋሕዷል እንጂ ሥጋ አልተዋሐደምና" እንዲል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ትርጓሜ)። ይህም ማለት ከተዋሕዶ በፊት ሥጋ እኔ ባይ አልነበረም ከተዋሕዶ በፊት እኔ ባይ የነበረ ቃል ነው ማለት ነው። ከተዋሕዶ በፊት ሥጋ እኔ ባይ ነበረ ካልን ግን ኀድረት የሚል ክሕደትን ያመጣል። የሆነ ሆኖ በጊዜ ተዋሕዶ ግን አምላክ ሰው፣ ሰው አምላክ ሲሆን መቀዳደም ስለሌለ በሁሉም መገለጽ ይችላል።

**፻፵፯. ኃጢአትን ይቅር የሚል የአንበሳ ልጅ አንበሳ ወልድ ተወለደ ሲል ምን ለማለት ነው?**

መልስ፦ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ በተለዋጭ ዘይቤ መግለጽ የተለመደ ነው። ለምሳሌ ዳን ወልደ ያዕቆብ የአንበሳ ልጅ ተብሎ ነበር (ዘዳ.33፥22)። ቅዱስ ያሬድ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስን የአንበሳ ልጅ አንበሳ ብሎታል። በዚህ አገላለጹ አብንም አንበሳ ብሎታል ማለት ነው። አንበሳ የማይፈራ፣ ኀዱዕ (ጸጥ ያለ) ነው። እግዚአብሔርም በባሕርዩ ፍርሀት የሌለበት ጥቡዕ፣ ብንበድል ቻሉሎ የማያጠፋን ኀዱዕ በመሆኑ አንበሳ ተብሏል። ይህ የአንበሳ አብ ልጅ አንበሳ ወልድ ከድንግል ማርያም በሥጋ ተወለደ ማለት ነው።

፻፺፰. እመቤታችን ቤተ መቅደስ ገብታለች (ኖራለች) ስንል በብሉይ ኪዳን ሴቶች ወደ ቤተ መቅደስ ይገቡ ነበር?

መልስ፦ ቤተ መቅደስ የሚባለው ሰሎሞን ያሠራው ቤተ እግዚአብሔር ነው። ይህም ሕንፃውንም በዙሪያው ያሉ ቤቶችንም ቤተ መቅደስ ማለት የተለመደ ነው። አሁን ከቅጽረ ቤተክርስቲያን ውስጥ ከሕንፃ ቤተክርስቲያን በተጨማሪ የመቃብር ቤት፣ የፍትሐት ቤት፣ ደጀ ሰላም፣ ቤተልሔምና የመሳሰሉት እንዳሉ ያን ጊዜም በቤተ መቅደስ ዙሪያ ሌሎች ቤቶች ስለነበሩ ድንግል ማርያም በዚያ ትኖር ነበር ለማለት ነው እንጂ ሊቀ ካህናቱ በዓመት አንድ ጊዜ ከሚገባበት ቅድስተ ቅዱሳን ወይም ሌዋውያን ካህናት ከሚያመሰግኑበት የመቅደሱ ክፍል ትኖር ነበር ለማለት አይደለም። ዙሪያውን ሌሎችም ይኖሩ እንደነበረ ማስረጃው "ከአሴር ወገንም የምትሆን የፋኑኤል ልጅ ሐና የምትባል አንዲት ነቢይት ነበረች። እርሷም ከድንግልናዋ ጀምራ ከባልዋ ጋር ሰባት ዓመት ኖረች። እርሷም ሰማንያ አራት ዓመት ያህል መበለት ሆና በጣም አርጅታ ነበር። በጾምና በጸሎትም ሌሊትና ቀን እያገለገለች ከመቅደስ አትለይም ነበር" የሚለው ነው (ሉቃ.2፥36-37)። በእርግጥ ብትገባም ያንስባታል እንጂ አይበዛባትም ነበር። አማናዊት መቅደስ እርሷ ራሷ ናትና። ሰሎሞን በሠራው ቤተመቅደስ እግዚአብሔር በረድኤት ያድር ነበር። በታላቂቱ ቤተ መቅደስ በድንግል ማርያም ግን ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ሰው ሆኖ ከረድኤት በበለጠ በከዊን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ኖሮባታልና።

፻፺፱. ገብርኤል ማርያምን እንዲያበሥራት የተደረገ በምን ምክንያት ነው?

መልስ፦ ይህ በትርጓሜ በትውፊት እንደሚነገረው በመላእክት ዓለም ሳጥናኤል አምላክ ሳይሆን አምላክ ነኝ ብሎ ሁከት በፈጠረ ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል አምላካችንን እስክናገኘው ድረስ በያለንበት እንቁም ብሎ መላእክትን በማረጋጋቱ "ሑር አብሥራ ለወለተ ሐና። ሒድ የሐናን ልጅ ማርያምን የደስታ ዜና ንገራት" ተብሎ እንደተነገረ ተጽፏል (አክሲማሮስ አንድምታ)።

፪፻. ማርያም ግን ይህን ሁሉ ትጠብቀው ነበር ይላል። የምትጠብቀው ምንን ነው?

መልስ፦ ቅዱስ ያሬድ ማርያም ግን ይህንን ሁሉ ትጠብቀው ነበር ያለውን "ዝኬ ውእቱ ገብርኤል ዘዜነዋ ጥዩቀ" ብሎ አጉልቶታል። ይኸውም ገብርኤል የነገራትን ነው ብሎታል። ትወልጃለሽ ያላትን ከገብርኤል ሰምታ ለሌላ ልናገረው አላለችም ነገሩን አስተውላ በልቧ በምሥጢር ትጠብቀው ነበር ማለት ነው። አረጋዊ ስምዖን ስለጌታ የተናገረውን ትንቢትም ሰምታ በልቧ ታስተውለውና ትጠብቀው ነበር። ምሥጢር ጠባቂነትን ከእርሷ እንማራለን (ሉቃ.2፥19)።

**፻፶፩. ቅዱስ ገብርኤል አበሠራት ይላል። በሌላ በኩል ደግሞ ደራሲው "እግዚአብሔር እግዚእ ሶበ ለገብርኤል ተመሰሎ" ይላል። አይቃረንም?**

መልስ፦ አይቃረንም። በሁለቱም ያስተረጉማል። አንደኛው ገብርኤል የላኪውን የእግዚአብሔርን ሐሳብ ስለተናገረ በገብርኤል አድሮ የተናገረ ራሱ እግዚአብሔር ስለሆነ እግዚአብሔር ገብርኤልን መስሎ ተናገራት ማለት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ምንም ከእግዚአብሔር ተልኮ ቢናገርም ተናጋሪው ገብርኤል ስለሆነ ገብርኤል አበሠራት ተብሏል።

**፻፶፪. ድንግል ማርያም ገብርኤልን ቃልህን አሰማኝ ድገምልኝ ድገምልኝ አለችው ይላል። ምን ማለት ነው? ገብርኤል ሲያበስራት እንደዚያ ብላው ነበር?**

መልስ፦ በመጽሐፍ ቅዱስ ይህ አልተገለጸም። በትውፊት ግን እንዲሁ ትወልጃለሽ ሲላት ቃሉን ለመረዳት ደግማ እንደጠየቀችው ይነገራል። ድገምልኝ ድገምልኝ የሚለው ለዚህ ነው። በሌላ መልኩ የመጽሐፍ ቅዱሱን ሐሳብ በሌላ አገላለጽ የቀረበ ሆኖም እናገኘዋለን። ትወልጃለሽ ሲላት እንዴት ይሆናል ብላ መጠየቋ ነገሩን የበለጠ እንዲገልጽላት በመሆኑ ይህንን ድገምልኝ በሚል አገላለጽ ቅዱስ ያሬድ ጽፎታል (ሉቃ.1፥34-38)።

**፻፶፫. ክብሮሙ ለመላእክት ከመ መንኰራኵር ወረደ ይላል። የከመ ንጽጽር እዴት ነው?**

መልስ፦ መንኰራኵር የሚለው የሠረገላ ተሽከርካሪው ክፍል (እንደ ጎማ ያለው) ነው። ተጎታቹ ከቦታ ቦታ የሚሔድ በመንኰራኵር አማካኝነት ነው። የመላእክት ክብራቸው እግዚአብሔር እንደ መንኰራኵር ወረደ ማለት ነው። መንኰራኵር ፈጣን እንደሆነ ቀጠሮው እንደደረሰ እግዚአብሔር ፈጥኖ ሰው ሆነ ማለት ነው።

**፻፶፬. ገብርኤል ማለት አምላክ የሆነ ሰው ማለት ነው ሲል ምን ማለት ነው? ገብርኤል አምላክ ነው ወይ?**

መልስ፦ የመላእክት ስም የእግዚአብሔርን ግብረ ባሕርይ የሚገልጽ ነው። ለምሳሌ ዑራኤል ማለት ብርሃነ እግዚአብሔር/ የእግዚአብሔር ብርሃን ማለት ነው። ገብርኤል የሚለው ስም ደግሞ አምላክ የሆነ ሰው ማለት ነው። አንድም እግዚእ ወገብር ሰው

የሆነ አምላክ ማለት ነው። በአጭሩ ስማቸው የእግዚአብሔርን ግብረ ባሕርይ የሚያመለክት ነው እንጂ ራሳቸው አምላክ ናቸው ማለት አይደለም። ስለዚህ ገብርኤል አምላክ አይደለም።

**፻፶፭. ድንግል ማርያም ሐርን ለደብተራ እየፈተለች ወርቅን እየፈተለች ገብርኤል የፍቁር ወልድን መምጣት አበሠራት ይላል። ለመሆኑ ሐር እና ወርቅ ምንድን ነው? ወርቅስ እንዴት ሊፈተል ይችላል?**

መልስ፦ ደብተራ ያላት ቤተ መቅደስን ነው። ይኸውም ቤተ መቅደስ በደብተራ ኦሪት ስለተተካች ነው። አሁን ያሉ እናቶቻችን አክርማውን ቀጭተው፣ ሰበዝ ሰብስበው አገልግል ሙዳይ ሰፍተው ለቤተክርስቲያን እንደሚሰጡ ሁሉ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም ለቤተ መቅደስ ሐርንና ወርቅን እያስማማች ትፈትል ነበር ማለት ነው። አሁን በልብሶቻችን ወርቅና ልዩ ልዩ መዓድናትን እያደረግን እንደምንሰፋው ሁሉ ድንግል ማርያምም በሐሩ ላይ ወርቅን እንደጌጥ እያደረገች ትሰፋው ነበር። ወርቅ በቁሙ ወርቅ ነው። ሐር የሚባለው ደግሞ ጥጥ የመሰለ የሐር ትል የሚባል ትል ሸረሪት ድርን እንደምትሠራው እንደ ድር የሚሠራው ነው።

**፻፶፮. በምድር ላይ ሁሉ የደስታ ቃልን የሚናገር ገብርኤል ወደ ገሊላ ሀገር ወደ ማርያም መጣ ሲል ምን ማለት ነው? ገብርኤል የቁጣ ቃል አይናገርም ወይ?**

መልስ፦ በቅዱሳን መላእክት ኀዘን፣ ብስጭት፣ ቁጣ የለባቸውም። መጽሐፍ ቅዱስና አዋልድ መጻሕፍት የመላእክትንና የእግዚአብሔርን ሥራ በሚናገሩ ጊዜ ለሰው ቅርብ በሆነ ቋንቋ ለመግለጽ በሰውኛ ምሳሌ (Metaphorical expression) ይናገራሉ። በዚህ አግባብ ፍርዳቸውን፣ ቅጣታቸውን ለመግለጽ ይቆጣሉ ተባለ እንጂ በመላእክት ዘንድ ቁጣና ብስጭት የለም። በቅዱሳት ነፍሳትም እንዲሁ ነው። ዓለሙ ሁሉ መስማት የሚፈልገውና ቢሰማው የሚያስፈልገው ዜና ነበር። ይህ ዜናም የአምላክ ሰው መሆን ነው። ይህንን ታላቅ ዜና ለሰው ልጆች በመናገሩ ገብርኤል መልአከ ፍሥሓ ይባላል። በምድር ላይ ሁሉ የደስታ ቃልን የሚናገር የተባለበት ምክንያት የክርስቶስ ሰው መሆን ለምድር ሁሉ ደስታ ስለሆነ ይህንን የምሥራች ደግሞ ገብርኤል ስለተናገረው ነው።

**፻፶፯. ማርያምን ሚካኤል መልአክ በክንፉ ተሸከማት ሲል ምን ማለት ነው? ረቂቅ (ሚካኤል) እና ግዙፍ (ማርያም) እንዴት ነው?**

መልስ፦ ረቂቃን መላእክት ግዙፍን የመሸከም አቅም ወይም ኀይል አላቸው። ረቂቁ እግዚአብሔር ግዙፉንም ረቂቁንም ዓለም ይዞት እንደሚኖር የታወቀ ነው። ስለዚህ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ድንግል ማርያምን በክንፉ ይይዛት ነበር ማለት ነው። ጠባቂ መልአኳ እርሱ ቅዱስ ሚካኤል ነበርና።

፻፶፰. ወገቡም ጭኑም በአፌዝ ወርቅ [ያሸበረቀ] ገብርኤል የሚባል አንድ መልአክ አለ ይላል፡፡ ኤፌዝ ወርቅ ምንድን ነው? ምስጢሩስ ምንድን ነው?

መልስ፦ አፌዝ ወርቅ የሚገኝበት የወርቅ ቦታ ነው፡፡ የአፌዝ ወርቁ ጽሩይ ንጹሕ እንደሆነ ሁሉ የገብርኤል ወገቡና ጭኑ በአፌዝ ወርቅ ያሸበረቀ ነው ማለት ረቂቅ አካሉ ጽሩይ ንጹሕ ነው ማለት ነው እንጂ ለገብርኤል ግዙፍ የወርቅ ልብስ አለው ለማለት አይደለም፡፡

፻፶፱. ኢሳይያስ ሐዳስዩ ጣዕዋ አላት ይላል፡፡ ግን ከኢሳይያስ አላገኘሁምና የት አለ? ይቤላ ስንል እንዴት ነው? ለምሳሌ ጽንዕት ምድር ዘኢሳይያስ ጸምር ዘጌዴዎን መሰንቆ ዘዳዊት ጽርሕ ዘሚልክያስ ትባላለች፡፡ እነርሱ ስላሏት ነው ወይስ ሊቃውንት በእነርሱ ምሳሌ ሰለመሰሏት?

መልስ፦ እኔም ነቢዩ ኢሳይያስ ድንግል ማርያምን ሐዳስዩ ጣዕዋ ያለበትን ቦታ አላገኘሁትም፡፡ አላት የሚለው ግን የሊቃውንት ትርጓሜ ነው፡፡ ሊቃውንት በብሉይ ኪዳን የተደረገውን ድርጊት መሠረት አድርገው ከአሁኑ ጋር ምሳሌ አድርገው ይናገራሉ፡፡ ይህ መንገድ ራሱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ ነውና፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በኦሪት ለእስራኤል ውሃ ያፈልቅላቸው የነበረውን ድንጋይ ያ ድንጋይ ክርስቶስ ነው ብሎ እንደተረጎመው (ዘፀ.17፥6፤ 1ኛ ቆሮ.10፥4)፡፡ በዚህ አግባብ ነቢያት በዘመናቸው ለሆነ ድርጊት የተናገሩትን ሊቃውንት ልክ እንደ ጳውሎስ ምሥጢሩን አይተው በሐዲስ ኪዳን ለተከናወነ ድርጊት ይጠቅሱታል፡፡ ሲጠቅሱም ይቤ፣ ይቤላ፣ ይቤሉ ማለታቸው የሐሳቡ ምንጭ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው፡፡

፻፷. መድኀኒታችን በተድላ መለኮት ተወለደ ይላል፡፡ ተድላ መለኮት ማለት ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ተድላ ማለት ምቾት፣ ደስታ፣ ሥልጣን፣ መገባት ማለት ነው፡፡ ስለዚህ መድኀኒታችን በተድላ መለኮት ተወለደ ማለት በመለኮት ሥልጣን ተወለደ ማለት ነው፡፡ ይህንን የመሰለ በቅዳሴ ተጽፏል፡፡ "ወረደ እንዘ ኢየዐርቅ በተድላ መለኮት" እንዲል (ቅዳሴ ጎርጎርዮስ)፡፡ ለመለኮቱ በሚገባ መንገድ ወይም ለመለኮቱ በሚመች መንገድ ተወለደ ማለት ነው፡፡ ለመለኮቱ የሚገባ የሚመች ማለት መለኮት በዘመን ብዛት አይለወጥም፡፡ ስለዚህ መለኮት መለወጥ ሳይኖርበት [እንበለ ውላጤ] ሰው ሆነ ማለት ነው፡፡ በሥልጣኑ ሳለ ሰውነትን ገንዘብ አድርጎ ተወለደ ማለት ነው፡፡

፻፷፩. ነአምን አበ ፈናዌ ወልደ ተፈናዌ መንፈሰ ቅዱሰ ማሕየዌ ዐቢየ ኖላዌ ሰማያዌ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ይህ አብ ፈናዊ፣ ወልድ ተፈናዊ፣ መንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ እንደሆነ እናምናለን ማለት ነው፡፡ አብ ፈናዊ፣ መንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ መባላቸው ግብረ ባሕርይ ነው፡፡ ይህም የወልድ ሰው መሆን የአብም ፈቃድ መሆኑን ለመግለጽ ፈናዊ ተብሏል፡፡ ማሕየዊ የሚለው የሚያድን ወይም የሚያኖር ተብሎ ይተረጎማል፡፡ ይህም ከዚህ ላይ

ተለይቶ ለመንፈስ ቅዱስ ቢነገርም በማሕየዊነት ሦስቱ አካላት አንድ ስለሆኑ ወልድንም አብንም ይመለከታል። ሦስቱም አካላት ነባቢ፣ አንባቢ፣ ለባዊ፣ አለባዊ፣ ሕያው፣ ማሕየዊ ይባላሉና። አንባቢ፣ አለባዊ፣ ማሕየዊ ለፍጡራን ስለሆነ አፍኣዊ ግብር (ግብረ ባሕርይ) ነውና። ወልድ ተፈናዊ መባሉ በተለየ አካሉ ሰው የሆነ እርሱ በመሆኑ ነው። ሰው መሆኑን መላክ ብሎታል። ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ላይ አብ በተለየ አካሉ ፈናዊ ይባላል የሚለው ግብረ ባሕርይን ለየአካላቱ አድሎ መናገር ልማደ መጽሐፍ ስለሆነ ነው። አብ አምላክ እንዲል።

**፻፳፪. ጌና ማለት ምን ማለት ነው? የታኅሣሥ28 ልደት እውነት ነው? እውነት ከሆነ 7ኛው ጳጉሜን በሆነበት ዘመን ታኅሣሥ 27 ዕለት ልናውለው ልናከብረው ነው? 6ኛይቱ ጳጉሜን መያጢተ በዓል ከሆነች ስለምን የክርስቶስ ልደት ብቻ መለሰች? ልደት በ28 ሲውል ጌና በ27 ይሆናል ማለት ነው? ልደት፣ ገና፣ ጌና ልዩነታቸው ምንድን ነው?**

መልስ፦ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ገና ወይም ጌና ማለት ልደት ማለት እንደሆነ ገልጸዋል። አዎ በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ልደት ታኅሣሥ 28 ይከበራል። ይህም የሊቃውንት የሥርዓት ብያኔ ነው። የካቲት 23 ይውል የነበረውን የቃና ዘገሊላ በዓል የውሃን በዓል ከውሃ በዓል ለማያያዝ በማለት ጥር 12 ቀን እንዲከበር አድርገዋል። በዚሁ መሠረት የገና በዓልም ጳጉሜን 5 ዕለተ መድኀኒት፣ ዕለተ ምርያ ትባላለች። እርሷ በዋለችበት ቀን ገና እንዲውል ሥርዓት ስለሠሩ በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ታኅሣሥ 28 ይሆናል። ታኅሣሥ 28 ቀን ገና መባሉም ስለዚህ ነው። በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ይውልበታልና። የውሃን በዓል ከውሃ በዓል ብለን ለይተን ቃና ዘገሊላን ከየካቲት 23 ወደ ጥር 12 እንዳመጣነው ሁሉ ዕለተ መድኀኒትን ከዕለተ መድኀኒት ለማያያዝ ከሌሎች ለይተን ገናን ብቻ ጳጉሜን 5 በዋለችበት ዕለት እናከብረዋለን። ሌላው በነበረበት ይከበራል። [በነገራችን ላይ ይህ ሥርዓት ስለሆነ በቅዱስ ሲኖዶስ ሊሻሻልም ይችላል]። ምንም እንኳ በስድስት መቶ ዓመት አንድ ጊዜ ጳጉሜን ሰባት ብትመጣም በቀመር ብቻ ሰባት ትሆናለች ተብላ ትነገራለች ታስባ ትውላለች እንጂ በመደበኛው ስድስት ቀን ብቻ ተደርጋ ስለምታልፍ በዓለ ልደትን ወደ ታኅሣሥ 27 አታወርደውም።

**፻፳፫. ሰብአ ሰገልን በቅድስና ሕይወት ነው የምንይዛቸው? ከውዳሴ ማርያም ዘዓርብ ትርጓሜ ኮከብ ብሩህ ዘነጸርዎ ቅዱሳን ይልና ሰብአ ሰገል ካለ በኋላ ቅዱሳንን ጽኑዓን ሲል ነው ይላል።**

መልስ፦ ሰብአ ሰገል ቅዱሳን ናቸው የሚል የለም። እንዲያውም ለጌታ እጅ መንሻ አቅርበው ሲመለሱ ድንግል ማርያም ምግብ [የገብስ ዳቦ] ሰጥታ ሸኝታቸው ነበር (ተአምረ ኢየሱስ)። በኋላ ሀገራቸው ከገቡ በኋላ በእሳት የሚያመልኩ ሆነዋል። እንደገና ሐዋርያው ናትናኤል አስተምሮ አጥምቋቸዋል (ማቴ.2፥11 አንድምታ ትርጓሜ)። ኮከብ ብሩህ ዘነጸርዎ ቅዱሳን ያለውም "ቅዱሳንን" ጽኑዓን፣ ኀያላን ብሎ መተርጎሙ ስለዚህ ነው።

፻፷፬. ሰብአ ሰገል ስለክህነቱ ዕጣን ስለመንግሥቱ ወርቅ ስለሞቱ ከርቤን አመጡለት ይላል። የጌታ መንግሥት ከወርቅ፣ ሞቱ ከከርቤና ክህነቱ ከዕጣን ምን ያገናኘዋል?

መልስ፡- ለንጉሥ ወርቅ እንደሚገበር ሁሉ ክርስቶስንም ንጉሠ ሰማያት ወምድር ነህ ሲሉ ወርቅ ገብረውለታል። ካህን ዕጣን አጥኖ ሰውን ከእግዚአብሔር እንደሚያቀርብ ሁሉ ሰውንና እግዚአብሔርን ለማስታረቅ ሊቀ ካህናት ሆኖ በመስቀል ተሰቅሎ ራሱ መሥዋዕት፣ ራሱ መሥዋዕት ተቀባይ፣ ራሱ መሥዋዕት አቅራቢ ሆኖ አድኖናል። በዚህ አግባብ ሊቀ ካህናት ነህ ለማለት ዕጣን አቅርበውለታል። ከርቤ መራራ ነው። ስለዚህ ምንም ንጹሐ ባሕርይ ብትሆን መራራ ሞትን ትሞታለህ ለማለት ከርቤን አቅርበውለታል።

፻፷፭. እናቱ በድንጋይ በረት አስተኛችው የበለስ ቅጠልም አለበሰችው ይላል። በጨርቅ ጠቀለለችውና የበለስ ቅጠል አለበሰችው የሚለው እንዴት ይታረቃል? የድንጋይ በረት የሚለው ምንድን ነው?

መልስ፡- የድንጋይ በረት ማለት ከድንጋይ የተሠራ በረት ማለት ነው። ድንግል ማርያም ጌታን በወለደች ጊዜ በጨርቅ ጠቅልላ የበለስ ቅጠልም በላዩ ላይ ጣል አድርጋበታለች። በጨርቅም ጠቅልለዋለች እንዳይበርደው ብላ የበለስ ቅጠልም በላዩ አድርጋለታለች። ስለዚህ የሚቃረን ነገር የለውም።

፻፷፮. የፈረሰውን ይሠራ ዘንድ፣ ነፍሳትንም ይቤዥ ዘንድ ቸር እረኛ [ክርስቶስ] ከሰማይ ወረደ ሲል ምን ማለት ነው? መቤዠት ምንድን ነው?

መልስ፡- መቤዠት ማለት ዕዳን ከፍሎ ማዳን ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳምን ዕዳ በመስቀል ከፍሎ አዳምን ስላዳነው ተቤዠው ይባላል። አዳምን ከመርገም ነጻ አውጥቶ አዳነው ማለት ነው። የፈረሰውን ይሠራ ዘንድ ያለው በቤት ግሥ ተናግሮት ነው። የፈረሰ ቤት ሲሠራ አዲስ እንደሚሆን በመርገመ ሥጋ በመርገመ ነፍስ ተይዞ የነበረውን አዳም ክርስቶስ መጥቶ በሐዲስ ተፈጥሮ አድሶታልና ይህንን ለመግለጽ ነው። ከሰማይ ወረደ መባሉ ሰው ሆነ ተብሎ ይተረጎማል።

፻፷፯. የያዕቆብን ደም ግባት የወደደ [እግዚአብሔር] ነው ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፡- ደም ግባት ያለው ሰው ለተመልካቹ ደስ እንደሚያሰኝ ሁሉ እግዚአብሔርም የያዕቆብን ደም ግባት ወደደ ተብሏል። ይህም ውጫዊ ደም ግባትን የሚያመለክት አይደለም። እግዚአብሔር የሚወድ ምግባርን ሃይማኖትን አይቶ ስለሆነ የያዕቆብን ሃይማኖትና ምግባር የወደደ ተብሎ ይተረጎማል። ምሥጢሩ የያዕቆብ ደም ግባት የተባለች ከያዕቆብ ወገን የተወለደች ድንግል ማርያም ናት። በምግባሯ በሃይማኖቷ ከሰው ልጆች ሁሉ ብትበልጥ ድንግል ማርያምን እናቱ ትሆን ዘንድ የወደደ ማለት ነው (መዝ.46፥4 ትርጓሜ)።

**፻፳፰. ኢየሱስ ክርስቶስ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ነው ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፡- ከብርሃን አብ የተገኘ ብርሃን ወልድ ነው ማለት ነው። አብ በባሕርዩ ብርሃን እንደሆነ ወልድም ብርሃን ነውና።

**፻፳፱. ሙሴ የሰበከው የይስሐቅ ቤዛ ይህ ልጅህ ነው ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፡- ክርስቶስ የይስሐቅ ቤዛ ነው የሚለው በምሳሌና በአማናዊ ይተረጎማል። በምሳሌ ይስሐቅ ሊታረድ ሲል በይስሐቅ ፈንታ በግ በዕፀ ሳቤቅ መጥቶ በጉ ታርዷል። ያ በግ የክርስቶስ ምሳሌ ነው፣ ዕፀ ሳቤቅ የድንግል ማርያም ምሳሌ ናት (ዘፍ.22፥13)። በአማናዊ ሲተረጎም ምንም ይስሐቅ ደግ ሰው የነበረ ቢሆንም እንደሌሎች የብሉይ ኪዳን ደጋግ ሰዎች ሲሞት ሲኦል መግባት አልቀረለትም። ከዚያ ያዳነውና ቤዛ ሆኖ ልጅነትን የሰጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

**፻፴. ወደ ዓለም የመጣው ብርሃን የጽዮን በኵር ይባላል ሲል ምን ማለት ነው? ጽዮን ሲል ማንን ነው?**

መልስ፡- በኵር የሚለው የመጀመሪያ ማለት ነው። ጽዮን ያላት ቤተክርስቲያን፣ ድንግል ማርያም ናት። በምሳሌ ድንግል ማርያምም ቤተክርስቲያንም በጽዮን ይመሰላሉና። ክርስቶስ የድንግል ማርያም በኵር መባሉ ተቀዳሚም ተከታይም የሌለው ልጇ መሆኑን ለመግለጽ ነው። የቤተክርስቲያን በኵር መባሉ ለልጅነት፣ ለትንሣኤ ሙታንና ለመሳሰሉት በኵር በመሆኑ ነው።

**፻፴፩. ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም መጥቷልና ኑ በብርሃኑ እንመላለስ ይላል። በብርሃኑ እንመላለስ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፡- የክርስቶስ ብርሃን የተባለች ያስተማራት ወንጌል ናት። በብርሃኑ እንመላለስ ማለት በወንጌል እንኑር ማለት ነው። ይኸውም ምግባር ትሩፋትን እንሥራ ማለት ነው።

**፻፴፪. አዳም ያገለደመው በለስና እመቤታችን ጌታን ያለበሰችው በለስ አንድ ዓይነት ነው?**

መልስ፡- አላውቀውም።

**፻፴፫. ክርስቶስን ለእኛ የተሰጠ የተሠወረ መዝገብ ነው ሲለው እንዴት ነው?**

መልስ፡- ክርስቶስ የተሠወረ መዝገብ ይባላል። ይህም የተሠወረን መዝገብ ሁሉ እንደማያገኘው ክርስቶስንም ያመነበት እንጂ ያላመነበት አያገኘውምና ነው። መዝገብ መባሉ በመዝገብ ብዙ ወርቅ እንደሚገኝ ከክርስቶስም ለምእመናን የሚሰጥ ብዙ ጸጋ አለና።

፻፸፬. ሥጋዋን አንጽቶ በእርሷ አደረ የሚለው ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ሥጋዋን አንጽቶ የሚለው አነጋገር እስከ ጽንሰተ ክርስቶስ በመርገም ቆይታ በኋላ አንጽቶ ተጸነሰ ማለት አይደለም። ከሰው ልጆች ሁሉ ደግ እንደምትሆን በመለኮታዊ ዕውቀቱ አውቆ ከእናቷ ማሕፀን ጀምሮ ንጽሕት አድርጎ ጠብቋታል። ይህንን መጠበቁን ለመግለጽ ቅዱስ ያሬድ አንጽቶ ብሎ ገልጾታል። ከእናቷ ማሕፀን ጀምሮ ጠብቆ ማለት ነው።

፻፸፭. ዘመነ ሐዲስ ከጽንሰተ ክርስቶስ ጀምሮ ነው። ስለምን እስጢፋኖስ ቀዳሜ ሰማዕተ ይባላል? ሕፃናተ ገሊላ ቀድመው ሰማዕት ሆነው የለምን? ከካሣ ወዲህ (ከክርስቶስ ሞት ወዲህ) ነው ከተባለ እነለንጊኖስ በትንሣኤ ውስጥ እንደሞቱ ይነገራልና እንዴት ነው?

መልስ፦ እስጢፋኖስ ቀዳሜ ሰማዕት (የሰማዕታት መጀመሪያ) የተባለው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ በመጻፍ ነው። ይህ ደግሞ "ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ። ክብሩንም ገለጠ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ" ከሚለው ጋር ይመሳሰላል (ዮሐ.2፥11)። እንጂ በተአምረ ኢየሱስም፣ በተአምረ ማርያምም እነ ጊጋር መሰፍንን የመሰሉ ሰማዕታት ቀድመው እንደሞቱ ተጽፏል። ሆኖም ከመጀመሪያዎቹ በመጽሐፍ ቅዱስ በመጻፍ እስጢፋኖስ ስለሚቀድም ቀዳሜ ሰማዕት ተብሏል።

፻፸፮. በስምንተኛ ቀን ይገዝሩት ዘንድ ሕፃኑን ወሰዱት ስሙንም አማኑኤል አሉት ይላል። ሉቃ.2፥21 ስሙ ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ ይላል። ሁለቱ አይቃረንም?

መልስ፦ አይቃረንም። በስምንተኛው ቀን ሲገዘር የተሰየመው ስም በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው "ኢየሱስ" ተብሎ ነው። አማኑኤል እየተባለ የሚጠራውም ግን ያው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ለመግለጽ ቅዱስ ያሬድ "አማኑኤል" ተባለ ብሎታል።

፻፸፯. ከያዕቆብ ወገን የወጣ የቅዱሳን ፀሐይ ክርስቶስ የሃይማኖት ጥሩር ነው ሲል ምን ማለት ነው? የያዕቆብ ወገን ሲል ምን ማለት ነው? ጥሩር ምንድን ነው?

መልስ፦ ጥሩር የሚባለው በቀድሞው ዘመን ራስን ከጦር፣ ከቀስት ለማዳን የሚደረግ የራስ ቁር ነው። ይህም ለዐይን ማያ ብቻ ጥቂት ቀዳዳ ኖሮት እንደቆብ ያለ ከአንገት በላይ ያለውን አካል ሁሉ የሚሸፍን የብረት ልብስ (ቆብ) ነው። ክርስቶስም ከጠላት ሰይጣን የዳንንበትና የምንድንበት በመሆኑ የሃይማኖት ጥሩር ተብሏል። ክርስቶስ የያዕቆብ ወገን፣ የዳዊት ወገን፣ የአብርሃም ወገን እየተባለ ይጠራል። እንዲህ የተባለው እነርሱ አያት ቅድመ አያቶቹ ስለሆኑና በዘር ሐረግ ከእነርሱ ስለሚወለድ ነው።

፻፸፰. ሞትን ያልቀመሰ ዮሐንስ ድንግል ወገቡን በጌታው መታጠቂያ ታጠቀ ይላል። በጌታው መታጠቂያ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ አሁን መነኰሳት እንደሚታጠቁበት ያለ ጌታ ወገቡን የሚታጠቅበት መታጠቂያ ዝናር ነበረው፡፡ ያንን መታጠቂያ አንድ ቀን ዮሐንስም ታጥቆት በዚህ ምክንያት ፍትወት እንስሳዊት ጠፍታለታለችና ይህን ለመግለጽ ነው (መጽሐፈ ቅዳሴ ትርጓሜ)፡፡

**፻፸፱. ከልጅነቱ ጀምሮ ያለበደል ያደገ፣ ከእሳት አጠገብ የተቀመጠ ዮሐንስ ነው ሲል ምን ማለት ነው? ሰው ሆኖ የማይበደል አለ ወይ? ከእሳት አጠገብ ሲልስ ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ዮሐንስ ወንጌላዊ እንደበደለ የተገለጸበት ቦታ የለም፡፡ ያለበደል መባሉ ስለዚህ ነው፡፡ ደግነቱ ግን በወንጌልም በሌሎችም መጻሕፍት ተገልጿል፡፡ ሰው ሆኖ ያለበደል ንጽሕናን ጠብቆ መኖር ይቻላል፡፡ እግዚአብሔር በበደሉት ላይ ገሃነምን የሚፈርድበት ምክንያት ሳልበደሉት ደግሞ መንግሥተ ሰማያትን የሚሸልምበት ምክንያት ለሰው ልጅ አለመበደል የሚችልበትን ክሂል ስለሰጠው ነው፡፡ ከእሳት አጠገብ ተቀመጠ ማለቱ እሳት ያለው ክርስቶስ ነው፡፡ እሳተ መለኮት ገንዘቡ ነውና፡፡ ከክርስቶስ አጠገብ ተቀመጠ ማለት ነው፡፡

**፻፹. አብ ወልድን ቅድመ ዓለም ሲወልደው አንድ ጊዜ ነው?**

መልስ፦ አዎ፡፡ በሃይማኖተ አበው "ወኢየኀልቅ ልደቱ እምኔሁ" ይላል (ሃይ.አበ.13፥24)፡፡ ይህም ማለት ሁልጊዜ ወልድ ሲባል ይኖራል ማለት ነው እንጂ ሁልጊዜ ሲወለድ ይኖራል ማለት አይደለም፡፡ ሳዊሮስ ዘእስሙናይንም ከፀሐይ ክበብ ብርሃን ያለማቋረጥ እንደሚወጣ ወልድም ከአብ ያለማቋረጥ እንደሚወለድ ገልጿል፡፡ ይትወለድ የሚለው ካልኣይ አንቀጽ በቀዳማይ አንቀጽ ተወልደ ተብሎ መተርጎም ስለሚችል ያለማቋረጥ ተወለደ ተብሎ ይተረጎማል፡፡ ካልኣይ በቀዳማይ ቀዳማይ በካልኣይ ይተረጎማልና፡፡ ለዚህም ማስረጃው አመ ይወፅኡ እስራኤል እምግብጽ የሚለው ነው፡፡ አመ ወፅኡ ማለት ነውና፡፡ ያለማቋረጥ (እንበለ ተመትሮ) ተወለደ የሚለውም እናት ልጇን ስትወልድ በህልውና ከእርሷ ይለያል ተመትሮ አለበት፡፡ ወልድ ከአብ ሲወለድ ግን በህልውና ከአብ ሳይለይ ነውና ይህንን ለመግለጽ ነው፡፡

**፻፹፩. አቡቀለምሲስ ማለት ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ አቡቀለምሲስ የተባለ ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው፡፡ ትርጉሙም ረኣዬ ኅቡዓት ማለት ነው፡፡ ይህም ምሥጢርን ያየ፣ የሚያይ ማለት ነው፡፡

**፻፹፪. ዮሐንስን ደስ የሚያሰኝ ምሥጢርን ያየህ በምድር ያለህ መልአክ ነህ ሲለው እንዴት ነው? መልአክ እንዴት ተባለ?**

መልስ፦ ተፈጥሮው ምድራዊ ሆኖ በተግባር መላእክትን የመሰለ ሰው መልአክ ዘበምድር ይባላል፡፡ ለምሳሌ መላእክት ሥጋዊ ምግብን አይበሉም፡፡ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም ከሥጋው ከደሙ በቀር ምግብን አይበላም ነበረ፡፡ በዚህ ምክንያት መልአክ ዘበምድር

ይባላል። ዮሐንስም ፍትወት እንስሳዊት የጠፋለት በመሆኑና ንጽሕናው እንደመላእክት ስለነበር መልአክ ዘበምድር ተብሏል።

**፶፫. ማርያምም እስኪ ጠይቁ ብነግራችሁ ከአፌ እሳት ወጥቶ ዓለምን ሁሉ ያጠፋል አለቻቸው ይላል። እንዴት? ነቢያት ማርያምን እንደጠየቋት ይናገራል። ሳይኖሩ እንዴት?**

መልስ፦ ድንግል ማርያም በክብር ከፍጡራን በላይ ናት። ለእርሷ የተገለጠውን ምስጢር ለሌላው ብትናገር የሌላው ፍጥረት ያንን ምስጢር የመስማት አቅም ዝቅተኛ ስለሆነ ብናገር ከአፌ እሳት ወጥቶ ዓለምን ያጠፋል ብላለች። ለምሳሌ በትንሽ አምፖል ብዙ ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኀይል ብንለቅበት ይቃጠላል። አምፖሉ የሚቃጠለው ከአቅሙ በላይ የሆነ ኀይል ስለተለቀቀበት ነው። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሰማችውን ምሥጢር ሌላው ፍጥረት መስማት አይችልም። እንዲያውም በአንድ ወቅት ሐዋርያት ንገሪን ብለዋት ታሪኩን ልትጀምርላቸው "ቀኑ ካፊያ ነበረ፣ ወትሮ የማውቀው መልአክ ቀርቶ ሌላ መልአክ መጣ" ብላ ወደ ምስጢሩ ልትገባ ስትል የመልአክ ድምፅ ተሰማ። ያን ጊዜ ሐዋርያት እንደ ቅጠል ረገፉ ይላልና (የማክሰኞ ውዳሴ ማርያም አይ ልሳን ትርጓሜ)። ነቢያት ጠየቋት ማለቱ ሰብአ አርድእትን ነቢያት ስለሚላቸው ሰብአ አርድእትም ጠየቋት ማለት ነው።

**፶፬. የርስታችን ፈለማ ፍጹም ውበታችንና ሽልማታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ሲል ፈለማ ምንድን ነው?**

መልስ፦ ፈለማ ማለት ዋናው ከመሰጠቱ በፊት የሚሰጥ ቅምሻ ማለት ነው። ለክርስቶስ ሲነገር ግን ዋናውም ቅምሻውም ራሱ ነው። ታዲያ ቅምሻ መባሉ ስለምን ነው ከተባለ በዚህ ምድር ሰጥቶን የሚኖረው ጸጋ በኋላ በመንግሥተ ሰማያት ከምናገኘው ጸጋ ስለሚያንስ ነው። ፈለማ ከዚህ ከሚሰጠን ጸጋ አንጻር የሚተረጎም ነው ማለት ነው። እንጂ ክርስቶስ በዚህም በዚያም አንድ ነው።

**፶፭. ከዕሴይ ሥር የክብር ፍሬ ወጣ ሲል ምን ማለት ነው? ዕሴይ ምንድን ነው?**

መልስ፦ ዕሴይ የዳዊት አባት ነው። ክርስቶስ ከዳዊት ዘር ስለተወለደ ዕሴይም ከቅድመ አያቶቹ አንዱ ነው። የዕሴይ ሥር የተባለች ድንግል ማርያም ሲሆን ከእርሷ የተገኘው የክብር ፍሬ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሥር ካለ ዘንድ ፍሬ አለ እንጂ ወርቁ ክብር የሚለው ነው። ክርስቶስ በባሕርዩ ክቡር ስለሆነ ከዚህ ክብር ተብሏል። እግዚአብሔር ፍቅር ነው እንደሚለው ነው (1ኛ ዮሐ.4፥16)።

**፶፮. ክርስቶስ በነጭ ወፍ የተመሰለበት ምክንያት ምንድን ነው?**

መልስ፦ ይህ ነጭ ወፍ በልዩ ስሙ ከራድዮን ይባላል። በታመመ ሰው ፊት ያኖሩት እንደሆነ አፉን ከአፉ ገጥሞ የታማሚውን እስትንፋስ ይወስዳል። ከዚያ ነጭ የነበረው

ወፍ ከሕመሙ የተነሣ ይጠቁራል። ብርድ ብርድ ሲለው ወደ አየር ከፍ ብሎ በርሮ ራሱን የፀሐይ ብርሃን ያስመታል። ከዚያ ሦስት ቀን በባሕር ቆይቶ በሦስተኛው ቀን እንደበፊቱ ነጭ ሆኖ ይመለሳል። ጌታም የታማሚውን አዳም ባሕርይ ባሕርይ አድርጎ ስለአዳም በመስቀል ተሰቅሎ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ ባለመታመም ግብር ጸንቶ ኖሯልና ክርስቶስ በነጭ ወፍ ተመስሏል (የአርብ ውዳሴ ማርያም ቡርክት አንቲ ተዐብዩ እምሰማይ ትርጓሜ)።

**፻፹፮. ዙፋኑ በኢዮር ላይ የሆነ መመላለሻው ደመና የሆነ፣ አዳራሹ የእሳት፣ ጣሪያው የውሃ የሆነ እግዚአብሔር ነው ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ኢዮር ከመላእክት ከተሞች የላይኛው ከተማ ነው። ዙፋኑ በኢዮር ላይ የሆነ ማለት ዙፋኑ ልዑል [ታላቅ] የሆነ ማለት ነው። አዳራሹ የእሳት የተባለው ባሕርዩ ራትዕ የሆነ ማለት ነው። ጣሪያው የውሃ ማለት ባሕርዩ መንጽሒ የሆነ ማለት ነው። ደመና መመላለሻው የሆነ ማለት በባሕርዩ ልዑል የሆነ ማለት ነው። "ዘበእንተ ዕበይከ ትትሜሰል በደመና" እንዲል። ሁለተኛው ትርጉሙ ደግሞ እንዳለ ይሆናል። እግዚአብሔር በዘፈቀደ የሚገለጥበት ዙፋን ከኢዮር በላይ ባለ በመንበረ ስብሐት ይገኛል። መመላለሻው የደመና፣ አዳራሹ የእሳት፣ ጣሪያው የውሃ ነው። ይህም ለብዙ ቅዱሳን በተገለጠላቸው መናገራችን እንጂ በዚህ ብቻ የሚወሰን አይደለም።

**፻፹፯. ቃል በቃሉ ተናገራት በመልአክ አምሳያ ታያት ሲል የተገለጸላት መልአኩ አይደለም ማለት ነው?**

መልስ፦ የተገለጸላት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ነው። ቃለ እግዚአብሔር ደግሞ በገብርኤል አድሮ ተናግሯታል። አካላዊ ቃል በገብርኤል አድሮ ትወልዲ በሚል በሚሰማ ድምፅ (ዝርው ቃል/ቦርፎሪኮን) ተናገራት ማለት ነው። በገብርኤል አድሮ የተናገረ ቃለ እግዚአብሔር ስለሆነ ባለቤቱን ቃል ብሎታል። በቃሉ ብሎ ደግሞ በማድረጊያ የተናገረው ትወልዲ በሚለው ዝርው ቃል ተናገራት ለማለት ነው።

**፻፹፰. ዘጠና ዘጠኙን ነገድ ትቶ ከሰማያት ወረደ ሲል ምን ማለት ነው? መቶ ነገድ የሚባለው እንዴት ነው? 99 ነገድ ለምን ተባሉ?**

መልስ፦ እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ የሚኖር አምላክ ስለሆነ አንዱን ለመፈለግ ሌላውን አይተውም። ስለዚህ ትቶ የሚለው አገላለጽ ባሕርያቸውን ሳይዋሐድ ተብሎ ይተረጎማል። የ99ኙን ነገደ መላእክት ባሕርይ ሳይዋሐድ ለይቶ የሰውን ባሕርይ ተዋሐደ ማለት ነው። "ኢነሥአ ለዘነሥአ እመላእክት ዘእንበለ ዳእሙ እምዘርአ አብርሃም" እንዲል (ዕብ.2፥16)። መላእክት ሲፈጠሩ መቶ ነገድ ነበሩ። አንዱ ነገድ ግን ከሳጥናኤል ጋር ወድቋል። በዲያብሎስ ምትክ ሰው ገብቷል። ሰውም ወደቀ። ነገር ግን ንስሓ በመግባቱ ባሕርዩን ተዋሕዶ አምላክ አድኖታል።

፻፺. ዮሐንስ ኢየሱስን አጠመቀው በጥምቀቱም ውሃ ተቀደሰ ይላል። ውሃ ርኩስ ነበረ ወይ? ከምን አንጻር ነው ተቀደሰ ያለው?

መልስ፦ ውሃ ርኩስ አልነበረም። ነገር ግን በብዙዎች ዘንድ እንደ ርኩስ ይታይ ነበር። ለዚህ መነሻ የሆነውም በኖኅ ዘመን የዓለም በንፍር ውሃ መጥፋት ነው (ዘፍ.7፥6)። ይህ ብቻ ሳይሆን ውሃ በነፍሳዊው ሕይወት ምንም ፋይዳ አልነበረውም። ክርስቶስ ሰው ሆኖ በዮርዳኖስ ከተጠመቀ በኋላ ግን ውሃ ተቀድሶበት ልጅነትን ለማግኘት ምክንያት ሆኗልና ተቀደሰ ተብሏል (ዮሐ.3፥5)። በጥምቀት ካህኑ ከቀደሰበት በኋላ ወደ ማየ ገቦ ተለውጦ ልጅነትን የምናገኝበት ሆኗልና።

፻፺፩. ከዓለም በፊት ብርሃንን የፈጠረ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ዓለም የሚለው ቃል በብዙ መንገድ ይተረጎማል። ከብዙዎች መካከል ጥቂቶቹን እንመልከት። አንደኛ ፍጥረታት ሁሉ ዓለም ይባላሉ (መዝ.90፥11)። ሁለተኛ ኃጢአት ዓለም ይባላል። "ኢታፍቅርዎ ለዓለም ወኢ ዘሀሎ ውስተ ዓለም ወዘሰ አፍቀሮ ለዓለም ኢሀሎ ፍቅረ እግዚአብሔር ላዕሌሁ" እንዲል (1ኛ ዮሐ.2፥15)። ሦስተኛ ዓለም የሚባለው ሰው ነው። "እስመ ከመዝ አፍቀሮ እግዚአብሔር ለዓለም እስከ ወልዶ ዋሕደ መጠወ ወወሀበ ቤዛ ለኵሉ ከመ ኵሉ ዘየአምን ቦቱ ኢይትኀጐል አላ ይረክብ ሕይወተ ዘለዓለም" እንዲል (ዮሐ.3፥16)። ከዓለም በፊት ብርሃንን የፈጠረ የሚለው በሦስተኛው የሚተረጎም ነው። ይህም ማለት ከሰው በፊት ብርሃንን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው ማለት ነው።

፻፺፪. ሙሴና ዳዊት ጠል ያሉት ቃልን ማርያም ወለደችው ሲል ምን ማለት ነው? ጠል የተባለበት ምክንያት ምንድን ነው?

መልስ፦ ሙሴና ዳዊት ቃለ እግዚአብሔርን ጠል ያሉት ከፀምር አንጻር ነው። ጠል እንደ ጤዛ በደመና ጊዜ ብናኝ መስሎ ወደ ምድር የሚወርድ ነው። በዚህ ጊዜ ፀምር ከመሬት ካለ ጠሉ ከፀምሩ ላይ ያርፋል። ጠል የደረቀውን እንደሚያለመልም ክርስቶስ በኃጢአት ደርቆ የነበረውን ዓለም አድኖታልና ነው። ጠሉ በፀምር እንዳረፈ ቃለ እግዚአብሔርም በድንግል ማርያም ማሕፀን ተፀንሶ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ኖሯልና ፀምር የድንግል ማርያም ምሳሌ ነው።

፻፺፫. ከእኛ ተሠውሮ ሲኖር ዛሬ ግን የተገለጠ ሆነ ውሃውንም ወይን አደረገው ይላል። ወይን ሲል ምን ማለት ነው? ተሠውሮ ሲኖር ማለትስ ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ወይን የተባለው በቁሙ ወይን ነው። ጌታ በቃና ዘገሊላ ውሃውን ወደ ወይን ለውጦታልና (ዮሐ.2፥1-11)። በምስጢር ደግሞ ወይን የተባለ የክርስቶስ ደም ነው። "ምንትኑ ሕይወቱ ለዘኢይሰቲ ወይነ እስመ ውእቱ ለትፍሥሕተ እጓለእመሕያው

ተፈጥረ" እንዲል (ሲራ.34፥27)፡፡ ተሠውሮ ሲኖር ያለው እግዚአብሔር ሳይታይ ይኖር ነበርና ነው፡፡ ሥጋን በተዋሐደ ጊዜ ግን በሥጋው ታይቷልና ይእዜሰ ክሡተ ኮነ አለ፡፡

**፪፻፴፬. ቴዎድሮስ ማለት መሥዋዕት ማለት ነው ይላል፡፡ ይህ ዓይነት አተረጓጎም እንዴት ነው? ስሙ ራሱ መሥዋዕት ማለት ነው? ኃያል ቴዎድሮስ የቃል ሰማዕት ነው ሲል የቃል ሰማዕት ማለት ምን ማለት ኘው?**

መልስ፡- በትርጓሜ ብዙ ዓይነት ስልቶች አሉ፡፡ አንደኛው ቃላዊ ትርጓሜ ነው፡፡ በቃላዊ ትርጓሜ ቴዎድሮስ የግሪክ ቃል ሲሆን በአማርኛ የእግዚአብሔር ስጦታ ማለት ነው፡፡ ሁለተኛው የትርጓሜ መንገድ ግብራዊ ትርጓሜ ነው፡፡ ይህም ማለት የሰዎችን ግብር መሠረት አድርገን የምንተረጉመው ትርጓሜ ነው፡፡ ለምሳሌ ይሁዳ ማለት ከሓዲ ማለት ነው ብንል ግብርን መሠረት ያደረገ ትርጓሜ ይባላል፡፡ ቴዎድሮስ ማለት መሥዋዕት ማለት ነው የሚለው ትርጉምም ግብራዊ ትርጓሜ ነው፡፡ እውነትን በመመስከር ለእግዚአብሔር ራሱን የከበረ መሥዋዕት አድርጓልና ነው፡፡

**፪፻፴፭. የከበረ ደሙንና እኛን የሚያነጻን ውሃን [ማየ ገቦን] ሰጠን ሲል ምን ማለት ነው? ጠበል፣ ውሃ እና ማየ ገቦን እንዴት እንገልጻቸዋለን?**

መልስ፡- ማየ ገቦ የሚለው ቃል በአማርኛ የጎን ውሃ ማለት ነው፡፡ ይህም ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ለንጊኖስ ጎኑን በወጋው ጊዜ ከጎኑ ውሃና ደም ወጥቶ ነበር፡፡ ውሃው ማየ ገቦ ይባላል፡፡ "አሐዱ እምሐራ ረገዞ ገቦሁ ዘየማን በኲናት፡፡ ወሶቤሃ ወፅአ እምኔሁ ደም ወማይ" እንዲል (ዮሐ.19፥34)፡፡ አሁን ካህናት ጸሎት አድርገውበት ሕፃናትን የሚያጠምቁበት ውሃ በእግዚአብሔር ቸርነት በዕለተ ዓርብ ከጌታ ጎን የፈሰሰውን ውሃ ሆኖ ልጅነትን ያሰጣል፡፡ ጠበል የሚባለው የተቀደሰ ውሃ ነው፡፡ ይህም የሰው ልጆች ፈውስ የሚያገኙበት ውሃ ነው፡፡ በውሃነት ሁሉም ውሃ ቢሆኑም ነገር ግን ለሰው ልጆች ባላቸው ጥቅም ይለያያሉ፡፡ ማየ ገቦ ልጅነትን፣ ጠበል ፈውስን የምናገኝበት ሲሆን ሌላው ውሃ ደግሞ እየጠጣነው፣ ልብስ እያጠብንበት…ወዘተ የምንጠቀምበት ነው፡፡

**፪፻፴፮. ማርያም አንተ ዕፍረትን ስሟንም በዓለም ሁሉ ያስቡ ዘንድ አደረገ ሲል ምን ማለት ነው? የሌሎች ስምስ እንዴት ነው የሚታሰበው?**

መልስ፡- ማርያም እንተ እፍረት የተነሣሒያን አብነት ስለሆነች የእርሷ ግብር ለሌላው ትውልድም ቢነገር አስተማሪ መሆኑን ጌታ ስላወቀ ይነገር ብሏል (ማቴ.26፥13)፡፡ የሌሎች ቅዱሳን ታሪክም ለእኛ ለሰው ልጆች አርአያ ይሆን ዘንድ ተጽፎ ይነገራል፡፡ ለዚህም አብነታችን ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን የብዙ አባቶች ማለትም የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ…ወዘተ ታሪክ ተጽፏል፡፡ በሐዲስ ኪዳንም የሐዋርያት ሥራን ብንመለከት የእስጢፋኖስ፣ የጳውሎስና የሌሎችም ታሪክ ተጽፏል፡፡ ከዚያም በኋላ የተነሡ አባቶች ታሪክ በድርሳናት፣ በገድላት ተጽፎ ይቀመጣል፡፡ ስለዚህ የማርያም

እንተ እፍረትን ብቻ ሳይሆን ቅዱሳንን ሁሉ እናከብራለን መልካም ሥራቸውንም እየተናገርን እንመሰክራለን።

**፻፺፯. የክርስቶስ መለኮት ውበት መገለጥ ሆነ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ የመለኮት ውበት ያለው ግብረ መለኮትን ነው። የክርስቶስ የመለኮት ውበት ታወቀ ማለት አምላካዊ ሥራው ታወቀ ማለት ነው። ይኸውም ዕው*ራንን በማብራት፣ የተራቡትን በማጥገብ፣ ሕሙማንን በመፈወስ፣ ተአምራትን በመሥራት አሳይቷልና ነው።

**፻፺፰. እንደሰው ሁሉ ሞት በኅበኛት ጊዜ የአምላክ እናት እንዴት አለቀሰች ይላል። ቅዱስ ጳውሎስ ልሄድ ከክርስቶስ ጋር መኖር ይሻለኛል እያለ ይደሰት ነበር። እንዴት ነው ሞትን የፈራችው? በወንጌል ለቅዱሳን ሞት ያስፈራል?**

መልስ፦ ሞት ያስፈራልም አያስፈራምም። መፍራት ኃጢአት አይደለም። ድንግል ማርያምን ከሞት በፊትም ሄሮድስ ልጅን ይገድልብኛል ብላ በመፍራት እሾሁ እየወጋት፣ ውሃ እየጠማትና በመሳሰሉት ከሄሮድስ ሠራዊት በመሸሽ አሳልፋለች። ሞትም እንግዳ በመሆኑ ፈርታለች። ለሰው ልጆች ሞትን መፍራት ተፈጥሯዊ ነው። ክርስቶስም ሰው እንደመሆኑ ፈራ ተብሏል። "ወፈርሀ ወአውተረ ጸልዮ" እንዲል (ሉቃ.22፥44)። የእርሱ መፍራት ፍርሀተ ነፍስን ከእኛ ለማራቅና ለቤዛነት ቢሆንም በሰውነቱ መፍራቱ በደል አያሰኝምና ነው። ቅዱስ ጳውሎስም ወደ ክርስቶስ ለመሄድ እቸኩላለሁ ማለቱ የሁሉም ክርስቲያን ፈቃድ ቢሆንም ሞትን አልፈራም የሚል አረዳድን ግን አያመጣም። ሞትን ይፈራሉ። የሚፈሩት ግን ሞትን መፍራት ተፈጥሯዊ ስለሆነ እንጂ በመጠራጠር አይደለም።

# ድጓ ዘፋሲካ ወዘክረምት ላይ የተጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው




አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው ካሣ

(የመጻሕፍተ ሊቃውንት፣ የመጻሕፍተ ብሉያትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)


ነሐሴ ፲፩፣ ፳፻፲፫ ዓ.ም

## ● መጽሐፈ ድጓ ላይ የተጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው ●

**፻፺፱. በመጀመሪያ ሐዋርያትን ዳግመኛ ነቢያትን ሦስተኛ ሊቃውንትን ለቤተክርስቲያን ጆሮ አድርጎ ሰጠን ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ከዚህ ነቢያት ያላቸው ሰባ ሁለቱን አርድእት ነው። "ወወረደ አሐዱ ነቢይ እምይሁዳ ዘስሙ አጋቦስ" እንዲል (የሐዋ. ሥራ 21፥10)። ሐዋርያትን፣ ነቢያትን፣ ሊቃውንትን ጆሮ አድርጎ ሰጠን ማለቱ በጆሮ ድምፅን እንደሚሰሙበት ሁሉ በሐዋርያት፣ በነቢያት፣ በሊቃውንትና በጠቅላላው በቅዱሳንም የእግዚአብሔርን ድምፅ [ትምህርት] እንሰማባቸዋለንና ነው።

**፪፻. ላሕም መግዝዕ ተጠብሐ ዘወለደት ለነ ሐዳስ ጣዕዋ ሲል እንዴት ይተረጎማል? አዲሲቷ ጥጃ ማን ናት? የሰባ ፍሪዳስ ማን ነው?**

መልስ፦ የሰባ ፍሪዳ የተባለ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የሰባ ፍሪዳ በሚበሉት ሰዎች ዘንድ የተወደደ እንደሆነ ሁሉ የክርስቶስ ሥጋንም አማኞች በልተውት ደስ ይላቸዋልና ነው። ይህንን የሰባ ፍሪዳ ያስገኘችዋ አዲሲቷ ጥጃ የተባለች ደግሞ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት። አዲስ ጥጃ የምትባል ከዚህ ቀደም ያልወለደች ጥጃ ናት። ለድንግል ማርያምም ክርስቶስ የበኵር ልጇ ነውና። ከእርሱ ውጭም ሌላ ልጅ የላትም።

**፪፻፩. ሰማያት በዓልን ያደርጋሉ ደመናዎች በዓልን ያደርጋሉ ምድርም በክርስቶስ ደም ታጥባ ፋሲካን ታደርጋለች ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ሰማያት፣ ደመናት ያላቸው አንድ ወገን መላእክት ናቸው። ሰማያት ያላቸው በመኖሪያቸው ነው። ፏሪን በመኖሪያ (ኀዳሪን በማኀደር)፣ መኖሪያን በኗሪ (ማኅደርን በኀዳሪ) መጥራት ልማደ መጽሐፍ ነውና። ደመናት ያላቸው ስለልዕልናቸው ነው። ምድር በክርስቶስ ደም ታጥባ ደስ ተሰኘች ያለውም በምድር ሰውን መናገሩ ነው። የሰው ልጆች በክርስቶስ ደም ስለተዋጁ በፋሲካ ደስታን ያደርጋሉ ማለት ነው።

**፪፻፪. በነቢይ ነፃ የወጣ ነው አለ። ነፃ የወጣ ማለት ሞት አያገኘውም ማለት ነው ይላል። ምን ማለት ነው? ክርስቶስን ሞቶ የተነሣ እርሱ ብቻ ነው ሲለው ምን ለማለት ነው? ሌሎችስ አሉ አይደል?**

መልስ፦ ይህ ቃል የሚገኘው መዝ.87፥5 ላይ ነው። ግዑዝ ውስተ ምውታን እንዲል። ይህ ስለክርስቶስ የተነገረ ነው። ግዑዝ (ነጻ የወጣ) ነው የተባለበት ምክንያት በመለኮቱ ሞት አላገኘውም ማለት ነው። ሞቶ የተነሣ እርሱ ብቻ ነው ማለት ሌሎች ቢነሡም በእርሱ አስነሺነት ነው። በራሱ ሥልጣን በመነሣት ግን ብቸኛ ስለሆነ ሞቶ የተነሣ እርሱ ብቻ ነው ተብሏል።

**፪፻፫. ትንሣኤ ሰመያ ለበዓለ ፋሲካ ማለት ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ክርስቶስ ከሞት የተነሣበት ቀን ፋሲካ ይባላል:: ፋሲካ ማለትም መሻገሪያ ማለት ነው:: ራሱ ቅዱስ ያሬድ ፋሲካ ብሂል ማዕዶት ብሂል እንዲል:: ይቺን ፋሲካን ደግሞ የተነሣባት መሆኗን ለመግለጽ ትንሣኤ ብሏታል::

**፪፻፬. ይህቺ ፋሲካ ደገኛዪቱ ሕግ ናት ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ደገኛ ማለት ዋና ማለት ነው:: ፋሲካ ከዋናዎቹ በዓላት መካከል ትቆጠራለች ማለት ነው:: ሕግ ናት ማለቱ የምትከበር ሥርዓት ናት ማለት ነው::

**፪፻፭. ስለአዳም ሞት ተፈጠረ ስለክርስቶስ ደግሞ ትንሣኤ ሆነ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ስለአዳም ሞት ተፈጠረ ማለት በአዳም አለመታዘዝ ምክንያት ሞት መጣ ማለት ነው:: የሞት ምክንያት የአዳም ስሕተት ነውና:: ስለክርስቶስ ደግሞ ትንሣኤ ሆነ ማለት በኵረ ትንሣኤ ሆኖ ለሌላውም ትንሣኤ ሰጥቷልና ትንሣኤም ምክንያተ ትንሣኤም ሆኗልና ነው (1ኛ ቆሮ.15፥21)::

**፪፻፮. እግዚአብሔር ወደ ሲኦል ወርዶ እንደ አድማስ ጽኑ የሆኑ መዝጊያ ቁልፎችን ቀጠቀጠ ሲል ምን ማለት ነው? አድማስ ምንድን ነው?**

መልስ፦ አድማስ ማለት ጽኑ ጠንካራ ማለት ነው:: በሲኦል ግዙፍ ቁልፍ፣ መዝጊያ ኖሮ አይደለም:: ጽንዐ መከራውን ለመግለጽ ነው:: ክርስቶስ እነዚህን ቁልፎች ቀጠቀጠ ማለቱ ጽንዐ መከራውን አስወግዶ ነፍሳትን ወደ ገነት መልሰ ማለት ነው::

**፪፻፯. የሞትን ፃእረኝነት አጠፋ ይላል:: ታዲያ ዛሬ የምንሞተው ሞት ምንድን ነው?**

መልስ፦ የሞት ፃእረኝነት የሚባለው ሙስና መቃብር፣ መርገም፣ ፍዳ ነው:: ክርስቶስ የሞት ፃእረኝነትን አጠፋ ማለት መርገመ ሥጋን መርገመ ነፍስን እና በሞት ምክንያት ፈርሶ በስብሶ መቅረትን አጠፋልን ማለት ነው::

**፪፻፰. በሰንበት የጨለማ ኀይል ራቀ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ የክርስቶስ ትንሣኤ ብርሃን ይባላል:: ትንሣኤው የተደረገው ደግሞ በሰንበት ስለሆነ ይህንን ለመግለጽ በሰንበት የጨለማ ኀይል ራቀ ተብሏል:: ምስጢሩ ሙስና መቃብር ጠፋ ማለት ነው::

**፪፻፱. በድንቅ ጥበቡ ከሙታን መካከል የተነሣ ኢየሱስን ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በበፍታ ገነዙት ይላል:: በፍታ ምንድን ነው?**

መልስ፦ በፍታ ማለት ኩታ [ጋቢ] ማለት ነው::

**፪፻፲. ዛሬ በዚህች ቀን በሰማያት የሕይወት ተስፋ ተሠራ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ በሰንበት ክርስቶስ ተነሥቶ ለእኛ መነሣትን ሰጥቶናል። እርሱ በኵረ ትንሣኤ ሆኖ ትንሣኤን ሰጥቶናል። ይህ የሆነው ደግሞ በሰንበት ስለሆነ የሕይወት ተስፋ ተሠራ ተብሏል። ክርስቶስ ሞቶ ባይነሣልን ኖሮ ግን ሞቶ መቅረት በእኛ ላይ ጸንቶ በኖረ ነበር።

**፪፻፲፩. ቀደምት ከሆኑ በዓላት የምትበልጪ ሰንበተ ክርስቲያን ሆይ በሰላም ነይ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ቀደምት ያላቸው የተሻሩ የኦሪት በዓላት ናቸው። በክብር ሰንበተ ክርስቲያን ትበልጣለችና የምትበልጪ አላት። በሌላ መልኩ ቀደምት የሚለው ታላላቆች ማለት ነው። ቀዳሚሆሙ ለአሕዛብ አማሌቅ እንዲል። ከታላላቆች በዓላት የምትበልጪ ማለት ነው። ሰንበት ከበዓላት ሁሉ የምትበልጥ የማታልፍ ዘለዓለማዊት በዓል ናት።

**፪፻፲፪. የአብ የመጀመርያ ፍጥረት ሞትን አሸነፈ ይላል። የአብ የመጀመርያ ፍጥረት የተባለ ማን ነው?**

መልስ፦ ይህ የቅዱስ ያሬድ ቃል ምሳ.8፥22ን መሠረት አድርጎ የተነገረ ነው። የአብ የመጀመሪያ ፍጥረት ብሎ የገለጸው ክርስቶስን ነው። የመጀመሪያ የተባለበት ምክንያት ደግሞ ለሐዲስ ተፈጥሮ መጀመሪያ ስለሆነ ነው። ትርጓሜው ቃል በቃል እንዲህ ይላል። "በሐዲስ ተፈጥሮ ከሚፈጥራቸው ምእመናን አስቀድሞ እግዚአብሔር ፈጠረኝ። ድኅረ ዓለም በሥጋ መፈጠሩ ቅድመ ዓለም በልበ ሥላሴ ስለታወቀ እንዲህ አለ" ይላል። የክርስቶስ ሥጋ ቅድመ ዓለም የነበረ ሳይሆን የተፈጠረ ነውና። ይህ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተነሣ ሥጋ ቃልን በተዋሕዶ ገንዘብ አድርጎ የባሕርይ አምላክ ሆኖ በመስቀል ተሰቅሎ ሞትን አሸነፈ ማለት ነው። ይህ ስለሰውነቱ የተነገረ እንጂ በአምላክነቱ እንደ አብ ሰማይን ምድርን የፈጠረ ነው።

**፪፻፲፫. ሃይማኖት ከአብ ተፈጥራ ወደ ወልድ ታደርሳለች በመንፈስ ቅዱስ ትፈጸማለች ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በአንድነት የሚሠሩትን ግብረ ባሕርይ ለየአካላቱ አድሎ መናገር መጽሐፍ ቅዱሳዊ አገላለጽ ነው። የፈጠሩ ሦስቱ በአንድነት ሆነው ሳለ ኢዮብ መንፈስ ቅዱስን ለይቶ "የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ" ብሏል (ኢዮ.33፥4)። ዮሐንስ ወልድን ለይቶ "ሁሉ በእርሱ ሆነ" ይላል (ዮሐ.1፥3)። ሙሴ አብን ለይቶ "አኮኑ ዝንቱ አብ ዘፈጠረከ ፈጠረከኒ ወገብረከ" ብሏል (ዘዳ.32፥6)። ቅዱስ ያሬድም ሃይማኖት በሦስቱ የአንድነት ፈቃድ እንደተሰጠች የታወቀ ቢሆንም ለአብ አድሎ ሰጥቷል። ወደ ወልድ ታደርሳለች በመንፈስ ቅዱስ ትፈጸማለች ማለቱ ለዚህ ማረጋገጫ ነው። ወደ ወልድ የምታደርስበት ሁኔታ አብ ማን ነው ባልን ጊዜ ወላዲ ስለምንል ወላዲ ካልን

ዘንድ ደግሞ ተወላዲ ስለሚኖር ተወላዲው ደግሞ ወልድ በመሆኑ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ትፈጸማለች ማለት አብን ወላዲ አሥራጺ ካልን ሠራጺ መንፈስ ቅዱስ ነውና። በአጭሩ ምሥጢሩ ሃይማኖት አብን ወላዲ አሥራጺ፣ ወልድን ተወላዲ፣ መንፈስ ቅዱስን ሠራጺ በማለት ትመሰክራለች ማለት ነው።

**፩፻፲፩. የእንስሳት፣ የሰውና የአራዊት ድምፅ ከሦስቱ የያሬድ ዜማዎች አያልፉም ይላል። ምን ማለት ነው? የእንስሳትና የአራዊት ድምፅ ከያሬድ ድምፅ ጋር የሚያገናኘው ነገር አለ?**

መልስ፦ ቅዱስ ያሬድ ቀድሞ ያልነበረ ድምፅ አልፈጠረም። ቀድሞ የነበረውን ድምፅ ግን አራራይ፣ ግእዝ፣ ዕዝል በማለት ቅርጽ አስይዞታል። ስለዚህም ልዩ ስልት ያለው አድርጎ እግዚአብሔር እንዲመሰገንበት አድርጓል። ማንኛውም ድምፅ ከሦስቱ ማለትም ከግእዝ፣ ከዕዝል፣ ከአራራይ አይወጣም። የአሁን ሊቃውንትን እንኳ ብንጠይቅ ለሆነ ጩኸት ምልክት ስጡት ቢባሉ ይሰጡታል። የእንስሳት፣ የአራዊት፣ የአዕዋፋት ድምፅ ዘፈቀዳዊ ነው። በተለየ የቅዱስ ያሬድ ግን ልዩ ስልተ ዜማ አለው።

**፩፻፲፪. ያላወረደውን ሥጋ ነስቶ ወደ ሰማይ ዐረገ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ የክርስቶስ ሥጋ ከሰማይ የወረደ አይደለም። ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተገኘ ነው እንጂ። አንዳንዶች የክርስቶስ ሥጋ ከሰማይ የወረደ ያልተፈጠረ ነው ይላሉ። ይህ ግን ፍጹም ክሕደት ነው። "መለኮትሰ ኢፍጡር ውእቱ። መለኮት ያልተፈጠረ ነው። ወሥጋሰ ፍጡር ውእቱ። ሥጋ ግን የተፈጠረ ነው። መለኮትሰ ኢሐማሚ ውእቱ። መለኮት የማይታመም ነው። ወሥጋሰ ሐማሚ ውእቱ። ሥጋ ግን የሚታመም ነው" እንዲል (ሃይ.አበ.39፥25)። ስለዚህ ያላወረደውን ነሥቶ ወደ ሰማይ ዐረገ ማለት ሥጋን ተዋሕዶ ከትንሣኤ በአርባኛው ቀን የርቀት ያይደለ የርኅቀት ዕርገትን ዐረገ ማለት ነው። "ወእንዘ ይባርኮሙ ተረኅቀሙ" እንዲል (ሉቃ.24፥51)።

**፩፻፲፫. የጌታችን ልብሱ የእሳት ዙፋኑ የሐር ነው ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ለእግዚአብሔር ልብሱ፣ ዙፋኑ፣ ሰይፉ...ወዘተ እያለ ሲነገር ባሕርዩ ተብሎ ይተረጎማል። ለእግዚአብሔር እሳትነት ሲነገር ኀያልነቱን ያመለክታል። የጌታችን ልብሱ የእሳት ነው ሲል ባሕርዩ ኀያል ነው ማለት ነው። ዙፋኑ የሐር ነው ማለት ሐር ነጭ እንደሆነ ሁሉ ክርስቶስም ጸዓዳ በመለኮቱ ይባላልና ባሕርዩ ንጹሕ ነው ማለት ነው (ዳን.7፥9)።

**፩፻፲፬. ማርያም የገነት እንኮይ ናት ሲል ምን ማለት ነው? እንኮይ ምንድን ነው?**

መልስ፦ እንኮይ ፍሬው የሚጣፍጥ የሚወደድ የዕፀዋት ዓይነት ነው። ማርያም የገነት እንኮይ ናት ማለት በአትክልት ቦታ ያለ እንኮይ የተወደደ እንደሆነ እመቤታችንም በአማኞች የምትወደድ መሆኗን ለመግለጽ እንኮይ ብሏታል።

**፪፻፲፰. ጻድቃን ማኅበራችንን በሰላም ጠብቅልን ብለው ጮሁ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ጮሁ ማለት አሰምተው ተናገሩ ማለት ነው። ጻድቃን ማኅበራችንን ጠብቅልን ብለው ጸለዩ ማለት ነው። ጻድቃን ትክክለኛ ክርስቲያን በመሆናቸው ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለሌላው ምእመንም [ለሕብረቱ] የሚጸልዩ ስለሆነ ጠብቅልን ብለዋል። ሕብረቱም ቤተክርስቲያን ስለሚባል ቤተክርስቲያንን ጠብቅልን ማለታቸው ነው።

**፪፻፲፱. አባ ጊዮርጊስ ገድሉን በትዕግሥት የፈጸመ ነው ይላል። አባ ጊዮርጊስ ይባላል ወይ?**

መልስ፦ "አባ" የሚለው አገላለጽ የክብር መገለጫ ነው። ለሽማግሌዎች፣ ለወላጅ አባት፣ ለመምህር፣ ለካህናት፣ ለመነኰሳትና ለመሳሰሉት ሲሰጥ ይስተዋላል። ሁሉም ግን ምስጢሩ ክብርን መግለጫዎች ናቸው። ቅዱስ ጊዮርጊስም ሰማዕተ ክርስቶስ ሆኖ ለምእመናን ሁሉ አርአያ ስለሆነ አባ ጊዮርጊስ እየተባለ በቅዱስ ያሬድ ተገልጿል።

**፪፻፳. ጌታም ሸክላ ሸክላ ሠሪን ይጠይቅ ዘንድ ታዝዟልን አላቸው ሲል ምን ማለት ነው? በመስቀል ሳለ መቼ ነው እንዲህ ያላቸው?**

መልስ፦ ክርስቶስ በመስቀል ሳለ የተናገራቸው ንግግሮች ሰባት ናቸው። እነዚህም አጽርሐ መስቀል በመባል ይታወቃሉ። ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ፣ አባ አመሐፅን ነፍስየ ውስተ እዴከ፣ አባ ሥረይ ሎሙ እስመ በዘኢየአምሩ ይገብሩ፣ ጸማዕኩ፣ የዎም ትሄሉ ምስሌየ ውስተ ገነት፣ ነዋ ወልድኪ ወነያ እምከ፣ ወይቤ ተፈጸመ ኵሉ። ሰዎች እስኪ ከመስቀል ውረድ ብለው እንደዘበቱበት በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጿል። "እመሰ ወልደ እግዚአብሔር አንተ ረድ እስኩ እመስቀልከ" እንዲል (ማቴ.27፥40)። ከአጻጻፍ ስልቶች አንዱ የሚያስኘውን እንደተባለ አድርጎ መግለጽ ነው። ሸክላ ሠሪ የተባለ ክርስቶስ ነው። ሸክላ የተባልን እኛ ነን። ሸክላ ሠሪ ሸክላውን እንደፈለገ ይሠራዋል እንጂ ሸክላ ሸክላ ሠሪን አያዝዘውም። በመስቀል ግን ፍጡር በፈጣሪ ተዘባብቷል። ፍጡር ፈጣሪን ለማዘዝም ሞክሯል። ይህ አካሔድ ተገቢ አለመሆኑን ለመግለጽ ጥያቄያዊ በሆነ መልኩ "ጌታም ሸክላ ሸክላ ሠሪን ይጠይቅ ዘንድ ታዝዟልን? አላቸው" ብሎ ጽፏል። ቅዱስ ያሬድ የሚያስኘውን እንደተባለ አድርጎ ጽፎታል። ይህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አገላለጽ ነው። "ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል" እንዲል (ማቴ.5፥43)። ጠላትህን ጥላ ተብሎ ባይጻፍም እንደሚያሰኝ ስለታወቀ ተገልጿልና።

**፪፻፳፩. ዓለምን ያድን ዘንድ የእውነት መንፈስ ጰራቅሊጦስን አወረደ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ዓለምን ማዳን የሦስቱ ማለትም የአብ፣ የወልድ፣ የመንፈስ ቅዱስ የአንድነት ግብር ነው። በማዳን ሂደት ቤዛ መሆን በተለየ አካሉ ለወልድ ይነገራል። ጸጋን ለሰው ልጆች በመስጠት ግን ሦስቱ አንድ ናቸው። የእውነት መንፈስ ጰራቅሊጦስን አወረደ የሚለውም ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ለሰው ልጆች ሰጠ ማለት ነው። በግብረ ባሕርይ ክርስቶስም መንፈስ ቅዱስ ሲባል ይገኛል። "ጠፈረ ጽድቅ ጠፈረ ሃይማኖት መንፈስ

ቅዱስ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ" እንዲል (ድጓ ዘፋሲካ):: መንፈስ ቅዱስም ወላዲ ሲባል ይገኛል:: "ወላዲ ውእቱ መንፈስከ" እንዲል (አረጋዊ መንፈሳዊ ድርሳን 35):: በግብረ አካል፣ በአካል ስም ግን አብ አብ ሲባል ይኖራል እንጂ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አይባልም:: ወልድም ወልድ ሲባል ይኖራል እንጂ አብ መንፈስ ቅዱስ አይባልም:: መንፈስ ቅዱስም መንፈስ ቅዱስ ሲባል ይኖራል እንጂ አብ ወልድ አይባልም::

**፪፻፳፪. ጌታችን ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ወርዶ ከተኛህበት ተነሥ አለው ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፡- ቅዱስ ጊዮርጊስ በገድሉ እንደተገለጸው ሞቶ ተነሥቷል:: ከተኛህበት ተነሥ ያለው ከሞትክበት ተነሥ ማለቱ ነው:: በዚህ ንግግሩም ጊዮርጊስ እየሞተ እየተነሣ አስተምሯል:: ሞትን መተኛት ማለት ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አገላለጽ ነው:: “ወዳጃችን አልዓዛር ተኝቷል ነገር ግን ከእንቅልፉ ላስነሣው እሄዳለሁ” እንዲል (ዮሐ.11፥11)::

**፪፻፳፫. በኍሩን ወደ ዓለም በላከው ጊዜ ለሰማይ አልነገረውም ከመላእክቶቹ ጋርም አልተማከረም ሲል ሰማይ ያለው ማንን ነው?**

መልስ፡- ይህ ዓይነት አገላለጽ አንድ ወገን ይባላል:: ይህም ማለት ሰማይ ያላቸውም መላእክት ናቸው:: ሰው የሚሆንበትን ጊዜ ለመላእክት አልተናገረም ማለት ነው:: "ወኢያእመረ መኑሂ እምእለ ሀለዉ ውስተ አርያም ምሥጢረ ምጽአቱ" እንዲል (ሃይ.አበ.60፥11):: እንዲሁም ሰማይ ማለት ልዑል ማለት ስለሆነ ልዑላን ሰዎችንም አላማከረም ተብሎ ይተረጎማል:: ስለዚህ ሰማይ መላእክትም፣ ታላላቅ ሰዎችም ተብሎ ይተረጎማል:: ልዑላን ሰዎችን ሰማያት ሲላቸው ማስረጃው "ወርእዩ ኪያሆን መላእክት ውሉደ ሰማያት" ሲል ይገኛል (ሄኖ.2፥2):: አላማከረም ማለቱም ልዩ ጊዜውን አልገለጸም ማለት ነው እንጂ ሰው እንደሚሆን በትንቢት ለሰዎች ተናግሯል::

**፪፻፳፬. የፋርስ ኮከብ የልዳ ፀሐይ ንዑድ ክቡር ቅዱስ ጊዮርጊስን እንደ ነፋስ ትቢያ በይድራስ ተራራ በተኑት ማለት ምን ማለት ነው? ፋርስና ልዳ የት አከባቢ ያሉ ናቸው? ኮከብ፣ ፀሐይ ሲልስ ምን ማለት ነው?**

መልስ፡- ፋርስ የምትባለው አሁን ላይ ኢራን ናት:: የፋርስ ግዛት ቀድሞ ሰፊ ነበር:: ልዳም ከፋርስ ግዛቶች መካከል አንዱ ነበር:: አሁን ላይ ግን ልዳ በእስራኤል ሀገር ውስጥ ትገኛለች:: ኢራንም ለብቻዋ ትገኛለች:: ከፀሐይ ክብር የኮከብ ክብር ያንሣል:: ፋርስ ሰፊ ነው:: በሰፊው ኮከብ ተብሏል:: ልዳ ትንሽ ቦታ ናት ከቦታዋ አንጻር ፀሐይ ተብሏል:: ምሥጢሩ ግን ሁለቱም ምሳሌ ነው:: በልዳ በፋርስ የከበረ ጊዮርጊስ ማለት ነው:: ጊዮርጊስን በደብረ ይድራስ በተኑት የተባለው ፈጭተው ቆራርጠው አካሉን በተራራው ዘሩት ማለት ነው::

**፪፻፷፫. ቅዱስ ጊዮርጊስ መንኰራኵርን በተመለከተ ጊዜ በመሞት ለመመስከር ጮኸ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ መንኰራኵር የሠረገላ ተሽከርካሪው ነው። ቅዱስ ጊዮርጊስን በዚህ መንኰራኵር ፈጭተውታል። በመንኰራኵሩ ሊፈጩት መሆኑን ባየ ጊዜ ሳይፈራ ሰማዕት ለመሆን ጮኸ ማለት አሰምቶ ተናገረ፣ ጸለየ ማለት ነው።

**፪፻፷፬. የሚካኤል ጌታ ኀሊና ወደ ማይደርስበት በደመና ዐረገ ይላል። በደመና ሲል ምን ማለት ነው? ዐረገ ሲልስ እንዴት ነው? ጌታ በርኅቀት ያረገበት ምክንያት በሥጋው ውሱን ቢሆን ነው። አሁን በሥጋው (በዓለመ ነፍስ) መደብ የት ነው ያለ?**

መልስ፦ በደመና ዐረገ የሚለው በክብር ዐረገ ማለት ነው። ክርስቶስ በሚያርግበት ጊዜ በባሕርዩ ክቡር መሆኑን ለመግለጽ ደመና ታይቷል (ማቴ.24፥30 አንድምታ ትርጓሜ)። እንጂ ደመና ተሸክሞት ዐረገ ማለት አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ በመሆኑ ለማረግ ሌላ ተሸካሚ አይሻም። "ወኢይቤ አዕረግዎ። መላእክት አሳረጉት አላለም። አላ ለሊሁ ዐርገ። እርሱ ራሱ ዐረገ አለ እንጂ። ወኢፈቀደ መራሔ ፍኖት ቅድሜሁ። በፊቱም በመንገድ የሚመራው መሪ አይሻም። ዳዕሙ ውእቱ ዐርገ ውስተ ፍኖት። በዚያ ስፍራ በዚያ ባሕርይ እርሱ ራሱ ዐረገ አለ እንጂ። እስመ ከመዝ ኢክህለ ኤልያስ ይዕርግ በዝንቱ መካን ከመ ክርስቶስ። ኀይላት አዕረግዎ ኀበ ተአዘዙ። ኤልያስን የታዘዙ መላእክት ወደታዘዙበት ቦታ አሳረጉት። ወቃለ እግዚአብሔርሰ ዋሕድ ለሊሁ ዐርገ በሥልጣኑ። አካላዊ ቃል ግን በሥልጣኑ ዐረገ። እስመ እግዚአ ኀይላት ውእቱ" እንዲል (ሃይ.አበ.67፥12-13)። ስለጌታ ዕርገት ስንናገር ሁለት ዕርገታትን እናስተውላለን። አንደኛው የሥጋ ዕርገት በማሕፀን ሲሆን ሁለተኛው የቃል ዕርገት በአርባ ቀን ነው (ሃይ.አበ.17፥9 ትርጓሜ)። የሥጋ ዕርገት ማለት ሥጋ በተዋሕዶ የቃልን ገንዘብ ገንዘብ አድርጎ በኪሩቤል ጀርባ ተቀምጧልና ይህንን ለመግለጽ ነው። በጊዜ ተዋሕዶ ለሥጋ ዕርገትን ስንናገር በዚያው ቅጽበት ለቃል ርደትን እንናገራለን። ድንግል ማርያምን የሥጋ ዕርገት የቃል ርደት ምክንያት የሆንሽ ብለን የምናመሰግናት ለዚህ ነው። የሥጋ ዕርገት የተባለበት ውሱን የነበረ ሥጋ ውሱንነቱን ሳይለቅ በተዋሕዶ በሁሉ ቦታ መኖርን ገንዘብ በማድረጉ ነው። ከዚህ የዕርገት ምስጢሩ አምላክ መሆን ነው። ለቃል የርደት ምስጢሩ ሰው መሆን ነው። የቃል ዕርገት በአርባ ቀን የሚለው በተዋሕዶ ሥጋን ገንዘቡ አድርጓልና የሥጋ ዕርገት ለእርሱ ስለሚነገር የቃል ዕርገት ተብሏል። እውነት ነው ውሱንነቱን አልለቀቀም አይለቅምም። ለዘለዓለም ውሱንም ምሉዕም ሆኖ ይኖራል። ሥጋ አልጠፋምና። የት ይኖራል ለሚለው ግን በመለኮቱ በሁሉ ምሉዕ ሆኖ ሲኖር በሥጋ የት እንዳለ የሚገልጽ አላገኘሁም። ስለዚህ ይህንን አላውቀውም።

**፪፻፷፮. ከሰው ቸር ገላውዴዎስን የሚመስል የለም ሲል ምን ማለት ነው? ሌሎች እንዴት ይታያሉ?**

መልስ፦ ይህ ገላውዴዎስ ሰኔ 11 ቀን በስንክሳር የሚታሰበው ታላቁ ሰማዕት ነው፡፡ እርሱን የሚመስል የለም የሚለው በሁለት መልኩ ይተረጎማል፡፡ አንደኛው በተፈጥሮ ገላውዴዎስን የሚመስል የለም፡፡ እርሱ ብቻ ሳይሆን ሁላችንም በተፈጥሮ ልዩ ነን፡፡ በዋናነት ቅዱስ ያሬድ ገላውዴዎስን የሚመስል የለም ማለቱ ግን በምግባር እንደ እርሱ ያለ የለም ማለቱ ነው፡፡ ብዙ ቅዱሳን አሉ አይደለም ወይ ለምን እንዲህ አለ ከተባለ ከኃጥኣን አንጻር የተነገረ ነው፡፡ እርሱ ጻድቅ ስለሆነ ከኃጥኣን እርሱን የሚመስል የለም ማለት ነው፡፡ በቅዱሳን ዘንድ የከበረ መሆኑን ለመግለጽም ይሆናል፡፡ ኮከብ እምኮከብ ይኄይስ ክብሩ እንዲል፡፡ እርሱ በክብር የሚበልጣቸው አሉና ከእነርሱ እንደእርሱ የሚሆን የለም ብሏል፡፡ ይህ የለም አንጻራዊ የለም ወይም አለመኖር ነው፡፡

፪፻፳፰. የመላእክት አለቃ ሚካኤል መለከትን በነፋ ጊዜ ሙታን ይነሣሉ ሲል እንዴት ነው?

መልስ፦ በሰማይ መለከት ኖሮ አይደለም፡፡ መለከት በስልት በስልት ሲነፋ የደስታ አዋጅ፣ የኀዘን አዋጅ፣ የክተት አዋጅ...ወዘተ መግለጫ ነው፡፡ ስለዚህ ሚካኤል የንጉሡ የክርስቶስ አዋጅ ነጋሪ ሆኖ ንቃሕ መዋቲ ብሎ አዋጅ ይናገራልና አዋጅ በተናገረ ጊዜ ሙታን ይነሣሉ ማለት ነው፡፡

፪፻፳፱. ኪሩቤል እና ሱራፌል የእግዚአብሔርን ዙፋን ስለሚሸከሙ በሁሉ ምሉኣን ናቸው የሚባል ሰምቻለሁ፡፡ ትክክል ነው?

መልስ፦ አይደለም፡፡ ስሕተት ነው፡፡ ማንኛውም ፍጡር ወሰን አለበት፡፡ ኪሩቤል ሱራፌልም ምንም እንኳ ረቂቃን ፍጥረታት ቢሆኑም ወሰን ግን አለባቸው፡፡ የሚሸከሙት ዙፋን እግዚአብሔር በዘፈቀደ [በወደደ] የሚገለጥበትን ነው እንጂ እግዚአብሔርን ራሱን በባሕርዩ መሸከም አይችሉም፡፡ እርሱ ይሸከማቸዋል እንጂ፡፡

፪፻፴. አባ ገሪማ፣ ገላውዴዎስ እና  ሠርፀ ድንግል አገራቸው የት ነው?

መልስ፦ አባ ገሪማ በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ከመጡ ተስዓቱ ቅዱሳን አንዱ ሲሆን የትውልድ ቦታው ሮም ነው (ስንክሳር ሰኔ 17)፡፡ በድጓው የተገለጹት ገላውዴዎሶች ሁለት ናቸው፡፡ መደበኛው ሰማዕቱ ቅዱስ ገላውዴዎስ ነው፡፡ ይህም ሀገሩ ሮም ነው (ስንክሳር ሰኔ 11)፡፡ ሁለተኛው የተድባበ ማርያምን ሕንፃ ቤተክርስቲያን ያሠራውና በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው ኢትዮጵያዊው ንጉሥ አፄ ገላውዴዎስ ነው፡፡ ሠርፀ ድንግል የተባለውም በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ የኢትዮጵያ ንጉሥ የነበረው አፄ ሠርፀ ድንግል ነው፡፡

፪፻፴፩. ሚካኤልን በፍጥረታት ሁሉ ላይ ሾመው ይላል፡፡ ምን ማለት ነው?

መልስ፦ በፍጥረታት ሁሉ ሾመው ማለት ለፍጥረታት ሁሉ ይለምን ዘንድ ፈቀደለት ማለት ነው፡፡ መላእክት በአዕዋፋት፣ በመባርቅት፣ በብርሃናት፣ በዕፀዋት፣ በአራዊት፣

በእንስሳት፣ በግዑዛን ፍጥረታት...ወዘተ በመሳሰሉት ተሹመዋል። ሚካኤል ደግሞ ሊቀ መላእክት ነውና በሁሉ ተሹሟል ማለት ነው። ሹመታቸውም ከቀድሞ ጀምሮ [ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ] ነው።

**፩፻፴፪. አባ ገሪማ ጠዋት በጥበቡ ይዘራል በሠርክ ከእርሻው ይሰበስባል ሲል ምን ማለት ነው? የመደራ ቁስ ሲለውስ እንዴት ነው?**

መልስ፦ በገድለ ተስዓቱ ቅዱሳን እንደተገለጸው አባ ገሪማ ዕለቱን ዘርቶ ዕለቱን እህሉ እንዲደርስ አድርጎ ዕለቱን አጭዶ ዕለቱን ያገባ ነበር። ጠዋት በጥበቡ ይዘራል በሠርክ ይሰበስባል ማለቱ ስለዚህ ነው። በጥበቡ ማለቱ ይህ የሚሆነው በጸሎት በቅድስና ስለሆነ በመንፈሳዊ ጥበቡ ማለት ነው። የመደራ ቁስ ያለው ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የኖረበትና ያገለገለበት መደራ የምትባል ቦታ ስለሆነች የመደራ አገልጋይ ማለት ነው።

**፩፻፴፫. ሞገስን የተሞላ በጸጋ በሃይማኖትና በጽድቅ ፍጹም የሆነ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ በመሆኑ በሁሉ ነገር ፍጹም ነው። ሞገስን የተሞላ በጽድቅ ፍጹም ነው ማለት በባሕርዩ ሞገስ ያለው ጻድቀ ባሕርይ ነው ማለት ነው። በጸጋና በሃይማኖት ፍጹም ነው ማለት ለፍጡራን የሚሰጠው ጸጋ ለእርሱ በባሕርዩ ያለው ነው ማለት ነው።

**፩፻፴፬. አምላኮቻችን ሥላሴ ሆይ የሙሴ የምስጋና መሥዋዕታችሁን እነሆ እናቀርባለን ይላል። አምላኮቻችን ሲል ምን ማለቱ ነው?**

መልስ፦ የአንዱ አምላክ ሦስት አካል እንዳለው ለመግለጽ አማልክቲነ (አምላኮቻችን)፣ አጋዕዝቲነ (ጌቶቻችን) እንላለን። ቅዱስ ያሬድ አምላኮቻችን ብሎ የገለጸው "አጋዕዝተ ዓለም ሥላሴ (የዓለም ገዢዎች ሥላሴ" በሚለው አግባብ ነው። አብ አምላክ፣ ወልድ አምላክ፣ መንፈስ ቅዱስ አምላክ የሚለውን ለመግለጽ አማልክቲነ ብሏል። ነገር ግን በየራሳቸው የሚኖሩ የማይገነዛዘቡ ሳይሆኑ የሚገነዛዘቡ መሆናቸውን ለመግለጽ ደግሞ አሐዱ አምላክ እያልን እንናገራለን (1ኛ ሳሙ.28፥13 አንድምታ ትርጓሜ)። የሙሴ የምሥጋና መሥዋዕታችሁን እናቀርባለን ማለት እናመሰግናችኋለን ማለት ነው።

**፩፻፴፭. እኛ የሥላሴ ቤተሰቦች የሙሴን መና አንመኘውም ምግባችን የሚቀድስ ተናጋሪ ነውና ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ የሙሴ መና የተባለው ለእስራኤላውያን ምግበ ሥጋ ይሆናቸው ዘንድ የወረደላቸው ምግብ ነው (ዘፀ.16፥31)። አሁን ይህንን መና አንመኘውም። ምክንያቱም ይህን መና በልተውት ከቆይታ በኋላ መልሶ ረኀብ ይመጣል። እኛ የምንመኘውና የምንፈልገው መና የማያስርብና ዘለዓለማዊ ሕይወትን የሚያሰጥ መናን ነው። ይህ

ደግሞ የሚቀድስና የሚናገር ነው:: የሚናገርና የሚቀድስ ምግብ የተባለው ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ዮሐ.6፥32-48):: ተናጋሪ ማለቱ ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕርዩ የሚናገር ነባቢ ስለሆነ ነው:: የሚቀድስ ያለው ከኃጢአት የሚያነጻ ሕይወትን የሚባርክ በመሆኑ ነው::

**፪፻፴፮. ቁርቆስ በሦስት ዓመቱ ሃይማኖትን መመስከሩ ተአምር ነው? ወይስ የቁርቆስ ዕውቀት?**

መልስ፦ በእርግጥ መጠኑ ቢለያይም የሦስት ዓመት ሕፃንም ዕውቀት አለው:: ከሕፃንነቱ ጀምሮ ክርስትናን ስለተማረ በተማረው መጽናቱ የዕውቀትም የተአምርም ነው:: ባለው ዕውቀት እግዚአብሔርን ቢያመልክ እግዚአብሔር ደግሞ በተአምር ጸጋን ሰጥቶት እንደበቱን አርትቶለት ለሰማዕትነት ብቁ እስከመሆን ደርሷል::

**፪፻፴፯. ዲበ ሠረገላ ኤልያስ አነብረከ ሲለው ቁርቆስን ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ እግዚአብሔር ኤልያስን በእሳት ሠረገላና በእሳት ፈረስ ወደ ሰማይ አሳርጎታል (2ኛ ነገ.2፥11):: እግዚአብሔር በዚያ ኤልያስን ባሳረገበት ሠረገላ የቁርቆስን ሥጋ እንደሚያኖር ቃል ገብቶለታል ማለት ነው (ስንክሳር ጥር 15)::

**፪፻፴፰. ብርሃን የጋረደህ ደብረ ታቦር ሆይ ሰላም ላንተ ይገባል ሲል ምን ማለት ነው? በደብረ ታቦር ሙሴ በአካለ ነፍስ ነው የመጣው? ትጌይሰኒ መቃብርየ የሚል አለ?**

መልስ፦ ግዕዛን የሌላቸውን ፍጥረታት በሰውኛ ዘይቤ መናገር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘይቤ ነው:: "ወይቤልዋ ዕፀው ለራምኖን ንዒ አንቲ ንግሢ ለነ" እንዲል (መሳ.9፥14):: ደብረ ታቦር ሆይ ሰላምታ ለአንተ ይገባል ማለቱ የክርስቶስ ብርሃነ መለኮቱ ስለተገለጠበት ክብር ይገባዋል ማለት ነው:: የከበረ ቦታን ሰላም ማለት (መሳለም) ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስም ተገልጿል (ሕዝ.46፥3):: በደብረ ታቦር ሙሴ የመጣው ነፍሱ ከአካለ ነፍስ ሥጋው ከመቃብር ተነሥተው በተዋሕዶ ነው የመጣው:: ኤልያስም ካረገበት ከብሔረ ሕያዋን ነው የመጣ:: መቃብሬ ይሻለኛል አለ የሚለው አገላለጽ ብርሃነ መለኮቱን ማየት ባይችል ወደ መቃብር መግባቱን ለመግለጽ ነው:: "ወሶበ ሰምዐ ቃለ አብ ወድቁ ሐዋርያት ወኮኑ ከመ ምውታን ወተመይጠ ሙሴ ኀበ መቃብሩ ወኤልያስ ዐርገ ውስተ ሰማያት" እንዲል (ስንክሳር ነሐሴ 13)::

**፪፻፴፱. የቤተክርስቲያን ምሰሶዎች የምድር ዓይኖች ሆይ ሐዋርያት ትባላላችሁ የምድር ጨው ናችሁ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ሐዋርያት የቤተክርስቲያን ምሰሶዎች የተባሉበት ምክንያት ቤት በምሰሶ ጸንቶ እንደሚኖር ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ወንጌል በሐዋርያት ትምህርት ጸንታ ትኖራለችና ነው:: የምድር ዓይኖች የተባሉበት ምክንያት በዓይን ምክንያት ብርሃንን እናያለን:: በሐዋርያት ትምህርትም ብርሃን ክርስቶስን እናይበታለንና ነው (ዮሐ.8፥12):: የምድር

ጨው የተባሉበት ምክንያት ጨው የምግብ ማጣፈጫና የቊስል ማድረቂያ እንደሆነ ሁሉ ሐዋርያትም አልጫ የሆነውን ዓለም በትምህርታቸው ስላጣፈጡትና የቆሰለውን ዓለም በወንጌል ስለፈወሱት ነው።

**፪፻፴. ኢየሉጣ የጽጌረዳ ምንጭ የሆነ ቂርቆስን ወለደች ሲል ምን ማለት ነው? ሕፃን ቂርቆስም በጎልማሳ መንፈስ ለእናቱ ከስሕተት መዳኛ ሆናት ሲልስ ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ የጽጌረዳ ምንጭ የሚለው የጽጌ ረዳ ማቀፊያውን ነው። ነቅዐ=አቀፈ የሚል ምስክር አለና። በዚህ ጊዜ ጽጌረዳ የክርስቶስ ምሳሌ ይሆናል። ከጽጌረዳ ጥሩ መዓዛ እንደሚወጣ ሁሉ ከክርስቶስም ልጅነት፣ ክብር፣ ረድኤት፣ በረከትና የመሳሰሉት ጸጋዎች ይገኛሉና። ስለዚህ ቂርቆስ ነቅዐ ጽጌረዳ መባሉ ክርስቶስን የያዘ ማለት በክርስቶስ ያመነ ደግ ልጅ ማለት ነው። እንዲሁም ክርስቶስን የያዘ ማለት ለባሴ እግዚአብሔር ማለት ነው። በአጭሩ ኢየሉጣ ክርስቲያናዊ ደግ ልጅ ቂርቆስን ወለደች ማለት ነው። በጎልማሳ መንፈስ ለእናቱ ከስሕተት መዳኛ ሆናት ማለቱ ሕፃን ሳለ ሳይፈራ እንደጎልማሳ እንጽና ብሎ እናቱ ኢየሉጣን አጽናንቶ እርሷም በልጇ ቃል ተጽናናታ ድናለችና ነው።

**፪፻፴፩. የጻድቃን ነፍሳት ደናግል ይባላሉ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ድንግል የሚለው ቃል ተደንገለ=ተጠበቀ ከሚለው የግእዝ ቃል የሚወጣ ነው። ድንግል ማለት የተጠበቀ፣ የጠበቀ ማለት ነው። የጻድቃን ነፍሳት ድንግል የተባሉበት ምክንያት የእግዚአብሔርን ሕግ ስለጠበቁና ከክፉ ሥራ ሁሉ ስለሚጠበቁ [ስለሚርቁ] ነው።

**፪፻፴፪. በጥበብ መብራት በፊቱ የሚሄዱ ዐሥሩ ደናግል ስማቸው እምነት፣ ተስፋ፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥትና ፍቅር ናቸው ሲል ምን ማለት ነው? መቼ ዐሥር ሞሉ?**

መልስ፦ ዐሥር የሚለው ቃል ፍጹም ለማለት ነው እንጂ በብዛት ዐሥር የሚለውን አያመለክትም። ዐሥሩ ደናግል የተባሉት ብሎ የዘረዘራቸው ስድስት ናቸው። ይኸውም ፍጹም የሆኑ የፍጹምነት ሥራዎች መሆናቸውን ለመግለጽ ነው። ዐሥር የሚለው ብዛትን የሚያመለክት ቢሆን ኖሮ ስድስት ብቻ አይጠቅስም ነበር። ወንጌል ላይ በጥበብ መብራት በፊቱ የሚሄዱ አምስት እንደሆኑ ገልጿል። ከዚህ ዐሥር እንደሆኑ ገልጿል። ወንጌል ሃይማኖትን ከምግባር ይዘው የሚጸድቁት ሁሉም ሳይሆኑ ጥቂቶች መሆናቸውን ለመግለጽ በአንጻር የተናገረው ነው። ድን ዐሥር ያላቸው ሃይማኖትን ከምግባር የያዙትን ብቻ ያለምንም አንጻር ብቻቸውን ጠቅሶ ነው። ደናግል ብሎ የጠቀሳቸው ግን እምነት፣ ፍቅር፣ ተስፋ፣ ትዕግሥት፣ ሰላም፣ ደስታ ናቸው። እነዚህ ምግባራት ናቸው እነዚህን የያዘ ይጸድቃል ለማለት ነው እንጂ ትዕግሥት የሚባል አካልና ህልውና ያለው ነገር ኖሮ ትዕግሥት ይጸድቃል ለማለት አይደለም።

፩፻፺፫. ደብረ ታቦር የእግዚአብሔር መቅደስ ነው ሲል እንዴት ነው?

መልስ፦ መቅደስ የሚለው እግዚአብሔር በክብር የሚገለጥበትን ቦታ ነው። ሰሎሞን በሠራው መቅደስ "የእግዚአብሔር ክብርም የእግዚአብሔርን ቤት ሞልቶ ነበር" ተብሏል (1ኛ ነገ.8፥11)። በደብረ ታቦርም የእግዚአብሔር ወልድ ክብር ተገልጧልና ደብረ ታቦር መቅደስ ተብሏል (ማቴ.17፥2)።

፩፻፺፬. እግዚአብሔር ማርያምን ዘመንሽ ዘመኔ ነው መጠንሽ መጠኔ ነው አላት ይላል። እንዴት?

መልስ፦ ዘመንሽ ዘመኔ ነው ያላት እግዚአብሔር በአካል በህልውና ለዘለዓለም ኖሯል። እርሷ ደግሞ በኅሊናው በበጎ ታስባ ትኖር ነበርና ነው። ዘመንሽ ዘመኔ ነው ያላት በዚህ አግባብ ነው እንጂ ከጥንት ጀምራ በአካል በህልውና ነበረች ማለት አይደለም። መጠንሽ መጠኔ ነው የሚለው አብ ወልድን ያለ እናት እንደወለደው ሁሉ እርሷ ድንግል ማርያም ደግሞ ክርስቶስን ያለ አባት ወልዳዋለችና በዚህ አግባብ ነው።

፩፻፺፭. ከአብ በስተቀር የወልድን ሐሳብ የሚያውቅ የለም ከወልድ በስተቀር የአብን ሐሳብ የሚያውቅ የለም ሲል መንፈስ ቅዱስስ አያውቅምን?

መልስ፦ "በስተቀር" የሚለው አገላለጽ ከፍጡራን ሲለየው ነው እንጂ ከመንፈስ ቅዱስ ለመለየት አይደለም። ምስጢሩ "ከአብ በቀር የወልድን የመንፈስ ቅዱስን ሐሳብ የሚያውቅ የለም፣ ከወልድ በቀር የአብን የመንፈስ ቅዱስን ሐሳብ የሚያውቅ የለም፣ ከመንፈስ ቅዱስ በስተቀር የአብን የወልድን ሐሳብ የሚያውቅ የለም" ማለት ነው። ይህም ሦስቱ አካላት በአንድ ባሕርይ ስለሚገናዘቡ በሐሳብ፣ በፈቃድ፣ በክሂል፣ በሥምረትና በመሳሰለው አንድ ናቸው ማለት ነው።

፩፻፺፮. የዕለታት ሁሉ በኵር የሆነች እሑድ ትሰለጥናለች ይላል። አታልፍም ማለት ነው? ሰንበት ማለት ዕለቷ ራሷ ናት ወይስ ጌታ? ሰንበተ ብሂል ኢኮነ ዕለተ አላ አነ ውእቱ እግዚአብሔር እስመ ባቲ ተንሣእየ አግሐድኩ ለኵሉ ይላልና [ድርሳነ ሰንበት]። የማያልፉስ እነማን ናቸው?

መልስ፦ የዕለታት በኵር የሚለው አገላለጽ በተፈጥሮ የመጀመሪያዋ ዕለት በመሆኗ ነው። አታልፍም የተባለበት ምክንያትም ትንሣኤ ዘጉባኤ የሚደረግ በዕለተ እሑድ ነው። በዚያው መዓልትና ሌሊት ሳይፈራረቁ ፀሐያችን ክርስቶስ እያበራልን እንኖራለንና ነው። ክርስቶስ ራሱ ሰንበት ይባላል። ሰንበት ማለት ዕረፍት ማለት ስለሆነ ፍጹም ዕረፍታችን ደግሞ እርሱ ስለሆነ ነው። ለዘለዓለም ጸንተው የሚኖሩ የማያልፉ ፍጥረታት መላእክት፣ ሰው፣ እሑድ፣ መንግሥተ ሰማያት፣ ገሃነም ናቸው።

፩፻፺፯. ማርያም በሰማይና በምድር ያለች አዳራሽ ናት ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ማርያም አዳራሽ የምትባልበት ምክንያት ንጉሠ ሰማያት ወምድር ኢየሱስ ክርስቶስ የገባባት አዳራሽ በመሆኗ ነው፡፡ ይህም ማለት ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን እርሷን ቤት አድርጎ ኖሮባታልና ነው፡፡ በምድር አዳራሽ የከበሩ ሰዎች ይገባሉ፡፡ በሰማይ አዳራሽ የከበሩ መላእክት ይገባሉ፡፡ በእርሷ ደግሞ አምላክም ሰውም የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኖረባት የሰማይ አዳራሽ የምድር አዳራሽ ትባላለች፡፡

**፩፻፺፰. ስለ የዋህነቷ ርግቤ ይላታል፣ ስለዝምታዋ መልካሟ ይላታል፡፡ እመቤቴ የምስጢር ደጅ፣ የምትናገር ተራራ ናት ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ከአዕዋፋት ርግብ የዋሂት ናት፡፡ በዚህም ምክንያት ለየዋሃን ሰዎች ተወካይ ሆና ትቀርባለች፡፡ ድንግል ማርያም የዋሂት መባሏ ኀዳጊተ በቀል ስለሆነች ነው፡፡ ደግሞም በየዘመኑ እንደሚነሡ ቀባጣሪ ሴቶች ስላልነበረችና ዝምተኛ ስለነበረች የሰው ልጅ ውበቱ ደግሞ ዝምታው በመሆኑ መልካሟ ተብላለች፡፡ የምስጢር ደጅ መባሏ ምስጢር የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ በደጅ ይገቡበታል ይወጡበታል፡፡ ክርስቶስም ከእርሷ ተፀንሶ ከእርሷ ተወልዷልና ልጇ ምስጢር እርሷ ደጅ ተብላለች፡፡ የምትናገር ተራራ መባሏ ቀድሞ እግዚአብሔር በደብረ ሲና ተገልጦ ነበር፡፡ ያ ተራራ ግን አይናገርም፡፡ ከድንግል ማርያም ሲገለጥ ግን እርሷም የምትናገር በመሆኗ የምትናገር ተራራ ተብላለች፡፡ ተራራ መባሏ ስለ ልዕልናዋ ነው፡፡

**፩፻፺፱. ማርያም አዲስ መርከብ፣ የኢሳይያስ የተጠማች ምድር ናት፣ አፏ እንደ እንኮይ ነው፣ ዓይኖቿ የርግብ ናቸው፣ መናን የተሸከመች ፈጣን ደመና ማርያም ናት ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ኖኅ በመርከብ ከጥፋት ውሃ ድኗል፡፡ የሰው ልጅ ሁሉ ደግሞ ከመርገም የዳነባት አዲሲቷ መርከብ ድንግል ማርያም ናት ማለት ነው፡፡ በቀድሞዋ መርከብ ኖኅ ነበረ፡፡ ኖኅ ማለት ዕረፍት ማለት ነው፡፡ በአዲሲቷ መርከብ ደግሞ ዘለዓለማዊ ዕረፍት የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ነበረና፡፡ የተጠማች ምድር የሚዘንብባትን ዝናም ትቀበለዋለች፡፡ ድንግል ማርያምም ዝናም የተባለ ወልደ እግዚአብሔርን በሥጋ ፀንሳዋለችና የተጠማች ምድር ትባላለች፡፡ "ወያስተርኢ በጽዮን ከመ ፈለግ ዘይውኅዝ ክብሩ በምድር ጽምዕት" እንዲል (ኢሳ.32፥2)፡፡ እንኮይ በበረሃ የሚገኝ ጣፋጭ ፍሬ ነው፡፡ ድንግል ማርያምም በክፉው ዓለም የተገኘች ንጽሕትና ተወዳጅ እናት ናትና፡፡ ዓይኖቿ የርግብ ነው ማለት የርግብ ዓይን አጥርቶ እንደሚያይ ሁሉ እርሷም እግዚአብሔርን በንጽሕና የምታይ ናትና ነው፡፡ መናን የተሸከመች ደመና ስትባል መና የተባለው ራሱ ክርስቶስ ነው (ዘኍ.11፥7)፡፡

**፩፻፶. መላእክት እንድርያስን ተሸክመው ሰውን ከሚበ*ሉ ሰዎች ሀገር አደረሱት ይላል፡፡ ሰውን ከሚበ*ሉ ማለቱ እንዴት ነው?**

መልስ፦ የሰውን ክብር ባለማወቅ ሰይጣን ያደረባቸው ሰውን የሚበ*ሉ ሰዎች ስለነበሩ እንድርያስ የክርስቶስን ወንጌል ለማስተማር ወደእነዚህ ሀገር ሄዶ ነበር ማለት ነው።

፩፻፶፮. የጳውሎስ ፍጽምት ድንኳን የልጇ አገልጋይ ዳዊት በመሰንቆ እየዘመረ ከሚያረጀው ዓለም ወደማያረጀው ዓለም ሄደች ሲል የዳዊት መሰንቆ ምንድን ነው?

መልስ፦ የጻድቃን ነፍሳት ከሥጋቸው ተለይተው በሚሄዱ ጊዜ ዳዊት በመሰንቆ እግዚአብሔርን እያመሰገነ፣ መላእክትም እያመሰገኑ [በይባቤ መላእክት] በደስታ ይሄዳሉ። የዳዊት መሰንቆ መምታት በአካለ ነፍስ፣ በረቂቅ መሰንቆ እንጂ ግዙፍ መሰንቆ ይመታል ለማለት አይደለም።

፩፻፶፯. ተክለ ሃይማኖት የጋዲ የወይን ቦታ ነው ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ጋዲ የወይን ሀገር ነው። የጋዲ ወይን ስመጥርና ታዋቂ እንዲሁም ተወዳጅ ነው። ተክለ ሃይማኖት የጋዲ ወይን ቦታ ሲባል የጋዲ ወይን የተባለ ክርስቶስ ነው (ሲራ.34፥27 ትርጓሜ)። ቦታ የተባለው ተክለ ሃይማኖት ነው። ተክለ ሃይማኖት በክርስቶስ የሚያምን ቅዱስ በመሆኑ በመሆኑ የጋዲ ወይን ቦታ ተብሏል።

፩፻፶፰. በየዘመኑ እንዴት እንደሠራ አይቼ እግዚአብሔርን እያመሰገንሁ ወደ ገዳም ወጣሁ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ቅዱስ ያሬድ ብዙ ጊዜ በብሉይ ኪዳን የተደረጉና የተነገሩ ነገሮችን በማጣቀስ አዲስ ድርሰትን ይናገራል። "እግዚአብሔርን እያመሰገንኩ ከገዳም ወጣሁ" የሚለው ንግግሩ "ወነለፍኩ እንተ ገዳም እንዘ እሴብሖ ወአእኵቶ ለእግዚአብሔር በእንተ ስብሐቲሁ ዘይገብር በበመዋዕሊሁ" ከሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተወሰደ ነው (ዕዝ.ሱቱ.12፥58)። ለጊዜው ዕዝራ ከገዳም ሄዶ በየዘመናቱ የተደረጉ ብዙ ምሥጢራት ተገልጸውለት በዚህ ምክንያት እያመሰገነ መመለሱን ይገልጻል። ቅዱስ ያሬድም በየዘመናቱ የተደረገውን ነገር እያሰበ ማመስገኑን ይገልጻል። ወደ ገዳም ወጣሁ ማለቱ ወደ ገዳም ቅዱስ ያሬድም ከአክሱም ወደ ስሜን ተራሮችና ወደ ሌሎችም ገዳማት እያመሰገነ መሄዱን ያመለክታል።

፩፻፶፱. ውሃን በደመና ሲያቁር ደመናው አይቀደድም ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ውሃ በደመና አይበት ተቋጥሮ በነፋስ ተጭኖ ከውቅያኖስ ተጨልፎ ወደ ሰማይ ይወጣል። ከዚያም በመጠኑ በመጠኑ ይዘንማል። የደመና አይበት ውሃውን ሲቋጥር አይቀደደም ማለቱ ነው። ይህም እግዚአብሔር በከሀሊነቱ ያስቻለዋልና ነው።

፩፻፶፲. በሁሉ አንደበት የምትመሰገኚ ማርያም ሆይ ንዕድ ክብርት ነሽ ሲል ምን ማለት ነው? የማያመሰግኗት አሉ አይደል?

መልስ፦ "ሁሉ" የሚለው ቃል ፍጹም ሁሉ አይደለም። አንጻራዊ ወይም ብዙውን ሁሉ በሚለው አግባብ የተነገረ ነው። በ99ኙ ነገደ መላእክት፣ ከሰውም በአማኙ ዘንድ ትመሰገናለችና በሁሉ አንደበት ትመሰገኛለሽ ብሏል።

### ፪፻፶፯. ሩፋኤል ካህን ነው ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ካህን ማለት አገልጋይ ማለት ነው። ቅዱሳን መላእክትም እግዚአብሔርን በምስጋና የሚያገለግሉ በመሆናቸው ካህናት ይባላሉ። ሩፋኤል ካህን መባሉ ስለዚህ ነው።

### ፪፻፶፰. መለኮትና ፍቅር በእርሷ ላይ ያደሩ የወልድ ጌጥ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ጌጥ ባለጌጡን ያስከብራል። ድንግል ማርያም የወልድ ጌጥ ናት መባሏ በእርሷ የሚመሰገንባት በመሆኑ ነው። በደግ አማኝ እግዚአብሔር ይመሰገናልና። "ከመ ይሰባሕ ስሙ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ በላዕሌክሙ። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስሙ በእናንተ ይመሰገን ዘንድ" እንዲል (2ኛ ነገ.1፥12)። መለኮትና ፍቅር በእርሷ ላይ ያደሩ የሚለው አብ ለአጽንዖ፣ መንፈስ ቅዱስ ለአንጽሖ፣ ወልድ ለተሰብኦ አድረውባታልና። ባለጌጥ ከጌጥ የበለጠ ክቡር እንደሆነ ሁሉ እግዚአብሔርም ከድንግል ማርያም የበለጠ የከበረ ነው። እርሱ የባሕርይ አምላክ ነውና።